ፍኖተ
# ነፃነት
ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ 6:00
2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.34

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## የሚያስደንቀው ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ይህንን ሁሉ ተቋቁመው እዚህ መድረሳቸው ነው

የተከበሩ አቶ ገብሩ ገ/ማሪያም ዑቱራ

6



## ኢመማ የኢትዮጵያን መምህራን ያዋረደ የደመወዝ ጭማሪ

ከመ/ር ቀለሙ ሁነኛው

13

## የአንዱዓለም አራጌ ደብዳቤ አትላንታ ላይ በጨረታ አንድ ሺ ዶላረ ተሸጠ

ከትላንት በስቲያ በሰሜን አሜሪካ አትላንታ የአንድነት ፓርቲ ደጋፊዎች የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት እንዳደረጉ የመረጃ ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ:: የመረጃ ምንጮቻችን እንደገለፁት “የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ም/ሊቀመንበር አቶ አንዱዓለም አራጌ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት የተፈፀመባቸውን የመግደል ሙከራ ያጋለጡበት ደብዳቤ ለተሰብሳቢው የተነበበ ሲሆን ደብዳቤው ገቢው ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ማጠናከሪያ የሚውል ለጨረታ ቀርቦ አንድ ሺ ዶላር ተሸጧል::” ተብሏል::

ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት “በኢህአዴግ አስተዳደር በአገር ቤት ውስጥ ሕይወታቸው ላለፉት ዜጐች የሕሊና ፀሎት የተደረገ ሲሆን የአንድነት አትላንታ ድጋፍ ሰጪ አካል ሊቀመንበር አቶ ግርማዬ ግዛው ንግግር ማድረጋቸው ተገልጿል:: የስብሰባው የክብር እንግዳ የሆኑት የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አቶ ስየ አብርሃ ንግግር አድርገዋል:: አቶ ስየም “በኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና መስፋፋቱን ሕወሓት የአቶ መለስና የወ/ሮ አዜብ መስፍን እየሆነ ነው፤ አሁን ያለው የፌዴራል ፖሊስ ፓራ ሚሊተሪ ነው:: ተቃዋሚዎችን በኃይል ለመደምሰስ የተቋቋመ ነው:: አረቦች ፍርሃትን አሸንፈዋል:: ኢትዮጵያውያኖች በመከራ ውስጥ ስለቆዩ ፍርሃት ውስጥ ናቸው:: የታመቀ ቁጣ በቃ ብሎ ሲነሳ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መልክ ይቀየራል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ጥፋት ተፈጽሟል:: የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ጠላት አይደለም:: ደርግ በግዳጅ ወገን ላይ እንዲተኩሱ አድርጓቸዋል:: በመጨረሻም ደርግን አንዋጋም ብለዋል:: ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም አያስጠብቅም:: እኔና አቶ ግርማዬ በአንድ ግንባር ላይ እርስ በእርስ ተዋግተናል:: እሱ ኢህአፓ እኔ ህወሓት ሆኜ ተዋግተናል:: ዛሬ አንድ መድረክ ላይ ተቀምጠን ለአንድ ፓርቲ ዓላማ እየታገልን ነው:: በጦርነት በየአቅጣጫው በርካታ ሰዎችን አጥተናል:: ቁርሾ መኖር የለበትም::

በፖለቲካ ሕይወት ስትኖር ሁሉም ሰው ይወደኛል ብሎ ማሰብ አያስፈልግም:: ሁላችንም ክንዳችንን አስተባብረን እንነሳ::” በማለት ንግግር ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል::

## ሕጋዊ የፍርድ ሂደትን ባልተከተለ ሁኔታ የታሰሩ ዜጐች በአስቸኳይ እንዲፈቱ መኢአድ ጠየቀ

10

## የመምህራን ደሞዝ ጭማሪ ቁጣን ቀሰቀሰ ተባለ

**- ሥልጠና የማይወስድ መምህር በየትኛውም ግል ት/ቤት ማስተማር እንደማይችል ተጠቆመ**

በቅርቡ በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ተነስቶ የነበረው የመምህሩ የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ ሰሞኑን በተጨመረው አንድ እርከን ደሞዝ ጭማሪ አነጋጋሪ እየሆነ መሆኑን የዜና ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ:: የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት “ጭማሪውን በመቃወም የተቃውሞ ፊርማ እየተሰበሰበ ነው” ይላሉ:: አንዳንድ መምህራን “ጭማሪው የሚያስተላልፈው መልዕክት መንግስት ለመምህሩ ያለውን ንቀት ያሳየበት ነው” ሲሉ የመምህራን ማህበሩ አመራሮች በበኩላቸው “ጭማሪው አበረታች ነው” ብለውታል::

አንዳንድ መምህራን ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት “አሁን ያለው የመምህራን ማህበር የመምህሩ ትክክለኛ ወኪል የነበረውን ነባሩን ማህበር ያፈረሰ ነው:: በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ መምህራን ማህበራት ጠንቅቀው ያውቁታል:: ይህ ማህበር የመምህሩን መብትና ጥቅም ለማስከበር የቆመ ሳይሆን የመንግስት ጉዳይ አስፈጻሚ ነው ተብሎ ስለሚታመንም የዓለም ማህበራት

ወደ 9 ዞሯል

## በዓረብ ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊንን መብት ለማስከበር፣ ሁላችንም ኃላፊነታችን እንወጣ !

4

## የአቶ መለስ እዉነተኛ የሥልጣን መሠረት ማን ነዉ?

15

# ማንም ሞትን ስለፈራ ዘለዓለም አይኖርም



ብስራት ወ/ሚካኤል

የወረቀት ጋጋታ የፖቲካ መድኃኒት ሊሆን አይችልም፤ የህዝብንም ሰቆቃ ይታደጋል ተብሎ አይታሰብም፡፡በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች አሉ፡፡ ስላሉት ችግሮች መባባስ ተጠያቂው ማነው? ገዥው ፓርቲ? ተቃዋሚዎች? ምሁራን ወይስ ህዝቡ ራሱ? እውነቱን ለመናገር መጠየቅ ካለባቸው ሁሉም አካላት ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም አሁን በሀገሪቱ ለተፈጠረው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ እያንዳንዳቸው አስተዋፅዖ አበርክተዋልና፡፡ አንዱ ሌላውን በመወንጀል የሀገሪቷን ችግርና የህዝቡን ስቃይ አራዝመውታል፡፡ በተለይ ፖለቲከኞች ድሮ የነበራቸውን ቂም በቀል መወጣጫ አሊያም ራሳቸው በፈጠሩት የበላይና የበታችነት ስሜት ከታሪክና ባህላዊ እሴቶች በተጨማሪ በክፋት አዲስ ማንነትን ለመፍጠር ይውተረተራሉ፡፡ እዚህ ላይ እንደቅደም ተከተላቸው ለሀገሪቱ የፖለቲካ ቤተሙከራም ዋነኞቹ ተዋናይ ስለሆኑ በአጭሩ እንያቸው፡፡

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ "የመጨረሻው ንጉሳዊ ሥርዓት" መውደቅ ትልቁ ምክንያት በትራንስፖርት ላይ የነዳጅ ዋጋ መጨመር፣ የሰራተኞች በተለይም የመምህራንና የወታደሩ ደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ገበሬው በሀገሩ የመሬት ባለቤት አለመሆን፣ የገዥዎችን የበላይነት የህዝብ የበታችነት ስሜት ሲንፀባረቅ ለ1960ዎቹ ዓ.ም አብዮት መቀጣጠል ለአፄ ኃ/ሥላሴ አስቀያሚ አወዳደቅ እንደምክንያት ሊጠቀስ ይችል ይሆናል፡፡ ዋናው ግን የሥርዓቱን ካባ ለብሰው የሚፈፅሟቸው መጥፎ ድርጊቶችና የወጣቶች ስሜታዊነት በስም በዚህም የዘውዳዊው ስርዓት ተሰናበተ፡፡ ከዚያም ያላሰበው ደርግ ሳይታሰብ በተከፈተው ቀዳዳ ከወታደራዊ ካምፕ ወጥቶ ስልጣን ጨበጠ፡፡

ደርግ (ወታደራዊው ኮሚቴ) በበኩሉ የተቀጣጠለውን የወጣቶች ስሜታዊነት አብዮትን በመጠቀም ጭሰኛ የነበረውን አብዛኛውን ገበሬ በአጠቃላይ ህዝቡን የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም የቤት መስሪያ ቦታ "መሬት ለአራሹ" የሚል አዋጅ አስነገረ፡፡ በጥቂቱም ቢሆን ህዝቡን በዜግነቱ ማግኘት የሚገባውን የከተማ ነዋሪ 500 ካሬ ሜትር በነፃ፣ የገጠሩ ህብረተሰብ ደግሞ 10 ሄክታር የእርሻ መሬት በነፃ እንዲያገኝ አስችሎታል፡፡ ነገር ግን ይህ ቅሬታ የነበራቸው ግማሹ የምስራቅ ሶሻሊስት ፖለቲካ ፍልስፍናን ሲያራግቡ ቀሪዎች ደግሞ "ተበለጥን፣ ተቀደምን" በሚል በበቀል የከተማ ውስጥ የደፈጣ ውጊያ ጀመሩ፤ ሌላው ጠብመንጃ (ነፍጥ) አንግቦ ጫካ ገባ፡፡

በስልጣን ላይ ያለውም ደርግ ወታደር ነበርና አፀፋውን መለሰ፡፡ በዚያን ወቅት የመጀመሪያውን የበቀል ጥይት በኢህአፓ "ነጭ ሽብር" በሚል በስውር ያቀዱትን በገሀድ ምሁር ሆኖ የእነሱ አባል ያልሆነውንና ከደርግ ጋር የሚሰራውን ሁሉ መግደል ተያያዙት፡፡ በዚህም የዓይን እማኞች እንደሚሉት ከደርግ ባላነሰ የኢትዮጵያን ምሁራን በመግደል ኢህአፓ ዋነኛው እንደሆነ ያወሳሉ፡፡

በርግጥ በወቅቱ የደርግም ሆነ የኢህአፓ አባላት ጥልቅ ብሔራዊ የሀገር ፍቅር ስሜት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ በኋላ ግን ኢህአፓ ውስጥ መከፋፈል እንደተፈጠረና የሻዕቢያ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ የቀረም እንዳለ የሚናገሩ አሉ፡፡ ነገር ግን ያኔ የበቀል ዱላ ያነሱና ኢህአፓ የነበሩ ድርጅታቸውን ከድተው ኢህዴን ከዚያም ጠበብ ባለ መልኩ በሻዕቢያና ህወሓት አስተሳሰብ የተገነባውንብአዴን የሆኑ እንደ አቶ በረከት ስምዖን (ራሳቸው "በሁለት ምርጫዎች ወግ" ላይ እንደፀፉት) ዛሬ ስልጣን ላይ ናቸው፡፡ የኢህአፓው "ነጭ ሽብር" አፀፋም በደርግ "ቀይሽብር" ተጠናቀቀ ተባለ፡፡

ያ የበቀልና የመጠፋፋት ትውልድ ደግሞ በምስኪኖችና የዋህዎች መስዋዕትነት፣ በኢህአዴግ ስም ስልጣን ላይ በመውጣት የአንድ እናት ልጆችን መተላለቅ የበቀል ሐውልት በመትከል አዲስ ፀያፍ ታሪክ አሁን ባለው ገዥው ፓርቲ ተሰራ፡፡ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮችም የ17 ዓመቱን የትጥቅ ትግል ለማካካስ በሚል 21 ዓመት በሀገር መሪነት ወንበር ላይ ሆነው እንኳ በፈፀሙት በቀል የረኩ አይመስልም፡፡ በዚህም የጠባቧ ዋሻ የደደቢት በረሃው አስተሳሰብ፣ በሰፊዋ ኢትዮጵያ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የሚገርመው ኢህአዴግ ከደርግና ከአፄ ኃ/ሥላሴ በህዝብ የተጠሉ ድርጊቶችን ከሀገር ውስጥ፤ ከውጭ ደግሞ ቅኝ ገዥ የነበሩትን የእንግሊዝን ከፋፍለህ ግዛ (Divide and rule) እና የጣሊያንን ሴራ ይዞ በመተግበር የሚስተካከለው ያለ አልመሰለኝም፡፡

ከአፄ ኃ/ሥላሴ ከወረሳቸውና በህዝብ ከተጠሉት መካከል ህዝብ (ግለሰብ) የመሬት ባለቤትነቱን ተነጥቋል፡፡ በኢህአዴግ ደግሞ በህግ ማዕቀፍ በአዋጅ የመሬት ባለቤት የሆነ ግለሰብ የገዥው መደብ አመራር ካልሆነ በስተቀር የለም፡፡ የንግዱን ሁኔታ ስንመለከት በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን ለፊውዳሉ ስርዓት የቀረቡና የንጉሱ ቤተሰቦች የሀገሪቷን ንግድ ተቆጣጥረው ነበር፡፡ ለምሳሌ ማተሚያ ቤት (ብርሃን ሰላም)፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ፣ አንበሳ የከተማ አውቶቡስ፣ ዋቢ ሸበሌ ሆቴሎች እና ሌሎችም፡፡ በኢህአዴግም የንግድ ስርዓቱ በግለሰብ ነጋዴ አሊያም በመንግስት የሚመራ ገበያ ሳይሆን በኢህአዴግና አጋሮቹ ነው፡፡ ለምሳሌ ባለቤቱ በውል ያልታወቀው በትግራይ ህዝብ ስም የሚነገድበትና በወ/ሮ አዜብ መስፍን የሚመራው ኤፈርት ድርጅቶችና ዲንሾ፣ ጥረት፣ ወንዶ የመሳሰሉ ግዙፍ የንግድ ኩባንያዎች ተጠቃሽ ሲሆኑ ገበያውን በማመስና የተለያዩ በመንግስትና በጥረታቸው ያፈሩ ግለሰብ ነጋዴዎችን የገበያ ውድድር በመዝጋት ከንጉሱ ስርዓት ይመሳሰላል፡፡

ከደርግ በኢህአዴግ የተወረሰው ደግሞ አምባገነንነት ሲሆን የሚለየው በሱፍና በካኪ ልብስ አሊያም በስም ብቻ እንጂ በግፍ አፈፃፀም ድርጊቶቻቸው አንድ ናቸው፡፡ ሁለቱም ነፃ አስተሳሰብን አይፈቅዱም፣ ሁለቱም መለኮት (አምላክ) ነኝ ከማለት በስተቀር የዚህች አገር ፈላጭ ቆራጭ እኛ ነን ባዮች ናቸው፡፡ ሁለቱም አምባገነንነትን ህጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ በመክተት፣ አዋጆችን በማውጣት ህዝቡን በማስፈራራት፣ በመፈረጅና በማሰር አንድ ናቸው፡፡ በመግደልም ቢሆን ሁለቱም በአፈሙዝ ሥልጣን የያዙ በመሆናቸው እጆቻቸው በሀገር ልጅ ደም የተጨማለቀ ነው፡፡ እዚህ ላይ እኔ ለሀገር ሳይሆን ለስልጣን ስል ሰዎችን በግፍ አልገደልኩም፣ ንፁህ ነኝ የሚል ከሁለቱም ስርዓቶች አይኖርም፡፡ ምክንያቱም የገደሉትና የጨፈለቁት ቁንጫና ቲማቲም ሳይሆን የሰው ልጅ ነውና መቼም ቢሆን ከህዝብ አይሰወርም፡፡

ሌላው ኢህአዴግን ከእንግለዝ ቅኝ አገዛዝ ጋር የሚያመሳስለው "የከፋፍለህ ግዛ" ሴራ ሲሆን ይህም ጐጥንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እዚህ ላይ ለመሪዎቹ ያለውም ጠቀሜታ ህዝቡን በቋንቋና በጐሳ በመከፋፈል እርስ በእሰርስ እንዲጋጩ በማድረግ የቤት ሥራ መስጠትና ባተሌ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ህዝቡ ህብረት ወይም አንድነት የሚል ጥያቄ እንዳያነሳና ስለዜግነትና ሀገር እንዳያስብ ማድረግ ሌላው ስልት ነው፡፡ ለዚህም ከቀበሌ መታወቂያ ካርድ ይጀምራል፡፡ ይሄ በኢህአዴግ እንግሊዝ በገዛቻቸው ሀገሮች የተገበረችው በኢትዮጵያም ያውም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ተደግሟል፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የቀበሌ መታወቂያን ብንመለከት ዜግነት የሚል ጠፍቶ ብሔር በሚል ተተክቷል፡፡ ይሄንን ማንም በእጁ ያለ ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ይሄም የሚሞላውና የሚፈፀመው በኢህአዴግ እንጂ በህዝቡ ፍላጐት አይደለም፡፡

ከጣሊያን የተወረሰው ደግሞ በአድዋ ጦርነት ሽንፈት ከተከናነበች በኋላ ጣሊያን የበቀል ሴራ ስልት ጀምራ እንደነበር የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ ለምሳሌ ጣሊያኖች የሰፈሩበት ቦታ ያሉትን ነዋሪዎች "እናንተ ከሁሉም ታላቅ ናችሁ" የሚልና በኃይማኖትና ጐሳ የመከፋፈል ሴራ በማድረግ ህዝብ ማጋጨት ተፈፅሞ ነበር፡፡ ይሄንንም ኢህአዴግ ደግሞታል፡፡ የሚገርመው ለምን እንደሆነ ባይታወቅም ኢህአዴግ ለራሱም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ መልካም ነገርን መኮረጅና ማምጣት የሰማይ መና ያህል ርቆበታል፡፡ ክፉ ነገሮችን በመኮረጅና በመተግበር ግን ከዓለም የሚቀድመው የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ አዳዲስ ክፉ ነገሮች በመተግበርና ህዝብን በማመስ፣ የህዝብን ህልውና የሚፈታተኑ ድርጊቶችንና አዋጆችን በመተግበር ሀገሪቱን የዓለማችን የክፉ ድርጊቶች ፖለቲካ ቤተ ሙከራ በማድረግ ለተቃዋሚዎችም እያስተላለፈ ይገኛል፡፡ በዚህም ሀገሪቷ የህዝብን ችግርና ሰቆቃ በካባና ስም በመቀያየር ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሆኗታል፡፡

ተቃዋሚዎች ጋር ስንመጣ ደግሞ ፖለቲካ ሳይገባቸው ወደ ፖለቲካው የገቡ፣ ማውራት እንጂ መተግበር የማይቀናቸው፤ እርስ በርስ ተተብትበው በመጠላለፍ ካባቸው ፖለቲከኛ ውስጣቸው ባዶ የሆኑና ለህዝቡ ከንቱ የተስፋ ዳቦዎች አሉ፡፡ እነኚህም የህዝቡን ሰቆቃ ዕድሜ በማራዘምና የሀገሪቱን የፖለቲካ ቀውስ በማባባስ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

እነዚህ ውስጥ በስልት በገዥው ፓርቲ የሚቋቋሙ ድርጅቶችም የሉም ለማለት ባልደፍርም በ "ምርጫ ቦርድ" በኩል ከፍተኛ የገንዘብ ድጐማ የሚደረግላቸው እና በኪሳቸው ማህተም ይዘው የሚንቀሳቀሱም እንዲሉ ይነገራል፡፡ የአባሎቻቸው ቁጥርና የስራ ድርሻ ላይ ንፅፅር ተደርጐ ከ "ምርጫ ቦርድ" የሚሰጣቸው ድጋፍ ለህዝብ ይፋ ቢሆን አንድ ሰው ሊቀመንበርም፣ ፀሐፊም፣ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊውም፣ አባላትም ያው አንዱ ሰው ብቻ የሆነም አይጠፋም፡፡ የሚገርመው ይሄን /እዚህን የፖለቲካ ድርጅት የመሰረታችሁት ለምንድነው? በአግባቡ ፕሮግራም/ ፖሊሲ እና ደንባችሁን እንዲሁም ከሌሎች አቻዎቻችሁ የምትለዩበትን ዘርዝራችሁ አስረዱን ቢባሉ ምናልባት የቢሮ ወይም የመሳቢያ ቁልፍ ጠፋብኝ፣ ሌላ ጊዜ እስጥሃለሁ የሚሉም እንዳሉ መገመት ይቻላል፡፡

አንዳንዶች ተቃዋሚ የሆኑና የራሳቸው ፕሮግራምና ደንብ ኖሮአቸው ተግባራቸው የሚቃወሙትን ሆነው የሚገኙም አይጠፉም፡፡ ለምሳሌ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ውስጥ የትምህርት አቅምም ሆነ የአመራር ብቃት የሌላቸው ህዝብን እያገለገሉ ሳይሆን በህዝብ እየተገለገሉ ሰርተው የማያሰሩ የቢሮ ጡረተኞች በብዛት አሉ፡፡ እነኚህ ሰዎች በገበያ ዋጋ ተወዳድረው መስራት ስለማይችሉ የተሳሳተ መረጃ በማስተላለፍ ሀገር የሚያምሱ ዕዳዎች ናቸው፡፡ እነኚህ ሰዎች ለተማረው አሊያም ብቃት ላለው/ ላላት ከማስተላለፍ አጥፍተው መጥፋትን ይመርጣሉ፡፡ ለበላይ አመራርም ታማኝ በመምሰል ጭራ እየቆሉ የሚሙለጨለጩ ሳሙናዎች ናቸው፡፡ ስራቸው ሁሉ መልካምና ፍፁም ጥሩ እንደሆነ ይደሰኩራሉ፡፡ አመራሮችም ከአዲስ አስተሳሰብ ጋር ከመላመድና ከመሄድ በ1960ዎቹ ውስጥ የነበረውን አመለካከት በ2000ዎች ውስጥ ያንፀባርቃሉ፡፡ ይሄ በስፋት ልክ እንደ ኢህአዴግ ሁሉ ተቃዋሚዎች ጋርም ይስተዋላል፡፡ በአምባገነንነቱ ኢህአዴግን እየወቀሱ ራሳቸውም የግል ፍላጐታቸውን በህዝብ ትከሻ ተንጠልጥለው ለማራመድ ሲሉ የመሪነቱን ወንበር ከአቶ መለስ ዜናዊ ባላነሰ መልኩ የሙጥኝ እንደ መዥገር የሚሉ እንዳሉ ሊዘነጋ አይገባም፡፡

ሌሎቹ ሰርተው የማያሰሩ ወንበሩ ላይ ተኝተው የፓርቲ ጡረተኞችም አሉ፡፡ ይህን ስል ግን ዕድሜያቸው የገፋና የሀገር ስሜትና ተቆርቋሪነት ኖሮአቸው የሚሰሩትን ማለቴ አይደለም፡፡ እዚህ ላይ የፖለቲከኞች (expired date) ቢኖር ጥሩ ነበር፡፡ አንዳንዱ ደግሞ የሚሰሩ አባሎቻቸውን በጥርጣሬ በማየት፣ በመፈረጅና እንቅፋት በመሆን የእነሱን ሥንፍና እና የአቅም ማነስ እንዳይጋለጥ አላሰራ የሚሉም አይጠፉም፡፡ እነኚህም ከኢህአዴግ ባላነሰ የህዝብን የሰቆቃ ጊዜ የሚያራዝሙ ናቸው፡፡

ለሀገርና ለህዝብ ጥቅምና መብት እንታገላለን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችም ቢሆኑ ቢሮ ተቀምጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ከማንጋጋት በተግባር ወደ ህዝብ ወርደው ከህዝቡ ጋር ሊሰሩ ይገባል፡፡ በዚህም የሚከፈል መስዋዕትነት ካለ ለመቀበል በቁርጠኝነት መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ አይ ቢሮ ተቀምጠን እንሰራለን እያሉ የሚፈሩም ካሉ ለሚሰሩት መልቀቅ፣ የሚሰሩትንም ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ አለበለዚያ ሌላው በከፈለው መስዋዕትነት ስልጣን ላይ ለመቀመጥ መሞከር "ከእጅ አይሻል ዶማ" ዓይነት ነገር ነውና ጊዜ ሳይሰጠው ሊታሰብበት ይገባል፡፡ በተጨባጭ ሀገሪቱ ለውጥ ትሻለችና፡፡

ኢህአዴግ ካምፕ ውስጥ ያሉትም ቢሆኑ በልባቸው እየተቃወሙ በድብቅ ተፅዕኖ ፈጣሪ ተቃዋሚዎችን ሲያገኙ "በርቱ፣ ከጐናችሁ ነን" ከማለት እውነትን ይዛችሁ የሚመጣባችሁን ለመቀበል በመዘጋጀት የምትቃወሙትን በድፍረት ፊት ለፊት ልትቃወሙ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ሀገራችን ውስጥ የሚፈጠረው ችግር ሁሉንም ዜጋ ስለሚነካ ድብብቆሽ አያዋጣም፣ የሚከፈላችሁ ደመወዝም የህዝብ እንጂ የኢህአዴግ እንዳልሆነ በድፍረት መናገርና ሀገርንና ህዝብን የሚጐዳ ተግባር ሲፈፀምም አይሆንም፣ አይደረግም በማለት መድፈር ይጠበቅባችኋል፡፡ እናንተም ኢትዮጵያውያን ናችሁና አስቡበት፡፡ እዚህ ላይ አመራሮቻችሁ ኢህአዴግ ከሌለ ኢትዮጵያ ትበታተናለች የሚሉትን ደረቅ ፈሊጥ፤ ኢትዮጵያ ከኢህአዴግ በፊት ካለንበት ጊዜ በእጅጉ በተሻለ መልኩ እንደነበረችና ወደ ፊትም እንደምትኖር አስረግጣችሁ ልትናገሩ ይገባል፡፡

ፊደል ቆጥረዋል የተባሉ ምሁራንም ቢሆኑ በህዝባቸውና በሀገሪቷ ሀብት ከመቀለድ ያለፈ እዚህ ግባ የሚባል አስተዋፅዖ ሲያበረክቱ አይታዩም፡፡ አይደለም በፖለቲካና ማህበራዊ ህይወት በሚሰሩበትና በሚጠቀሙበት ሙያ እንኳ ለትውልድ አርዓያ መሆን የሚችሉ እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ እነኚህ ምሁራን ሙያቸው በማይገባው ሰው ሲደፈጠጥ ከማጉረምረም ባለፈ ድሮ የተማሩትንና የሸመደዱትን መልሶ ከመገልበጥ የዘለለ ለምን ሲሉ አይታዩም፡፡ እንዲህ ዓይነት "ምሁራን" ደግሞ ለሀገር እዳዎች ናቸውና ቢያንስ ለሞያቸው ሲሉ ሊቆረቆሩና ሊሰሩ ይገባል፡፡

እዚህ ላይ አንዳንድ በዕድሜ አንቱ የተባሉ ለወጣቱ ግን ምሳሌ መሆን ያልቻሉ "ምሁራን" ላሳደጋቸውና ለወለዳቸው ገበሬ እንኳ ሲበደልና ሲጨፈለቅ ሲያዝኑለት አይታዩም፡፡ ምሳሌ ያልሆኑለትን ወጣቱን ሲረግሙና አቃቂር ሲያወጡ ይታያሉ፤ ዕዳዎች፡፡ የሚገርመው ደግሞ አንዳንድ ለወገንና ለሀገር ተቆርቋሪ የሆኑ ጐልማሳ ፖለቲከኞችን

# ሙስና !? ኡ ! ኡ 2



ፕሮፌሰር ሰይድ ሐሰን
መሪ ስቴት ዩኒቨርስቲ (አሜሪካ)
(Murray State University)

"የሥልጣን ጠላፊው" ሙሳና (ግራንድ ኮረፕሽን) ተግባራትና ተግባራዊ ምሰሎች (Variation in the Pattern of State Capture Corruption)

ባለፈው ሳምንት ሙስናን በሚመለከት በሰፊው ለማንሳት መሞከሬ ይታወሳል፡፡ በዛሬው ጽሑፌም የዚሁ ቀጣይ የሆነውን ማብራሪያ አውድ በአውድ አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

ከዚህ በታች (በከፊል) የጠቀስኳቸው "የሥልጣን ጠላፊው" ሙስናዎች ከላይ በጠቀስኳቸው ሀገሮች ውስጥ (ኢትዮጵያንም ጨምሮ) የተከሰቱ ናቸው።

"የሥልጣን ጠላፊው" (state capture) ሙስና፤

የአንዲት ሀገርን ፖሊቲካዊና ኤኮኖሚያዊ አውታሮች ለመቀማት ካስቻሏቸውና ከሚያስችሏቸው አንዱና ዋናው መንገድ፤ የሀገሪቱን የሕግ፤ የአስተዳደር፤ የወታደራዊ፤ የሕግ አስከባሪ፤ ማለት የፍርድ ቤቶችንና የፖሊስ አውታሮችን(apparatus) ማላላት/ማዳከም/መበተን ወይም እንዲዳከሙ ማድረግ (weakening state institutions)ነው። እነዚህን አውታሮች ከማዳከሙ /ከመበተኑ ጋር ተያይዞ የሀገርቷን ሀብት መበዝበር በሰፊው ይካሄዳል፤ ለቀጣይ ምዝበራ አመቺ ሁኔታዎችንም መፍጠር አንዱ ተግባራቸው ነው።

የሥለጣን፤ የመንግሥት አውታርና የኤኮኖሚ ጠላፊዎቹ፤ የኤኮኖሚ ለውጡን (Economic Reform) ሙሉ በሙሉ እንዳይሳካ ከማድረጋቸውም በላይ፤ ለውጡ በተገቢው እንዳይከናወን፤ እንዲቀለበስም ያደርጋሉ። የኤኮኖሚ ለውጥ ሂደቱን ተጠቅመውም የራሳቸውን ሀብት ያካብታሉ። ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች መካከልም፤ በመንግሥት ሥር የነበሩትን ኩባንያዎችና የኤኮኖሚ አውታሮችን ወደ ግል ባለሀብትነት ለመለወጥ በሚደረገው የሀራጅ ሂደት በርካሽ ዋጋ ለራሳቸውና ለጥቅም ተጋሪዎቻቸው እንዲዛወሩ በማድረግ ነው።

በሥልጣን ላይ በመባለግና ኢኮኖሚውን ወደ-ግል ባለሀብትነት ለመለወጥ በሚደረገው ሂደት ላይ ጣልቃ በመግባታቸው የተነሳ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ ወደ-ግል ሀብትነት እንዳይሸጋገር መሰናክል ይሆናሉ። በዚህም የተነሳ የሀገሪቱን ኤኮኖሚ ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት እንዲጨናገፍ ስልጣንን ተጠቅመው ጋሬጣ ይሆናሉ። ይህ አይነቱ ክስተት የተጠናወታቸው ሀገሮችም፤ ወይ ሶሻሊስት፤ ወይ የገበያውን የኢኮኖሚ መስመር ሳይከተሉ የቀሩና የኮኖሚው መሻሻልም (privatization and reform) ተጨናግፎ ይቀራል።

"የኤኮኖሚውን ሥርዓት መለወጥ /ማሻሻል" (privatization and reform)ተብሎ የሚጠራውን እና በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ ድርጅት የሚገፋውን መርህ ተጠቅመው የተቀናበረ ዝርፊያ ያደርጉና ባንኮችን፤ በመንግሥት ሥር ያሉና የነበሩ ድርጅቶችንና ኩባንያዎችን፤ የአስመጭና ላኪ የንግድ ዘርፎችን፤ የአከፋፋይና የተራ ንግድ ዘርፎችን፤ የከተማ መሬትንና በተለይም የመገናኛ ዘዴዎችን (media) ሆን ብለው /ትኩረት ሰጥተው በቁጥጥራቸው ሥር ያስገቡና የራሳቸውን የላቀና ከፍ ያለ በተለይም ከፖለቲካው ጋር የተዛመደ ኢኮኖሚንም (empires and oligarchs) ይመሰርታሉ። ይህ ተግባር በአብዛኞቹ ድህረ-ኮሙኒስት (Post-communist) ሀገሮችም ወደ የሞኖፖሊ ያዘነበለ /ያዘመመ የኢኮኖሚ ሥርዓትና አያያዝ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።

የጠላፊዎቹ ቁጥጥርና ጣልቃ ገብነቱ በበዛባቸው ሀገሮች፤ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ፓርቲያቸው በሕግ አስከባሪና አስፈፃሚ ውስጥም ገብተው ለመቆጣጠር ችለዋል። ፍርድ ቤቶችንና የሕግ አስከባሪ አውታሮችን በመቆጣጠርና ከነሱም ጋር በመተባበርም፤ የሀገርን ሀብት ዘርፈዋል። ዜጎችን ያለ-ምክንያት እስር-ቤቶች ከተዋል። እንደ ማፊያ ሆነው በመደራጀትና በመሥራትም፤ ድራሻቸውንም አጥፍተዋል።

የጠለፉትን ሥልጣን ተጠቅመው ለግላቸው (ለቡድኖቻቸው) ለገነቧቸው/ለመሰርቷቸው የኢኮኖሚ አውታሮች (their own empires and oligarchs) በሕገ-ወጥነት ከወለድ ነፃ የሆነ "ብድር" እንዲገፋላቸው ያደርጋሉ። የሥራ ፈቃድን "ለወገኖቻቸው" ብቻ ያድላሉ፤ ያለ-ጨረታ ኮንትራት ይሰጣሉ፤ ከግምሩክና ከታክስ ክፍያ ነፃ ያስደርጋሉ። ብዙ ጊዜም "ብድር" ተብሎ የተሰጠው ሳይከፈል ይቀራል።

ከውጭ በእርዳታ የተገኙ ብድሮችንም ሆነ ችሮታዎችን እንዲሁም መዋዕለ-ንዋይ ለራሳቸውና "የእኛ" ለሚሏቸው አድሎ በማድረገ ይሰጣሉ። ያቋቋሟቸውን "ኩባንያዎች" ለመጥቅም፤ የውሸት (በማር የተቀባ እሬታዊ ሕጎችን- phony regulations) አውጥተው ይጠቀማሉ።

በዝርፊያ በመሠርቷቸው ታላላቅ አውታሮች (Economic Empires and Oligarchs) እራሳቸውንና በተወሰነ ደረጃም የሚያምኗቸውን ሰዎች የቦርድ አባልና መሪ በማድረግ ይሾማሉ። ይህ ተግባር የኢኮኖሚውን ዋና ዋና አውታሮች ለመቆጣጠር ከማስቻሉም በላይ፤ የገቢ ምንጮቻቸውን ያበዛላቸውዋል። በአስመሳይነት የፈጠሯቸውን "ኩባኒያዎች" (shell companies and oligarchs) ተጠቅመው የዘረፉትን ሀብት ወደ-ውጭ ሀገር ያሸሻሉ።

በጠለፋ ሙስና የተዘፈቁት ቡድኖች፤ የተወሰኑ ኦሊጋርኪ ተቋማትን በመገንባት ብቻ ሳይወሰኑ በየቦታው፤ በየከፍለ-ሀገሩ፤ በውጭ ሀገርም ጭምር የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፉን ለመቆጣጠር በርካታ የንግድ ዘርፎችን ያቋቁማሉ (በእንግሊዝኛው create constellation of businesses, crony capitalism and predatory activities የሚባለው ነው)።

የማፊያ አይነት፤ አድሎ የበዛበት፤ ዘረኝነትም የሰፈነበት የኢኮኖሚ አውታር እንደ-ሸረሪት ድር ዘርግተው "የእኛ ወገን አይደለም" የሚሉትን የግል ባለሀብት ያገለለ የኤኮኖሚ ሥርዓትን ይመሰርታሉ። የማፊያ ጠባይ ስላላቸውም የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች የበለጠ ሲቀናቸውና እነሱን ሲበልጧቸው፤ ይቀኑና ግለሰቦቹንና ድርጅቶቹን አስፈራርተው ወይም ቀምተው (Blackmailing private firms) ያባራሉ።

ሙስናው ተስፋፍቶ ሲመጣ፤ ከሕዝቡም ሆነ ከለጋሽ ሀገሮችና ድርጅቶች ቅሬታ ይነሳል። ሕዝቡንና ለጋሾቻን ለመሸንገል፤ ከእነሱ ቁጥጥር ሥር ያልወጣ የፀረ-ሙስናው ተቋምን ያቋቁሙና (phony anti-corruption regulations) ከእጃቸው እንዳይወጣ አድርገው ይመሠርቱትና በሙስና ላይ የሚደረገውን ጦርነት እንዲኮላሽ ያደርጋሉ። በግልም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች የተቋቋሙትን የፀረ-ሙሳና እንቅስቃሴዎችን ይጠልፉና በቁጥጥራቸው ያስገባሉ። የፀረ-ሙስናው ትግልም ተኮላሽቶ ይቀራል። ሕዝቡም በመግሥትና በፀረ-ሙሳና ተቋሙ ላይ ተስፋውን ያጣል።

የ"ሥልጣን ጠላፊ ሙስና" በተስፋፋባቸው ሀገሮች በመንግሥትና በፖለቲካ ፓርቲዎች፤ እንዲሁም በመንግሥታዊ ድርጅቶችና በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል መኖር የሚገባው ልዩነት የደበዘዘ ነው። ይህም የደበዘዘ ግንኙነት (ልዩነትም) የሙስና መስፋፋት ምክንያትና አንዱ ጠባዩም ነው።

በጠላፊ ሙስና የተመሰረቱት "ኩባንያዎች" ሀብት፣የፖለቲካ ፓርቲን ለመገንባት ሕገ-ወጥና አድሎአዊ በሆነ መልክ ይውላል።

ባጠቃላይ፤ የሀገሪቱን ዋና ዋና የደም-ሥር ሀብቶች በቁጥጥራቸው ውስጥ በማስገባትና የሞኖፖሊ ሥርዓትን በማስፈር አጠቃላይ የሀገሪቱን የኤኮኖሚ እቅድ ለመግታት እንዲያስችላቸው (በእንግሊዝኛው cornering) ካማድረግ አይቆጠቡም።

የሥልጣን ጠላፊው ሙስናም በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን በሀብት ካለመጠን እንዲናጥጡ ያደርጋል። በድሃና በሀብታም መካከል ያለውን የሀብት ልዩነት በከፋ መልኩ ይለጥጣል።

አንባቢ መርሳት የሌለበት ነገር ቢኖር ምንም እንኳ በአስተዳደር ብልሹነትና ህጎችንና ደንቦችን በመማረክ/በመጥለፍ የሚከሰቱት ሙስናዎች በሥነ-ልቦናና በተግባር ልንለያቸው ብንችልም፤ አብዛኛውን ጊዜ አንዱን ከሌላው መነጠል ያስቸግራል። በተለይም ህጎችንና ደንቦችን በመማረክ/በመጥለፍ የሚከሰተው ሙስና (state capture) የከፋ ስለሆነ በአስተዳደር ብልሹነት (administrative corruption) የሚከሰቱት ሙስናዎችንም ይጨምራል።

ማጠቃለያ፤ ማሳሰቢያና የትብብር መልዕካት

እነ አቶ መለስ ዘናዊ፤ ስብሀት ነጋ፤ በረከት ስምንና መሰሎቻቸው ስለ-ሙስና ማላዘናቸውና መጮሀቸው በሁለት መልክ መታየት ይችላል። በአንድ በኩል፤ ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት፤ ችግሩን ለማርከስ የታሰበ እርኩስ ተግባር ሊሆን ይችላል። እነ አቶ መለስ ዘናዊ፤ ስብሀት ነጋ፤ በረከት ስምንና መሰሎቻቸው ማወቅ ያለባቸው ነገር ቢኖር ግን፤ ይህን የሚያደርጉት ስለሙስና ችግር ለማላዘን ከሆነ የበለጠ ይከፋናል፤ ይሰድበናል እንጂ ሙስናው አይቀነስልንም። በኢትዮጵያ ተንሠራፍቶ ያለው አሰቃቂው የሥልጣን ጠላፊ (State Capture) ሙስና እንደሆነ፤ የሙስናውን መርዝ የሚረጨው በታላላቆቹ የኢሕአዴግ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንደሆነም ያውቃል።ሥልጣንን ተደግፈውና ጠልፈው የሀገሩ ኤኮኖሚ እንደተዘረፈም፤ ዘራፊዎቹ እነማን እንደሆኑም ያውቃል። ከላይ የዘረዘርኳቸው የሥላጣን ጠላፊ ግዳንግድ ሙስና ክስተቶችና ከዚያም የበለጡ ወንጀሎች (Variation in the Pattern of State Capture) በኢትዮጵያችን እንደተከሰቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ ያውቃል። እናንተም ታውቁታላችሁ፡፡ የተረጨውም መርዝ እታች ወርዶ መላ ቅጡን ያጣ መሆኑን በመርዙ በየለቱ

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

---

እየተደበቁ "በርቱ አይዟችሁ፣ ከጐናችሁ ነን" ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ለምን ፊት ለፊት ወጥተህ አሁን ያልከውን ከህዝቡ ጋር አትደግመውም? ሲባል "ልጆቼን ላሳድግ፣ ቤተሰብ አለኝ" የሚል መልስ ሲሰጡ ይሰማል፡፡ ተመልከቱ ሀገሪቷ ምስቅልቅሏ እየወጣ "ልጆቼን ላሳድግ" ይላል፡፡ ለመሆኑ እንዲህ ዓይነት ወላጅ እውነት ለልጆቹ አስቧልን? የልጆቹ መኖሪያ ሲፈርስ የት ይሆን ልጆቹ የሚያድጉት? እዚህ ላይ ፍርሃት በቤተሰብና በልጆች ስም መደለል አዋቂነት አይደለም፡፡ የዳር ተመልካች በመሆንም የሌላ ታሪክ ለመዘብዘብ ግን የሚቀድማቸው የለምና እውነት ለልጆቻቸው፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለሀገራቸው የሚያስቡ ከሆነ የሀገር ሸክም ከመሆን አለኝታ መሆንን ቢመርጡ ለክብራቸውም ሆነ ለታሪካቸው ይበጃል ባይ ነኝ፡፡ አሁን በሀገሪቱ ላለውና ለተፈጠረው ምስቅልቅልም እጃቸው እንዳለበት ሊያውቁት ይገባል፡፡

ሌላው የህዝቡ ሚናን ብንመለከት በፍርሃት ተሸብቦ በኢትዮጵያ ያልታየ ታሪክ ሲፈጥር ይታያል፡፡ በዚህም ሀገሪቷ በቴሌቪዥን ስትበለፅግ በተግባር ስትማቅቅ ጉንጭን ተደግፎ በየጓዳው ማጉረምረሙን ግን ይችልበታል፡፡ የሚገርመው ህዝቡ ራሱ ያለበትን የሰቆቃ ህይወት ከመረዳት ይልቅ የቴሌቪዥን መስኮት ብልፅግና ሲደሰኩር ይታያል፡፡ ግን ደግሞ እቤቱ ለብቻው ያጉረመርማል፣ ይበሳጫል ከዚህ ባለፈ ሁሉ በእጁ ሆኖ ይለምናል፡፡ ይሄንን ነው መፍራት፡፡ የሚገርመው በምርጫ ወቅት ለ3 ወራት ሆዳቸው ሙሉ ጓዳቸው ባዶ የሆኑ የሌሎች መጠቀሚያ የሆኑም እንዳሉ ቤት ይቁጠረው፡፡ በመጨረሻም ቤሳቤስቲን ሳያገኙ የኑሮ ውድነቱ ከቀን ወደቀን እንደ ክረምት ደመና ሲጫናቸው ይታያል፣ ምርጫው ካለፈ በኋላም የመረጥኩት ለዚህ ነው? ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰዎች አሁንም አልገባቸውም ማለት ምክንያቱም እነሱ በፈቃዳቸው የምርጫ ወቅት መጠቀሚያ ካርድ እንጂ እንደዜጋ ሲታሰቡ አይታይምና፡፡ በእርግጥ እንዲህ ዓይነት ሰው ያውም መብቱንና ክብሩን በ3ወርና በሳምንት ሆዱ የሚቀይር ከሆነ ጥፋተኛው ራሱ እንጂ ተደልሎ የመረጠው አካል አይደለምና፡፡

የሚገርመው ገዥውንም ሆነ ተቃዋሚዎችን ወዳልሆነ አቅጣጫ ሲጓዙ ማስተካከል የሚችልበት አቅም እያለው ኃይሉን ግን መጠቀም አልቻለም፡፡ ለመብቱም ሌላ ሰው እንዲጮህለት እና እንዲታገልለት ይፈልጋል፡፡ እውነታው ግን እያንዳንዱ ለመብቱ እራሱ እንጂ ሌላ እንዲታገልለት ማሰብ ከሰውነት ጐዳና የመውጣት ያህል ነው፡፡ እዚህ ላይ ዕድሜያቸው ያልደረሱ ህፃናትን ያካትታል ማለት አይደለም፡፡ እነሱን በሚመለከት ወላጆቻቸው ናቸው ዕዳ ያለባቸው፡፡ ይህ ማለት ለብሔራዊ ውትድርና ሲጠየቅ ቀሚስና ሻሽ ለብሶ "ሴት ነኝ" እንዳለውና ሁልጊዜ በየዓመቱ ጊዜ ቆሞ የጠበቀ ይመስል ዕድሜያቸው ሲጠየቅ አንድ ዓይነት ዕድሜ የሚናገሩትን ሰነፎች አይመለከትም፡፡

በአጠቃላይ በገዥው ፓርቲ፣ በተቃዋሚዎች፣ በምሁራንና በህዝቡ መካከል ትልቅ የታመቀ የለውጥ ፍላጐት ይንፀባረቃል፡፡ ነገር ግን ሁሉም በፍርሃት ተውጧል፡፡ ተቃዋሚዎች ጋር ስንመጣ ደግሞ ወንበር ላይ ተቀምጠው የሚጠሩና የቢሮ ውስጥ ፖለቲካ የሚያራምዱ በህዝብ ስም የሚነግዱ በተግባር ግን ባዶ የሆኑ አሉና ህዝቡም ለይቶ የራሱን አስገዳጅ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ጦርነት፣ ብጥብጥ፣ ሁከትና ዝርፊያ ይፈፀም ማለት አይደለም፡፡ በተግባር ሊያታግላቸው ያልቻለውንና ሰርተው የማያሰሩ የሀገር ሸክም የሆኑ ፖለቲከኞችም የህዝብን የሰቆቃ ዕድሜ ከማራዘም ተቆጥበው ቁርጠኛ እንዲሆኑ የመለየትና የማጥራት ሥራ መስራት አለበት፡፡ ፖለቲከኛውም ከፍርሃት ተላቆ በመድፈር እውነተኛ ታጋይ ሊሆን ይገባዋል፡፡ አለበለዚያ እቤቱ መቀመጥ አለበት፡፡ ሀገሪቷም እየተጓዘችበት ያለው ሁኔታ ለውጥን የሚጠይቅ ነውና ኢትዮጵያን የዓለማችን የፖለቲካ ቤተሙከራ ከማድረግ ልንታደጋት ይገባል፡፡

ማንም ሰው ቢሆን ለውጥ ከፈለገ በተግባር ከጓዳ ወጥቶ መንቀሳቀስ አለበት፣ የተበታተኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ከ93 አሊያም ከ65 ድርጅትነት ቢያንስ በሚያስማማቸው ተስማምተው የሀገርንና የህዝብን ጥቅም በማስጠበቅ ወደ አራት /አምስት በመምጣት ጠንካራ ተፎካካሪ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይሄ ደግሞ የህዝብንም ድምፅና ሐሳብ ከመበታተን ይታደጋል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በየቢሮ መብዛት የዴሞክራሲ መገለጫ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ሲባል አንድ አምባገነን ይምራ ማለት ሳይሆን ፖለቲከኞች ወደ ውህደት ማምራት አለባቸው ለማለት ነው፡፡ ለዚህ ሁሉም ለለውጥ መድፈር አለበት፡፡ ማንም መኖርን ስለወደደ ከመሞት አያመልጥም፤ ሞትን ስለፈራም ዘለዓለም አይኖርም፡፡ የአንዲት ቀን የነፃነት ህይወት ሺህ ዓመት የሰቆቃ ዕድሜን ታስንቃለችና፡፡ ስለዚህ ሁሉም ዜጋ ነፃነትን ሲሰብክ ቅድሚያ ራሱ ነፃ መውጣቱ አለመወጣቱን በመፈተሽ ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ፣ ለነፃነቱም መድፈር አለበት፡፡

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ። ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው።

**ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል። የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን። ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ**

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤ.ቁ 028

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መሥፍን

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
አንዱዓለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

ህትመት ክትትል፡-
አያክሉህም ጀንበሩ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ
ስልክ +251 118-44 08 40
+251 922 11 17 62
+251 926 81 46 81
+251 913 05 69 42
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288



# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓረብ ሀገሯት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊንን መብት ለማስከበር፣ ሁላችንም ኃላፊነታቸን እንወጣ !

ገዥው ፓርቲ ለተከታታይ ዓመታት ባለሁለት አሀዝ ኢኮኖሚዊ ዕድገት እንደተመዘገበ፣ ድህነት በገጠርና በከተማ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሸነፈ መምጣቱን እየነገረን ይገኛል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ የትግበራ ዓመት ከድህነት በታች የሚገኙ ዜጎች 22 በመቶ ብቻ እንደሚሆን ተነግሮናል፡፡ ይህ ሳይበቃ አስገራሚ በሆኑት የመንግስት መረጃዎች በዜጎች መካከል ያለው የገቢ ክፍፍል ልዩነት (በተለይ በከተማ) እንደቀነሰ ተገልጧል፡፡

በተጨባጭ የምናየው እዉነታ ግን ፈረንጆች የሚሉት (common intuition) ከዚህ በእጅጉ የራቀ ነው፡፡ መልካም አስተዳደር የማምጣት ግብ በወረቀት ላይ የቀረ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ብዙ ሲባልለት የነበረውና ከፍተኛ ሃብት የፈሰሰለት ቢ.ፒ.አር (BPR) ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ሳይችል ቀርቷል፡፡ ተደጋግሞ እንደተነገረው ሙስና የሥዓቱ መገለጫ ሆኗል፡፡ የኑሮ ውድነቱ ከቁጥጥር ውጭ ወጥቷል፡፡ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቆ ስራ ማግኘት የማይታሰብበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡

ሀገራችን የምትገኝበት ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ምስቅልቅል፣ የፖለቲካው ነጸብራቅ ነው፡፡ የዚህ ምስቅልቅል አንዱ ማሳያ ከፍተኛ የሆነ የዜጎች ስደት ነው፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት ጋሎፕ ኢንተርናሽናል ባደረገው ጥናት ኢትዮጵያ ዜጎቿ ለኑሮ የማይመርጧት ሀገር እንደሆነች ተዘግቧል፡፡ ጥናቱ እንዳመላከተው እድሉን ካገኙ፣ 46 በመቶ በላይ ኢትዮጵያዊያን ወደ ውጭ የመውጣት ፍላጎቱ አላቸው፡፡

በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከሀገራቸው ውጭ በስደት የመከራን ሕይወት ለመግፋት ተገደዋል፡፡ ዜጎች ባገራቸው ሰርቶ የመኖር ዕድሉን ማግኘት ባልቻሉበት ሀገር፣ ስደትን መምረጣቸው የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡ እጅግ አሳሳቢው ጉዳይ፣ መንግስት በውጭ የሚገኙ ዜጎችን መብትና ጥቅም ማስከበር አለመቻሉ ነው፡፡

በተለይ ወደ ዓረብ ሀገራት የሚሄዱ እህቶቻችን የሚደርስባቸው ግፍና ውርደት፣ ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ አንገት የሚያስደፋ ሆኗል፡፡ በነዚህ ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሰሩበትን ደመወዝ ይከለከላሉ፤ ይደበደባሉ፤ ይደፈራሉ፤ በግፍ ይታሰራሉ፤ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ይገደላሉ፡፡ ይህ ዓይነት የዜጎች መብት ጥሰት ከማሻሻል ይልቅ፣ እየተባባሰ መጥቷል፡፡

የሶስት ልጆች እናት የሆነችው ዓለም ደቻሳ ላይ በቅርቡ በሊባኖስ የደረሰባት ግፍ ተመሳሳይ ነው፡፡ በሀገሯ ቆንጽላ ጽህፈት ቤት ፊት ለፊት፣ ዓለም ደቻሳን እንደ ውሻ እየጎተቱ ወደ መኪና ለማስገባት የሚደረገው ትግል ልብ የሚሰብር ነው፡፡ በቆንስላው ጽህፈት ቤት ውስጥ የሚገኙት ሰራተኞች፣ የዜጎችን መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ በላይ ምን ስራ አላቸው? የቆንስላው ኃላፊ በቢሮዋቸው ፊለፊት ይህ ሁሉ ጉድ ሲፈጸም መፍትሄ ለመፈለግ ያለመቻላቸው ነው ትንግርቱ፡፡

ስራ አሰፈጻሚውን ይቆጣጠራል የሚባለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ እንዲህ ያለ የስራ አስፈጻሚውን መጋደል ሲኖር ለምን ብሎ መጠየቅ የማይችል ነው፡፡ ብዙ ሺህ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩበት ሀገር፣ በቂ የሰው ኃይል ለምን አልተመደበም ብሎ ሊጠይቅ የሚችል አይደለም፡፡ ተጠያቂነት የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም፡፡ የኢትዮጵዊያዉያን ሕይወት የሚቆረቆርለት የሌለው መስሏል፡፡

በሱዳን፣ በሱማልያ፣ በሳውዲ ዓረብያ፣ በኬንያ፣ በየመን፣ በሊባኖስና በሌሎችም ሀገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ኑሮ ልብ የሚሰብር ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደታየው መንግስት በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንን ጥቅምና መብት ማስከበር አልቻለም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በቅርቡ ከ45 ሺህ በላይ ኢትዮጵዉያን የቤት ሠራተኞችን ወደ ሳውዲ ለመላክ ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ተሰምቷል፡፡ የነዚህን ዜጎች እጣ ፋንታ ከቀድሞዎቹ በምን ሊለይ እንደሚችል መተማመኛ የለም፡፡ መብታቸውንና ጥቅማቸውን ከማስጠበቅ አንጻር በሳውዲ የሚገኘው ሚሲዮን አቅም ዝቅተኛ ነው፤ የመንግስት ተነሳሽነትም ዝቅተኛ ነው፡፡

በየሀገሩ "ዲፕሎማት" ተብለዉ የተቀመጡ በችሎታ ሳይሆን በታማኝ ካድሬነታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ የዲፕሎማሲ ስራ ከፍተኛ እውቀትና ክህሎት የሚጠይቅ ስራ መሆኑ ተረስቶ፣ ጥብቅ በሆነ የፓርቲ ታማኝነት ላይ እንዲንጠለጠል ተደርጓል፡፡ የዜጎችን መብት ማስጠበቅ የምር ተደርጎ የሚወሰድ ስራ ሊሆን አልቻለም፡፡

በየሀገሩ የሚገኙ ቆንስላዎችና ኤምባሲዎች፣ ውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ያላቸው ተቀባይነት ዝቅተኛ መሆኑ ሊያስገርመን አይችልም፡፡ በውጭ ሀገር የሚገኙትን ሚስዮኖች ዋነኛ ስራ ዜጎችን መሰለል ሆኗል፡፡ በየሀገሩ የሚገኙ ቆንስላዎችና ኤምባሲዎች የኢህአዴግ እንጂ፣ የኢትዮጵያ አይምስሉም፡፡ በስም የኢትዮጵያ፣ በተጨባጭ የፓርቲ ናቸዉ፡፡ ኢህአዴግ በቅርቡ "የዲያስፖራ ረቂቅ ፖሊሲ" ባለው ሠነድ ላይ በግልጽ እንዳስተቀመጠው የሚሲዮኞቹ ዋንኛው ሥራ ከዜጎች ገንዘብ ማሰባሰብ እንጅ፣ ጥቅማቸውንና መብታቸውን ማስጠበቅ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ቦንድ ግዙ ብሎ መወትወት የማይሰለቸውን ያህል፣ የዲያስፖራውን የመምረጥ መብት ግን ለማክበር ፍቃደኛ አይደለም፡፡ ስለዚህ በዲያስፖራው የኢህአዴግ ተቀባይነት እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

በዓለም ደቻሳ ላይ የደረሰው ዘግናኝ ድርጊት መነሻችን ሆነ እንጂ፣ በየዓረብ ሀገሩ ያለው የኢትዮጵያውያን የባርነት ሕይወት እጅግ የሚያስቆጭ ነው፡፡ ላለፉት 20 ዓመታት በግልፅ እንደምናየው አገዛዙ የዜጎችን መብትና ጥቅም ማስከበር አልቻለም፡፡ በዓረብ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉንን መብት ለማስከበር፣ የምን ያህል ዜጎችን ሕይወት እስክንገብር መጠበቅ እንዳለብን ግልፅ አይደለም፡፡ በየሀገሩ የኢትዮጵውያን ውርደት ማቆሚያው የቱ ጋ እንደሆነም ግልፅ አይደለም፡፡

ስለሆነም በሀገር ቤትም በውጭም የምንገኝ ዜጎች ሁሉ ኃላፊነት ልንወስድ ይገባል፡፡ የአገዛዙን ድጋፍ ሳንጠብቅ ከዚህ አሳፋሪ ውርደት ለመውጣት ኢትዮጵዉያን ተባብረን መቆም ይኖርብናል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል፡፡ አንድነት/መድረክ በውጭ የሚገኙ ዜጎቻችንን መብት ለማስከበር ኃላፊነቱን መወጣት ይገባዋል፡፡ ዜጎችን በማስተባበር በአዲስ አበባ በሚገኙ ኤምባሲዎች ፊት ለፊት ሠላማዊ ሠልፍ በማድረግ መታገል አንዱ መንገድ ነው፡፡ በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን፣ የዜጎቻችንን መብት ለማስከበር የተቀናጀ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ የሊባኖስ ኤምባሲ ፊት ለፊት የተደረገው የኢትዮጵያዉያን ተቃውሞ የሚያበረታታ ነው፡፡

ይህን ሀገራዊ ውርደት በዘላቂነት መፍታት የሚቻለው የበለፀገችና ፍትህ የሰፈነባትን ኢትዮጵያን መፍጠር ሲቻል ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ግብ መዳረሻ እንቅፋት የሆነውን የኢህአዴግ ግትር አገዛዝ በሰላማዊ ትግል በብቃት መታገል ሲቻል ብቻ ነው፤ በውስጥም በውጭም ያሉ ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች ሀገራችን ካለችበት ውርደት ለማውጣት እጅ ለእጅ ተያይዘን መነሳት ስንችል ነው፡፡

በሀገራችን ተዋርድን፣ በውጭ ሀገር ተዋርደን መኖር እንዲበቃን በጋራ እንነሳ!!

*ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!*

# ነፃ አስተየት

## ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ ጠቋሚ የመፍተሔ ሃሳቦች፡፡

ከአብረሃም በቀለ ገለታ
(በቤልጂየም ጋንት ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ)

በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ቁጥር 31 ላይ "በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ተረጋግጦ የምናየው መቼ ነው?" የሚል ርዕስ ያለው ፅሁፍ ማቅረቤ ይታወሳል፡፡ በወቅቱ ላነሳኋቸው ችግሮች በቀጣይ አጠር ያሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ይዤ እንደምቀርብ ቃል በገባሁት መሠረት እነሆ ብቅ አልኩ፡፡

ዜጐች በዘለቄታዊነት በቂ መተዳደሪያ ገቢ ሊኖራቸው የሚችለው ጥሪት ሲቋጥሩ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የሚገጥማቸውን ችግር ሊቋቋሙበት የሚያስችላቸው በቂ ጥሪት እንዲያፈሩ እገዛ ማድረግ ላይ ነው፡፡ በዚህ በኩል መንግሥት እጅግ ከፍተኛ ስራ ይጠብቀዋል፡፡

የተለያዩ መርሃ ግብሮች ለምሳሌ የማማከር፣የትምህርት፣የሥራ ሥልጠና፣የቁጠባ፣ሥራ ፈጣሪነት እና የመሳሰሉት መዘርጋትና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እድሉ ለሁሉም እንዲደርስ ማድረግ ግድ የሚል ጉዳይ ነው፡፡

ዜጎች በቂ ጥሪት እንዲያፈሩ ከማገዝ ጎን ለጎን በድርጅት፣በማህበረሰብና በፖሊሲ ደረጃ እገዛውን ሊያጠናክሩ እና ሊያጎለብቱ የሚያስችሉ ለውጦችን ማምጣት ድህነትን ለመቀነስና ለማጥፋት ያስችላል፡፡

የገበሬውን የመሬት ባለቤትነት መብት ማረጋገጥ እና ፍትሃዊ የመሬት ክፍፍል ማድረግ ሌላው ትልቁ መፍትሄ ነው፡፡

በጋራ የሚተዳደር መሬትና ሐብት ለምሳሌ እንደ ግጦሽ መሬት ያለ የሚተዳደርበትን ባህላዊ ደንብ ህጋዊ እንዲሆን ማድረግና በሂደቱም ተጠቃሚው እንዲሳተፍ ማድረግ እና የመሬቱን ታሪካዊ፣ማህበራዊና ብሄረሰባዊ ስርዓቱን በደንቡ ውስጥ እንዲንፀባረቅ ማድረግ

የመሬት አስተዳደር አገልግሎት መስጫዎችን የግል ኩባንያዎች እንዲያስተዳድሯቸው መስጠት አስተዳደሩ ከፖለቲካ ግፊት ነፃ በሆነ መንገድ አገልግሎቱን ለመስጠት ያስችለዋል፡፡ ሙያዊም ያደርገዋል፡፡

የመሬት ኪራይና ሽያጭ እንዲኖር መፍቀድ መሬትን እንደመያዣ በመጠቀም የፋይናንስና ሌሎች አጋዥ አገልግሎቶችን ገበሬው እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ ይህ ደግሞ ተጨማሪ ሀብት የመፍጠሪያ መንገድ በመሆኑ ውጤቱ በሀገር ደረጃም ይገለጣል፡፡

መሬት በቅድሚያ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች በተጠናና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያመጣ መልኩ በማከራየት በሜካናይዝድ እርሻ እንዲለማ ማድረግ ለዜጎች በርካታ የሥራ እድል ከመፍጠሩ ባሻገር ለአገር ውስጥ ገበያ ፍጆታ የሚውል በቂ የእህል ክምችት ለመያዝና የውጪ ምንዛሪ ለማምጣት ያግዛል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ የዘመናት ችግር የነበረውን የወጪ ምንዛሬ ችግር የመፍቻ አንዱ መንገድ የሚሆን ነው፡፡

የገበሬውን የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጥና በቂ ጥሪት እንዲያፈራ እገዛ ማድረግ መሬቱን ለመንከባከብና ለምነቱን ለመመለስ መነሳሳትን ይፈጥርለታል፡፡ የደን ጭፍጨፋንም ለመታደግ የተሻለ የኃይል ምንጭ አማራጭ ማጥናትና ተግባራዊ ማድረግ የተራቆተውንም መሬት በሴፍቲኔት ገበሬውን በማደራጀት የደን መልሶ ማልበስ ሥራ እንዲሰራ ማድረግ፡፡

በገጠር ልማቱ ጎን ለጎን ለከተሞች እድገት ትኩረት መስጠት፤ የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ተቋማት ለግሉ ዘርፍ ማሸጋገር፤ጤነኛና ተፎካካሪ የገበያ ስርዓት በመዘርጋት ገበያው እራሱን የሚመራበትንና የሚስተካከልበትን ሁኔታ መፍጠር፤የገበያ ውሎችን ማስፈፀሚያ ደንቦችን እና የውለታ ደንቦችን ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ ለተግባራዊነቱም የተቋማቱን አቅም ግምባታ ማድረግ ነው፡፡

የፋይናንስ ስርዓቱ ላይ ለውጥ ማድረግና የፋይናንስ መሰረተ ልማት ተቋማትን ማስፋፋት የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለገበሬው የመሬት ባለቤትነቱን ማረጋገጥና መሬቱን መለወጥና መሸጥ እንዲችል ማድረግ መሬቱን መያዣ በማድረግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ የፋይናንስ ተቋማቱ አገልግሎት ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ አሁን የሚታየውን በደጋፊነትና በአባልነት የሚታደል

ፖለቲካ

# ጊዮርጊስ ብሔራዊ ቡድን ቢወክል ምን ችግር አለው?



ግርማ ሠይፉ ማሩ

በሣምንት አንድ የጋዜጣ ግማሽ መጣጥፍ ለማቅረብ የኔ ቢጤው ባተሌ የጊዜ ካልሆነ በስተቀር የመነሻ ሃሳብ ድርቀት ያለ አይመስለኝም፡፡ ጊዜ የሚባለውም ቢሆን ለሰበብ ያገለግል ካልሆነ ብዙም ችግር አይደለም፡፡ አንዳ አንድ ቦታ የምናባክነውን ጊዜ ሳስብው ማለቴ ነው፡፡ አንዱ አሣብ ጫሪ መቼም ኢቴቪ ነው፡፡ በዚህ ሳምንት ጉደኛው ኢቴቪ ያቀረበልን ቐሺ ገብሩ (ታጋይ ሙሉ) ታሪክ እያጣጣምን እያለ በዜና እወጃው ደግሞ የፕሬዘዳንቱን አለማረፍ (በህይወት መኖር ማለትም ነብስ ተስጋቸው ያለመለያየቱን) እንዲሁም የአወልያ ትምህርት ቤት መደበኛ ትምህርት መቀጠሉን፣ በሌላ ወገን ደግሞ በስልጤ ዞን ተከሰቶ የነበረው ግጭት በሀገር ሽማግሌ በባህላዊ ወግ በእርቅ መጠናቀቁን እያከታተለ ሲነግር ከረመ፡፡ እና ምን ይሁን? ምን ችግር አለው? ችግሩን አስረዳለሁ፡፡

ባለፈው ሳምንት በጣም ጠቃሚ ናቸው ብዬ የማምንባቸው ሁለት ስብሰባዎች ከሁሉም የሀገሪቱ ክልል ከመጡ የገዢው ፓርቲ አባላት ጋር ተቀምጬ ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከተሳታፊዎቹ ጋር በመድረከም፣ በግልም በዕረፍት ወቅት በነበረኝ ውይይት ብዙ ግንዛቤዎችን ከማዳበሬ በተጨማሪ አንዳንዶቹ እጅግ አሳሳቢ እንደሆኑ መገንዘብ ችያለሁ፡፡ ለዛሬ አንድ ሁለቱን ባጋራችሁ ወደድኩ አንዱ ከሚዲያ ጋር ተያይዞ ያለው የኢቴቪ ስለሆነ አብሬ አነሳዋለሁ፡፡ በዚሁ አጋጣሚ እጅግ አበረታች ሆኖ ያገኘሁት ምስጋና የሚገባው ደግሞ የበጀት ቀመር በባለሞያ ለማዘጋጀት የሚደረገው ጥረትና ተያይዞ ያለው የፌዴራሊዝም ፈተናዎችን ነው፡፡ ፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለዚህ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ አሳሳቢ ወዳልኳቸው ሁለት ነጥቦች ልውሰዳችሁ፤

1) የፓርቲና መንግስት ተግባራት መቀላቀል

«ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲጠናከሩ መንግስት ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል» ሲባል ኢህአዴግ መድረክን መደገፍ አለበት ብለው የሚረዱ ብዙ የኢህአዴግ አባላት መኖራቸውን መረዳት ችያለሁ፡፡ የመንግስት ተቋማት ለአገልግሎት ሰንዴድ ሰቃያችንም የሚበዛው ከፍተኛ ውሳኔ የሚሰጡት ሃላፊ ተብዬዎች በዚህ ወጥመድ ውስጥ ሰለሚገኙ ነው፡፡ የብዙሃን ፓርቲ መኖር ለዚህች ሀገር አማራጭ ብቻ ሳይሆን የእልውና ጉዳይ ነው የሚባልለት አጀንዳ ነው፡፡ የብዙሃን ፓርቲ ማበብ ከሚያገባቸው አካላት ዋነኛው መንግስት ነው፡፡ ኢህአዴግ አይደለም፡ ፡ በእግር ኳስ ምሳሌ ላሰረዳ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን እንዲጠናከር የፕርሚየር ሊግ ተወዳዳሪዎች መጠናከር አለባቸው ሲባል ብዙ ጊዜ ዋንጫ የሚበላው ጊዮርጊስ ሰለሆነ ጊዮርጊስ ቡናን ወይም ጉናን መደገፍ አለበት ማለት አይደለም፡፡ ጊዮርጊስ ቡናን የመደገፍ ሃላፊነት እንደሌለበት ሁሉ ኢህአዴግ መድረከን የመደገፍ ሃላፊነት የለበትም፡፡ መድረክም ይህንን አይጠብቅም፡ ፡ ለብሔራዊ ቡድን በጋራ መጫወት ግን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምንጠይቀው የብሔራዊ ቡድኑ ምሳሌ ለሚሆነው ምክር ቤት ሁላችንም እንድናዋጣ ግዴታችንንም በጋራ እንድንወጣ ይገባል መንግስትም ሊያሰብበት ይገባል ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ አንድ ቡድን ብሔራዊ ቡድኑን እንደወከለ ነው የሚቆጠረው፡፡ ምክር ቤቱ በአንድ ፓርቲ መሙላቱ ችግር አይደለም የሚሉ የኢህአዴግ አባላት ይህ ምሳሌ እንደሚጠቅማቸው እገምታለሁ፡፡

የመንግስት ሚዲያ አጠቃቀምን ፍትሃዊ ይሁን ብለን ብሮድካስት ባለስልጣን ስንሄድ፣ የስብሰባ ፈቃድ ለመጠየቅ (ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ጭምር) ወይም ለቢሮ መገንቢያ የሚሆን ቦታ ይሰጠን ብለን አዲስ አበባ መስተዳደር ስንሄድ፣ ለቢሮ የሚሆን ቤት ይሰጠን ብለን ኪራይ ቤቶች ሰንመላለስ፤ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ተቋም ይሁን፤.. ወዘተ ስንል ኢህአዴግ ጋ ደጅ እየጠናን ሳይሆን የመንግስት ተቋም እየመጣን እንደሆነ ልትገነዘቡልን ይገባል፡፡ ከኢህአዴግ አባላት ከሚሰባሰብ መዋጮ ቤሳ ቢስቲን እየጠየቅን አይደለም፡፡

2) በፈለጉት ሚዛን መጠቀም (ደብል ስታንዳርድ)

የ2002 ምርጫ ያመጣው ውጤት የህዝብ ውሳኔ ስለሆነ ተቀበሉ እንባላለን፡ ፡ በተለይ እኔ ሰለምርጫው ትክክለኛ ያለመሆን መናገር የምችል አይመስላቸውም፡ ፡ ሁሌም እንደምለው የቤቱ ንብረት ሁሉ ተሰርቆበት አንዱን (ማንኪያ ሊሆን ይችላል) ደርሶ ያሳጣለ ቤቱ ሌባ አልገባም እንዲል መጠበቅ ነው፡፡ ከምርጫ ጋር የተያያዘውን የህዝብ ውሳኔ ያለምንም ጥያቄ ተቀበሉ የሚል አመለካከት የሚያራምዱ ኢህአዴግ አባላት ሌሎች አማራጭ የሚሹ ጉዳዮች ሲነሱ ህዝቡ ምርጫውን ይፋ ሲያደርግ የተለያዩ ተቀጥላ በመስጠት ህዝቡ ተሳስቶ ነው የልማታዊ መንግስት ጥበቃ ያሰፈልገዋል እንባላለን፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የተደረገ ነው እንባላለን፡፡ እንደ እኔ እንደ እኔ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የተሳሳተም ቢሆን የህዝብን ምርጫ ማክበር ነው ህዝባዊነት፡፡

ሕዝቡ እንዳይሳሳት ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል ከሚሉት አንዱ ሚዲያ ነው፡፡ ማሳያውም በከተማችን በከፍተኛ ደረጃ ሽያጭ ያለቸው ጋዜጦች ልማታዊ ያልሆኑት ናቸው የሚል መደምደሚያ አላቸው፡፡ መንግስት ሆደ ሰፊ ሆኖ ነው እንጂ መዘጋት እንዳለባቸው ይታመናል ምክንያቱም ህዝቡ እነዚህን ጋዜጦች አይረቡም ብሎ ከገበያ ሊያሰወጣቸው የሚችል ግንዛቤም ችሎታም የለውም፡፡ እንዲያውም እንዲሰፋፉ ያደርጋል፡፡ ሰለዚህ የመንግስት ሞግዚትነት/ ጥበቃ የግድ ነው፡፡ ከነዚህ ጥበቃዎች አንዱ የግሉ ሚዲያ ሞኖፖሊ እንዳይኖር ጋዜጣ እያተሙ መፅሔት ማሰብ አይቻልም፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል፡፡

በመግቢያዬ ላይ ያነሳሁት የሚዲያ ጉዳይ ለመዝጊያ እንጠቀምበት፡፡ ሞኖፖሊ የተፈቀደለት የቴሌቪዥን ፕሮግራሙ በቅርቡ ቐሸ ገብሩ የተሰኘ ዘጋቢ ፊልም አቅርቦልናል፡፡ ቐሸ ገብሩ ሰንመለከት በእውነት ወዲያው ትዝ የሚለን አሞራው እንደሆነ ጥርጥር የለኝም፡፡ በፕሮፓጋንዳ ተሸፍኖ የተላለፈው መልዕክት እነዚህ ታጋዮች ለተሰለፉለት ዓላማ ቁርጠኞች እንደ ነበሩ ነው፡፡ ለዚህ አቋም ክብር አለኝ፡ ፡ አብሮት ላለው የፕሮፓጋንዳ ቁልል ያለኝ ንቀት ሊሸፍነው የማይችል፡፡ ቢሆንም ጥያቄ አለኝ፤ ኢህአዴግ በወቅቱ ሲማርካቸው የነበሩትን ወታደሮች (የደርግ ሰራዊት ማለት ለኔ ነውር ሰለሚሆንብኝ አልጠቀምበትም - የኢትዮጵያ ሰራዊት እንደነበሩ ሰለማምን) መጠይቅ ሲያደርግላቸው ለቆሙለት ዓላማ (ሀገር ያለማስገንጠል) ቁርጥ አቋም የነበራቸው አልነበሩም ወይ? ህይወታቸውን ለመስጠት ሳንጃ የተሞሻለቁት የመንግስቱ ኃይለ ማሪያምን ሥልጣን ለማሰጠበቅ ነበር? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሆነው የተቀዳ ፊልምና ድምፅ ካለ ለታሪክ ተመራማሪዎች ይፋ ማድረግ ነው፡፡ የአሞራውና የቐሸ ገብሩን ፊልም ሳያጠፉ በክምችት ክፍል ላኖሩልን ሁሉ ምሰጋናዬን እያቀረብኩ፤ እነዚህ ፊልሞች ከዚህ ሌላ ሌሎች ጉዳዮችን የያዙ ሰለሆነ በዚህ ዙሪያ ሚዛናዊ የሆነ ጥናት ለሚያደርጉ ባለሞያዎች ክፍት እንዲሆን እንጠይቃለን፡፡ እንደዚሁም ኢህአደግ በትግል ወቅት የቀረፃቸውን ፊልሞችና ሌሎች ዶክሜንቶች ለሚመለከተው አካል እንዲያሰረክብ እንጠይቃለን፡፡

ጉደኛው ኢቴቪ ሌላው ያቀረበው የፕሬዝዳንቱን ጤንነት የሚመለከተው ነው፡፡ አንድ የግል ሚዲያ ፕሬዝዳንቱ መታመማቸውን አስመልክቶ ሲዘግብ የፕሬዘዳንቱ ፅ/ቤት ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ ሆስፒታልም እንዳልገቡ ማስተባበያ ሰጥቶ ነበር፡፡ ማህበራዊ ሚዲያዎች የፕሬዝዳንቱን መሞት ሲዘግቡ ኢቴቪ ብድግ ብሎ ለህክምና ሳውዲ እንደሚገኙ እና ጤናቸውም በጥሩ ሁኔታ እንደሚገኝ የፕሬዘዳንቱን ፅ/ቤት ዋቢ በማድረግ ገልፆልናል፡፡ የመሄዳቸው ዜና ለምን አልተነገረንም ወይስ በተደጋጋሚ ሰለሚሄዱ ዜና መሆኑ ቀርቶዋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢቴቪ በአወልያ የሙስሊም ትምህርት ቤት ትምህርት መቋረጡን ሳይነግረን መጀመሩን፤ በሰልጤ ዞን ግጭት መኖሩን ሳይነግረን ሰምምነት መፈጠሩን ዘግቦዋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሰንመለከት ከጀርባቸው መንግሰት ምን ሚና እየተጫወተ ነው ለምን ከህዝብ ዕይታ ውጭ እንዲሆን ይፈልጋል? እንድንል ያሰገድደናል፡፡ የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ሞኖፖሊ የግል ሚዲያ እንዳያድግ የሚፈለግበት ምክንያትም ፖለቲካዊ እንደሆነ ይገባናል፡፡ ማህበራዊ ሚዲያዎች ኢቴቪን ማመን ዘግቶ ነው ብለውናል፡፡

በነገራችን ላይ የቐሺ ገብሩ ዘጋቢ ፊልም ስፖንሰር ያደረጉ ክልሎች የክልላቸው ሕዝብ ለሚጠይቃቸው ማህበራዊ አገልግሎት በጀት ዕጥረት ለመናገር ይችላሉ ወይ? እንደዚህ ያለ የመንግስት በጀት አጠቃቀም ለመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት የክልል ምክር ቤቶች እንዴት ያዩታል?

# የአቶ መለስ እዉነተኛ . . .

ከገፅ 7 የዞረ

ከላይ ያነሳናቸዉ የአቶ መለስ እዉነተኛ መሠረቶች ከግል ጥቅም ይልቅ ዘላቂ ጥቅማቸዉ ከሕዝብ ጋር መሆኑን ተረድተዉ ቢያንስ ወሳኝ ቀን ሲመጣ ከሕዝብ ጋር፣ ጊዜዉ ሳይመሽ፣ ይሰለፋሉ የተባለዉ ከዚህም እዉነታ አንፃር ጭምር ነዉ፡፡

የአቶ መለስ ሌላዉ የመንግሥት ሥልጣን መሠረት ተብሎ በበለጠ ጎሹ ወ/ሚካኤል ከላይ በተጠቀሰዉ ጽሑፍ የተመለከተዉ "የአሜሪካ እና የሌሎች ምዕራባዉያን መንግሥታት ዕርዳታና ድጋፍ" እንደሆነ ተገልጾአል፡፡

እነዚህ መንግሥታት የሀገራቸዉን ጥቅም ለማስከበር የተወከሉ በመሆኑ፣ በሥልጣን ላይ ያለዉ ማን ይሁን ማን፣ እንደ ቀዝቃዛዉ ጦርነት ወቅት፣ ዛሬ እምብዛም አይጨነቁም፡፡ የእነሱ ዋና መለኪያ፣ ጠንካራ ፓርቲ ወይም በሥሩ ሕዝብን ማሰለፍ የሚችል ግለሰብ ማን ነዉ? ሕዝቡስ ምን ያህል ለመብቱ ተቆርቋሪ ነዉ? የሚሉ ናቸዉ፡፡

ሕዝባዊ ተቃዉሞ ሲያይል ወይም አንድ ራሱን ያስመሰከረ ወይም ሊያስመሰክር ይችላል ብለዉ የሚያምኑት ኃይል ሲኖር፣ ለገዢዉ ፓርቲ እና መንግሥት የሚሰጡት ዕርዳታ እና ድጋፍ ከመቅጽበት ያቋዋርጣሉ ወይም ያቀዘቅዛሉ ወይም ከአዲሱ ኃይል ጋር ዉስጥ ለዉስጥ መግባባት ይፈጥራሉ ወይም ሁሉንም ያደራጋሉ፡፡

የምዕራብ ሀገሮች በሰሜን አፍሪካ በፈነዳዉ አብዮት፣ ለምሳሌ በግብፅ እና በሊቢያ፣ የሕዝብ ኃይል እየጠነከረ መምጣቱን በተመለከቱ ጊዜ፣ በሀገራቸዉ መመሪያ መሠረት፣ ዘለቄታዊ ጥቅማቸዉ ከሕዝብ ጋር በመሆኑ፣ መንግሥትም ተለዋዋጭ መሆኑን ያዉቃሉና፣ ቶሎ ከሕዝብ ጎራ ተሰልፈዉ ለሕዝብ ሰብአዊ መብት መሟገትን መርጠዉ፣ ገዢዉን ፓርቲ እና መንግሥት መቃወም እንደተያያዙ የምናስታዉሰዉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ፡ ፡ ስለዚህ ወሳኝ ሰዓት ሲመጣ የኢትዮጵያም ሁኔታ ከዚህ የተለየ እንደማይሆን በእርግጠኝነት መናገር የቻላል፡፡

ማጠቃለያ

የአቶ መለስ ማደናገሪያ ቃላቶች እንዳሉ ሆነዉ፣ የእሳቸዉ እዉነተኛ የሥልጣን መሠረት የአንድ ብሔረሰብ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቭል መሥሪያ ቤቶች ባለሟሎች እና ባለሥልጣኖች አይደሉም፡፡ እነዚህ ወሳኝ ቀን ሲመጣ፣ እንደማንኛዉም ሰዉ ሁሉ፣ በዘላቂ ራዕያቸዉ እና ጥቅማቸዉ ተመርተዉ፣ ከሕዝብ ጎን የሚቆሙ ናቸዉ፡፡

የምዕራቡ ዓለም ዕርዳታ እና ድጋፍም እንዲሁ ጊዜያዊ ነዉ፡፡ ወሳኝ ሰዓት ሲመጣ እነዚህ ለጋሽ መንግሥታት ዕርዳታቸዉን እና ድጋፋቸዉን አቀዝቅዘዉ ከሕዝብ ጎራ እንደሚቀላቀሉ በእየ ሀገሩ የታየዉ ልምድ ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

የአቶ መለስ እዉነተኛ የሥልጣን መሠረቶች በጊዜያዊ የግል ጥቅም ላይ ያተኮሩ፣ በአራቱ ፓርቲዎች ካድሬዎች እና ባለሥልጣኖች እየገበረ ያለዉ የኃይል አገዛዝ፣ የሚነዛዉ ፕሮፖጋንዳ እና የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎቻቸዉ የሆኑት፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አገልግሎት የተነጠቁት፣ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ድርጅቶች ናቸዉ፡፡

ሰሞኑን የ116ኛዉን የአድዋን የነፃነት በዓል አክብረናል፡፡ በ21ኛዉ ክፍለ ዘመን የግል ነፃነት ሳይከበር የሀገር እና የቡድን ነፃነት ዘለቄታ እንደሌለዉ በማጤን፣ ኤርትራን ያስታዉሰዋል፣ እለቱ በግል እና በጋራ ሆነን የግል ነፃነት ለማስከበር ለሕዝባችን ቃል የገባንበት እንደሆነም አስባለሁ!

እቴጌ ጣይቱ ነፃነት በመስዋዕትነት እንጂ በልመና እንደማይገኝ ለጣሊያን መልዕክተኛ አረጋግጠዉ ከባላቸዉ፣ ከአፄ ምኒልክ፣ ጎን በአድዋ ጦርነት እንደተሰለፉ ሁላችንም የምናስታዉሰዉ፣ ከትዉልድ ትዉልድ የተላለፈልን አኩሪ ተግባር ነዉ፡፡

ዛሬም ሴት እህቶቻችን ከወንድሞቻቸዉ፣ በተለይ የወቅቱ ገፈት ቀማሽ፣ ግን ወደፊት ኢትዮጵያን ተረካቢ ከሆነዉ፣ ከወጣቱ ጎን በቆራጥነት ተሰልፈዉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ከፍተኛ መስዋዕት በመክፈል የታገለለትን ሰብአዊ መብት፣ ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት፣ ለአንዴ እና ለዘለቄታዉ፣ ዳግም ወደ ኋላ ላይመለስ፣ ያረጋግጣሉ የሚል ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

---

አገልግሎት ያስቀረዋል፡፡ ይህ ደግሞ የፍታሃዊነትና የመልካም አስተዳደር ሌላኛው ገፅ መሆኑም ነው፡ ፡የምርጥ ዘር ማዳበሪያ እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስርጭት በፓርቲ አባለነትና በደጋፊነት ማደሉን አቁሞ ለሁሉም አርሶ አደር በእኩልነት እንዲደርስ ማድረግ፡ ፡ በኢህአዴግ ኩባንያዎች በሞኖፖል የተያዘውን የማዳበሪያ ገበያ ለማከፋፈል የሚችል ማንኛውንም አቅራቢ እንዲያከፋፍልና ተፎካካሪ ገበያ እንዲኖር ማድረግ፡፡ከሦስት ሺህ ዓመት በፊት ጀምሮ ጥቅም ላይ ሲውል የነበረውን ኋላ ቀር የአስተራረስ ዘዴ በተሻለ መንገድ እንዲለውጥ አስፈላጊውን ጥናት ማረግና መተግበር፡፡ አነስተኛ መስኖን በመዘርጋት ከዘወትር የዝናብ ጥገኝነት ገበሬው እንዲላቀቅ ማድረግና የፖለቲካ ሥራ በመስራት የተጠመዱትን የእርሻ ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሙያዊ አገዛቸውን ለገበሬው እንዲሰጡ ነፃ ማድረግ፡፡

የጤና ሽፋኑን ለማስፋት የጤና ባጀት ላይ መስተካከያ ማድረግና በይበልጥ በመከላከል ላይ ያተኮረ ማድረግ፡፡ ለዚህም ተፈፃሚነት እናቶችን ወይንም ህፃናት ተንከባካቢዎችን ስለምግብ አዘገጃጀት ስለንፅህና እና ህፃናት አመጋገብ ተገቢውን ትምህርት መስጠት፡፡ የሥነ ምግባር ትምህርትም ከታች ጀምሮ በሥርዓተ ትምህርቱ እንዲካተት ማድረግ፡ ፡ የንፁህ ውኃ እና ሳኒቴሽን ሽፋኑን ከፖለቲካ ፍጆታ በማላቀቅ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለማዳረስ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የተከበሩ አቶ ገብሩ ገ/ማሪያም ዑቱራ ይባላሉ፡፡ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ኦህኮ /ህብረትን/ ወክለው ለፓርላማ ተወዳድረው በመረጣቸው ለአምስት ዓመት የፓርላማ አባል ነበሩ፡፡ በፓርላማ ቆይታቸው የፓርላማው የህብረት ዋና ተጠሪ፣ የአፈጉባኤ አማካሪ ቋሚ ኮሚቴ አባል፣ የፓን አፍሪካ ፓርላማ አባልና የፓርላማው የንግድ የጉምሩክና የህዝብ ፍሰት /ኢሚግሬሽን/ ቋሚ ኮሚቴ ም/ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል፡፡ የፓርላማው የምርጫ ዘመን ሲጠናቀቅ በክብር ተሰናብተዋል፡፡ ስለ ግላቸው፣ ስለ ፓርቲያቸው፣ ስለመድረክና በእሳቸው እይታ ስለወቅቱ የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ከባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡

# የሚያስደንቀው ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ይህንን ሁሉ ተቋቁመው እዚህ መድረሳቸው ነው

➢ መቼና የት አካባቢ እንደተወለዱ? ቢገልጹልኝ፡፡

ስወለድ በነበረው አጠራር በሸዋ ጠ/ግዛት ጅባትና ሜጫ አውራጃ ደንዲ ወረዳ ልዩ ሥፍራው ሹሜ /በአሁኑ ጊዜ ቦሎጠ አዋሽ ቀ/ገ/ማ/ በሚባል አካባቢ በ1943 ዓ.ም ተወለድኩኝ፡፡

➢ የት የት ተማሩ?

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤትና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በጊንጪና በአምቦ ተምሬ አጠናቀኩኝ፡፡ ኮተቤ በሚገኘው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መምህራን ማሰልጠኛ እንስቲቲዩት ገብቼ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መምህርነት በዲፕሎማ ተመረኩኝ፡፡ እዚያው መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተመልሼ ገብቼ ለሁለተኛ ደረጃ በመምህርነት በዲፕሎማ ተመርቄአለሁ፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪ /BSC/ አግኝቼአለሁ፡፡

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በህዝብና ልማት አስተዳደር ሁለተኛ ዲግሪዬን /ማስተርሴን/ አግኝቼአለሁ፡፡ ከየካቲት ፖለቲካ ኢንስቲቲዩት በፖለቲካ ትምህርት ዲፕሎማ ተቀብዬአለሁ፡፡ በአገር ውስጥና በውጪ አገር በርካታ አጫጭርና ረዘም ያሉ በርካታ ሥልጠናዎችንና ወርክሾፖችን ተካፍያለሁ፡፡ በተማርኩባቸው ትምህርቶች በመላው አገሪቱ በመዘዋወር አገልግዬበታለሁ፡፡ አሁን ጡረተኛ ነኝ፡፡

➢ አሁን በፖለቲካው ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ኃላፊነትዎ ምንድነው? በምን በምን እየሠሩ ነው?

የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ /ኦህኮ/ ሥራ አስፈጻሚና የውጪ ግንኙነት ኃላፊ፣ በስድስት ሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተቋቋመው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ /መድረክ/ ሥራ አስፈጻሚና የውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባል ሆኜ እያገለገልኩ ነው፡፡

➢ በተቃዋሚ ፓርቲ መቼ ነው የተደራጁት?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኮንግረስ /ኦብኮ/ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከፓርቲው ጀርባ ነበርኩኝ፡፡ ምርጫ 97 ላይ ፊት ለፊት መውጣት እንዳለብኝ ታምኖበት በግልጽ አባልነቴን አሳውቄ ለምርጫው ቀረብኩ፡፡ በትውልድ ሥፍራዬ ተወዳድሬ ተመረጥኩኝ፡፡ እስካአሁን በትግሉ ቀጥያለሁ፡፡

➢ እርስዎ ወደ ተቃውሞ ትግል ሲገቡና ዛሬን ሲያነፃጽሩት ምን ይሰማዎታል?

ፓርቲው ሲቋቋም መጋቢት 15 ቀን በ1988 ዓ.ም ወይም በቀጥታ ፊት ለፊት የወጣሁበትን ምርጫ 97 አሁን ካለንበት ሁኔታ ጋር ስናነጻጽረው ምንም አይገናኝም፡፡ ምርጫ 97 የዴሞክራሲ ጮራ የፈነጠቀበት ነው፡፡ ህዝብ አማራጭ እንዲሰማ የፈለገውን እንዲመርጥ የተፈቀደበት ወቅት ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ የገዢውን ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ብቻ እንዲሰማ የተገደደበት፣ ከገዢው ፓርቲና ከአጋሮቹ ውጪ ለሀቀኛ ተቃዋሚዎች መንገዶች ሁሉ የጠበበት ወይም የፖለቲካ ምህዳሩ እጅግ የጠበበት የኢህአዴግ ካድሬና ደህንነት በሐቀኛ ተቃዋሚዎች ላይ የጥቃት ዘመቻ የጀመሩበት ወቅት ስለሆነ ሲፊ ልዩነት አለ፡፡

➢ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ሲባል መገለጫው ምንድነው?

ከዚህ ቀደም በፈለግን ጊዜ በፈለግንበት ቦታ አባሎቻችንን፣ ደጋፊዎቻችንን ሰብስበን እናወያያለን፡፡ ዓላማችንና ፕሮግራማችንን እናስታዋውቃለን፡፡ አማራጫችንን ለህዝብ እናቀርብ ነበር፡፡ ዛሬ ግን አይቻልም፡፡ ህዝብ እንድንሰበስብ አይፈቀድልንም፡፡ የስብሰባ አዳራሽ አግኝተን ፍቃድ ቢሰጠንም አንድ የኢህአዴግ አባል ስልክ ደውሎ በአደራሻችሁ ስብሰባ እንዳይደረግ ካለ ባለሆቴሉ ወይም የአዳራሹ ባለቤት ለኪራይ የተቀበለውን ገንዘብ መልሶ እንቢ ይላል፡፡

➢ ምህዳሩ ጠቦል የሚያሰኝ ከዚህ ያለፈ ነገር ይኖራል?

በአካባቢው ስብሰባውን ሲያስተባብሩ የነበሩ አባሎቻችን ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ይታሰራሉ፡፡ ያለ ምንም ማስረጃ ታስረው ይፈረድባቸዋል፡፡ ሲፈልጉም የተቀነባበረ የፈጠራ ክስና የፈጠራ ማስረጃ አቀናጅተው ከሰው ፕሮፓጋንዳ ሠርተው ያሰሯቸዋል፡፡ ሌሎቹ ከሥራቸው፣ ከመኖሪያቸው፣ ከንብረታቸው፣ ከቤተሰባቸው፣ እንዲፈናቀሉ ይደረጋል፡፡ እንዲሰደዱ እንሱም ሆኑ ቤተሰባቸው ለችግር እንዲጋለጡ ይደረጋል፡፡ ዛሬ ያለው የፖለቲካ ምህዳር እጅግ አስቸጋሪ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ የታየውን የዴሞክራሲ ጭላንጭል እያዳፈኑት ነው፡፡ ቀደም ሲል አባሎቻችንን ጥሪ አድርገን የምናነጋግርበት ሁኔታ ነበር፡፡ ጽ/ቤቶች በየቦታው ነበሩ፡፡ ከ97 ምርጫ በኋላ በተከናወ ነው ወከባ፣ በተከናወነው እስራትና ድብደባ፣ በተፈፀመው ግድያ፣ በተከናወነው አፈና፣ በተከናወነው ከአገር የማሳደድ እንቅስቃሴ ተግባር መላው አገሪቱ በተለይ በኦሮሚያ ጽ/ቤትቶቻችን ተዘጉ፡፡ ከኢህአዴግ ጋር እንደ ህብረት ለመደራደር ተሞክሮ አልተሳካም፡፡ የጋራ ም/ቤት ተቋቁሞ እንቅስቃሴ ተጀምሮ በኢህአዴግ ማን አለብኝነት እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ እንደ ከሸፉ ከተደረገ በኋላ ጽ/ቤቶቻችን እንደተዘጉ ቀርተዋል፡፡ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል የምንለው በተጨባጭ በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ኢህአዴግ ግን ያለ ምንም ማስረጃ ጠቧል ይላሉ እያለ ያላግጣል፡፡ አባሎቻችን ጋዜጠኞችን አነጋገራችሁ፤ ከሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጋር ተገናኛችሁ፤ ተብለው ሲታሰሩ ካድሬና ደህንነት ከመንገድ ላይ እየጐተተ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት ሲፈጽም ይታያል፡፡ እያንዳንዱ ህጋዊና የሠላማዊ ትግል እንቅስቃሴ በሽብርተኝነት የሚፈረጅበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ በዚህ ምክንያት የፓርቲያችን መዘውሮች ታስረዋል፤ ተገለዋል፤ ተሰደዋል፤ በኢኮኖሚ እንዲሽመደመዱ ተደርጓል፡፡

➢ በአንድ ወቅት ፓርቲያችሁ ተከፋፍሎ ነበር፡፡ ለመከፋፈሉ የፓርቲው የውስጥ የዴሞክራሲ ችግር ነው ይባል ነበር፡፡ እርስዎ እንዴት ያዩታል?

ፓርቲው ተከፋፍሏል ማለት አይቻልም፡፡ ፲ አለቃ ቶሎሳ ተስፋዬ በኢህአዴግ እጅ የፓርቲውን ጽ/ቤት ሠብሮ መበጥበጡ ይታወቃል፡፡ የኦብኮ መሪ ነኝ ብሎ የሠራው ሥራ አለ፡፡ ይህ ከፓርቲው ደንብና አሠራር ውጭ ነው፡፡ አንድ ፓርቲ ተከፋፈለ የሚባለው የፓርቲው የፖለቲካ ቢሮ ሁለት ቦታ ሲከፈል ነው፡፡ ቶሎሳን ተከትሎ የሄደ አንድም የፖለቲካ ቢሮ አባል የለም፡፡ ራሱና ኢህአዴግ አደራጅቶ የሰጠው የሰው



ኃይል ነው፡፡ በፍ/ቤት የፓርቲውን ደንብ ልናስከብር ሞክረን አልቻልንም፡፡ ስማችንን ኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ /ኦህኮ/ ብለን ቀይረን እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ በፓርቲያችን የውስጥ ዴሞክራሲ ችግር የለብንም፡፡

➢ በአገራችን ፖለቲካ አብዛኛው ፓርቲው ሲመሠረት ፕሬዝዳንት የሆነ 10 እና 15 አንድ ሰው ይሆናል፡፡ በእናንተም ፓርቲ ይህ ሲነሳ እንሰማለን፡፡ ትክክል ነው ብለው ያስባሉ?

ትክክል ነው ብዬ አላስብም፡፡ የፓርቲ ፕሬዝዳንትነት የግል ጉልተርስት አይደለም፡፡ መዘዋወር አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡ የበርካታ ፓርቲ አመራሮች በቋሚነት ቦታውን ይዘው መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ኃላፊነቱ ሲዘዋወር ግን በአንድ ጊዜ ብድግ አድርገህ የምትሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ ተተኪ መዘጋጀት አለበት፡፡ የፓርቲውን ዓላማና ፕሮግራም ጠንቅቆ የተረዳ ለደንቡ ተገዢ የሆነ የፓርቲውን የትግል ሥልት የተረዳ ሊኖር ይገባል፡፡ መሪዎች በራቸውን ክፍት አድርገው ተኪያቸውን ለማፍራት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እላለሁ፡፡

➢ መድረክ ከሦስት ዓመት በፊት ተመስርቶ የመጀመሪያውን መግለጫ ሲሰጥ አንድ ጥያቄ አንስቼ ነበር፡፡ በወቅቱ የመድረኩን አመራሮች አበሳጭቶ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ጥያቄው ዛሬም የሕዝብ ጥያቄ ነውና እርስዎን እንደ ግል ልጠይቆት፡፡ ከዚህ ቀደም በርካታ የፓርቲ ጥምረቶች፣ ቅንጅቶች ትብብሮች /ኢዲኃህ፣ ኢተፓድህ፣ ትድህ፣ ጋፓመ፣ ቅንጅት፣ አማራጭ ኃይሎች . . ./ ተቋቁመው ግባቸውን ሳይመቱ ፈርሰዋል፡፡ መድረክ ይህንን ያህል ተጉዞ ግንባር ለመሆንም እየተጐተተ ነው፡፡ ችግሩ ምንድነው? ያለፈው ችግር ላለመከሰት ዋስትናው ምንድነው?

መድረክ ወደ ግንባር አለመሸጋገር እንደ ግል ያሳዝነኛል፡፡ መድረክ ሲቋቋም ያለፉት ድክመቶችና ስህተቶች ሁሉ እንደ ልምድ ተወስዷል፡፡ እንደ ሥራ አስፈጻሚም እንደ መሥራችም የተጓዝንበትም መንገድ ጥንቃቄ የተሞላበት ነው፡፡ ህዝብ በሚፈልገውና በሚጠብቀው ፍጥነት ተጉዘናል ብዬ አልገምትም፡፡ መድረክን ለማቋቋም ብቻ አንድ ዓመት ተኩል ፈጅቶብናል፡፡ አሁን ወደ ግንባር ለማሸጋገር እንደዚሁ ረጂም ጊዜ ወስዶብናል፡፡ እያንዳዷን ጉዳይ እየሰነጠቅን ለማየት ሞክረናል፡፡ የጥንቃቄ ጉዞአችን ዲያስፖራውም አገር ውስጥ ያለው ኃይልም በቀላሉ ላይረዳው ይችላል፡፡

አሁንም የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያልተረዱ ፖለቲከኞች አሉ፡፡ ወይም ለመረዳት የማይፈልጉ ያሉ ይመስለኛል፡፡ በንጉሱ ዘመንና በደርግ ዘመን በነበረው የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያስቡ አሉ፡፡ በጭፍን አንዲት ኢትዮጵያ መኖር አለባት ብለው ያስባሉ፡፡ አንዲት ኢትዮጵያ በመኖሯና ባለመኖሯ ጉዳይ ድርድር የለም፡፡ መኖር አለበት፤ አዎ መኖር አለበት፤ ጥቄው ምን ዓይነት ኢትዮጵያ? ለማን የምትመች? በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች በአገሪቱ ውስጥ አሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ለሁሉም በእኩልነት የምትሆን አገር የመገንባት ጥያቄ እንዴት ይመለስ? የሚለው ግምት ውስጥ ያስገባ የጥንቃቄ ጉዞ እየተጓዝን ነው፡፡ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ጥያቄ ሳይነሳ ከዚህ በፊት የምናውቃት ኢትዮጵያ በጭፍን መኖር ትችላለች ብሎ መደምደም የአገሪቱን ፖለቲካ መሬት ባለው ሁኔታ መረዳት አለመቻል ነው፡፡ አሁን ግንባር ለመፍጠር ስምምነት ላይ ደርሰናል፡፡ የሚቀረን 6ቱም ፓርቲዎች በተናጥል የፓርቲያቸውን ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተው ማፅደቅ ነው፡፡ ሶስቱ ፓርቲዎች ቀደም ብለው አፀድቀዋል፡፡ እኛም በቅርቡ አፅድቀናል፡፡ የዘገየነው በገንዘብ ችግር ነው፡፡ ሁለቱም በቅርቡ ያፀድቃሉ ብለን እየጠበቅን ነው፡፡ እስከ አሁን የዘገዩት በገንዘብ ችግር እንጂ ሌላ ችግር አይደለም፡፡

➢ መድረክን ስታቋቁሙ 8 ነበራችሁ፡፡ ሁለቱ ወጥተዋል፡፡ ከእንግዲህ ሌላ የሚወጣ ይኖር ይሆን?

በፍጹም አይኖርም፡፡ መድረክ ሲቋቋም ምንልባትም ሰልለው እንዲወጡ ግዳጅ ተሰጥቶአቸው ተቀላቅለው የነበሩ ግዳጃቸውን ጨርሰው ሄደዋል፡፡ ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ነጥረው በመውጣት ጉዞአቸውን ቀጥለዋል፡፡ የጉዞው ፍጥነት በአቋም ጉዳይ አይደለም፤ የአገሪቱ ተጨባጭ ፖለቲካ ሁኔታ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ ጥያቄ ክፍተት በማይፈጥር መልኩ እንዴት ይፈታ የሚለው ነው፡፡

➢ የሠላማዊ ትግል ጉዞ ላይ በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ የሠላማዊ ትግል ሥልቶች በርካታ ናቸው፡፡ በአገራችን እንደ ብቸኛ መታገያ የተያዘው የተቃውሞ መግለጫ ማውጣት ብቻ ነው፡፡ በተቃውሞ መግለጫ መውጣት እርካታ አግኝቶ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ይታያል፡፡ ኢህአዴግ ከቡና ጠጡ ፕሮግራም አልፎ እያንዳንዱን ዜጋ አንድ ለአምስት የማደራጀት ደረጃ ደርሷል ይባላል? የእናንተ ትግል የት ያደርሳል ይላሉ?

ፈረንጆች “ሊወዳደር የማይችልን ነገር አታወዳድር” ይላሉ፡፡ ኢህአዴግ መላውን የአገሪቱን ሀብት ለድርጅቱ ሥልጣን ያውላል፡፡ የአገሪቱን ሀብት በጠቅላላ በድርጅቱና በመንግስት ስም ከተቆጣጠረ በኋላ ያለምንም ይሉኝታ ያሻውን ያደርጋል፡፡ በቀን መልቲ ቢሊዮን እየመነዘረ ለጥፋት ሥራው ያውላል፡፡ የተቃዋሚውን አመራርና አባል እንዲሁም የአገሪቱን ዜጎች ያሸብራል፡፡ ጠንካራ ተቃዋሚዎችንና ጋዜጠኞችን ያሳድዳል፡፡ ያስራል፤ ይደበድባል፤ ይገላል፤ በምንም ክፍተት ተቃዋሚዎች ከህዝብ ጋር እንዳይገናኙ ይሠራል፡፡ መደነቅም፣ መገረምም፣ ካስፈለገ ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ይህንን ሁሉ ተቋቁመው እዚህ መድረሳቸው ነው፡፡ ይህ ሁሉ ህገወጥ ድርጊት በህጋዊ የመንግስት ተቋማት ሽፋን እየተሰጣቸው መፈፀሙ ይልቅ የሚያሳዝን ነው፡፡

➢ አሁን በተጨባጭ አለ የሚሉት ችግር ምንድነው?

ዛሬ ህገ መንግስታዊ የሆነውን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በመጨፍለቅ አንድ አምባገነናዊ ሥርዓት እየተገነባ ነው፡፡ በየመንደሩ ህወሓት ት/ቤት መሥርቷል፡፡ ት/ቤቶች መደበኛ ትምህርታቸውን ትተው የኢህአዴግ ህዋሶች መፈልፈያ ሆነዋል፡፡ ሀቀኛ ተቃዋሚዎችን በማግለል ይጠቅሙኛል፣ ያገለግሉኛል፤ ያላቸውን ፓርቲዎች፤ የፓርቲዎች ም/ቤት አቋቁሟል፡፡ ገንዘብ፤ የአየር ሰዓት እየሰጠ የሚሰሩትን ህዝብ እያየው ነው፡፡ እራሱ ኢህአዴግ ባመነው እንኳን ብንመለከት ከኢህአዴግ ቀጥሎ ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው መድረክ ነው፡፡ ምርጫ ቦርድም ከኢህአዴግ ቀጥሎ ሁለተኛውን ከፍተኛ በጀት ማግኘት ያለበት መድረክ መሆኑ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ምርጫ ቦርድ በጀት ሲመድብ ስንት ለስንት እንደመደበ ሁላችንም ሰምተናል፡፡ ለኢህአዴግ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር ሲመድብ ለመድረክ 3ሺ ብር መድቧል፡፡ ይህ የሚመደበው ገንዘብ የአገርና የህዝብ ነው፡፡ ፍርዱን ለህዝብ መተው ነው፡፡ መድረክ አሁን ባለበት ሁኔታ ዋና ተቃዋሚ ነው፡፡ ህዝብ የዋና ተቃዋሚውን ድምጽ እንዳይሰማ ተከልክሏል፡፡

ይህ ከላይ የጠቀስኩት የኢህአዴግ ችግር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ራሳችንን ሳንመለከት አሁን ያለው ዋናው የመድረክ ችግር ከዚህ በፊት በተቃዋሚዎች ትብብር እስከዛሬ ከደረሰው ችግር በመነሳት አሁን ያለው የጥንቃቄ ብዛት ትግሉን እየጐተተው ነው፡፡ ህዝብ አሁን ባለው ሥርዓት ቀንና ለሊት ይተከዛል፡፡ ያዝናል፤ ይበሳጫል፤ ለውጥ ይፈልጋል፤ ነገር ግን አንተ ሞተህለት እሱ የድሉ ተጠቃሚ መሆን ይሻል፡፡ ከተቃዋሚ መሪዎች ከፓርቲዎች ብቻ ውጤት ይጠብቃል፡፡ ከእኔ ምን ይጠበቃል ብሎ ራሱን አይጠይቅም፡፡ ስሙ ሳይጻፍ እንኳን ገንዘብ መርዳት ይፈራል፡፡ በሚበድላቸው ኢህአዴግ ሲታዘዙ ግን ሚሊዮን ብር ዘርግፈው ይሰጣሉ፡፡ ኢህአዴግን ለሚታገል ድርጅት ብለው የገንዘብ ድጋፍ አያደርጉም፡፡ ለመብቱ መታገል ያለበት እያንዳንዱ ዜጋ ነው፤ ህዝብ ነው፡፡

➢ እርስዎ ያሉበት የመድረክ የውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እስከ ዛሬ ምን ሠራ? ለመሆኑ እቅድ አለው? የስድስቱን ፓርቲዎች የውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴዎች ያስተባብራል? ግንኙነትስ አለው? አቅጣጫስ ያሲዛል?

ከላይ እንደገለጽኩልህ በጤና ምክንያት ከኮሚቴው ጋር የተፈለገውን ያህል አልተጓዝኩም፡፡ ኮሚቴው በሥራ አስፈጻሚው የፀደቀ እቅድ አለው፡፡ ለማንኛውም ሥራ ገንዘብ ወሳኝ ነው፡፡ ቁርጠኝነት ያለው አገር ወዳድ ዜጋ አልተገኘም፡፡ ውጪ አገር ሄደን የመድረክን ዓላማና ፕሮግራም ለማስረዳት ድጋፍ ለማሰባሰብ የትኬት ወጪ የሚሸፍን እንኳን አልተገኘም፡፡ ይህ ውጪ ላሉ ኢትዮጵያውያን በጣም ቀላል ነው፡፡ አገር ውስጥ ላለው ከባድ ነው፡፡ ቋሚ ኮሚቴዎች በጠቅላላ በእቅዳቸው ለመንቀሳቀስ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ገንዘብ መርጃው ሰዓት አሁን ነው፡፡ በውጪ አገር የተለመደ ነገር አለ፡፡ አገሬ ከእኔ ምን ትፈልጋለች፤ ብሎ ያስባል፡፡ ከመዝናኛዬ ይህንን ቆጥቤ፤ ለእኔ ለሚታገለው ብሎ ያጠራቅማል፤ ይረዳል፡፡ በአገር ውስጥም፤ ከድራፍት፣ ከሻይ ቡና ቀንሶ ለሚታገልለት ድርጅት መርዳት ይጠበቅበታል፡፡ እጅንና እግርን አጣጥፎ ጣት በማንም ላይ መቀሰር ትርፉ ትዝብት ነው፡፡ ኑሮ ተወደደብኝ ፍትህ አጣሁ፡፡ የዜግነት መብቴ ተነካ ማለት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ሊስትሮውም ሳይቀር ብሔራዊ ግዴታ አለበት፡፡

➢ በአገራችን በርካታ አሳሪ ህጐች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ተቃዋሚዎች እነዚህን አሳሪ ህጐች ለመቃወም ያደረጉት ትግል በቂ ነው ብለው ያምናሉ?ለምሳሌ የአሰብን ወደብ በመቃወም፣ የኤርትራን የማስገንጠል ድምጽ አሰጣጥ ሂደት በመቃወም፣ ፊርማ ተሰባስቦ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የታሪክ ማህደር ሆኖ ተቀምጧል፡፡ እነዚህን አፋኝ ህጐች በመቃወም ምን ተሠራ? ዛሬስ የሚጠበቅ ነገር የለም? ይላሉ፡፡

እኔ ፓርላማ በነበርኩበት ወቅት ለአገርና ለህዝብ አይጠቅሙም፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጐጂ ናቸው፤ ያልናቸውን ሁሉ አውግዘናል፡፡ ተቃውመናል፤ ህግ ሆነው እንዳይወጡ ታግለናል፡፡ ሆኖም ግን ኢህአዴግ በሚከተለው የማን አለብኝነትና ጀብደኝነት ባህርዩ በጉልበት አዋጅ አድርጐ አውጥቶአቸዋል፡፡ የፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ፣ የብዙኃን መገናኛ አዋጅ፣ የበጐ አድራጐት አዋጅ፣ የፀረ ሽብር አዋጅ፣ የመሳሰሉትን አዋጆች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዛሬ በእነዚህ በእብሪት በወጡ አዋጆች ንጹሐን ዜጐች እየማቀቁ ናቸው፡፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የመድብለ ፓርቲ ሥረዓቱ አደጋ ውስጥ ገብቷል፡፡ በወቅቱ ህዝቡ በዝምታ አልፎታል፡፡ ኢህአዴግ ባለው ንቀትና በተጠናወተው ማን አለብኝነት በቅርቡ የሊዝ አዋጅንም አውጥቷል፡፡

አገሪቱ የምትመራው እኛ እናውቅራሐለን በሚሉ በጥቂት ሊቅህን ፖሊሲ አውጪዎች ነው፡፡ የአገሪቱ ምሁራን፤ የአገሪቱ ዜጐች አይሳተፉበትም፡፡ አገሪቱንና የህዝቡን ፍላጐት የማያውቁ ራሳቸውን ብቻ በሚሰሙ ጥቂት ሊቅህን አገር ይታመሳል፡፡ ህዝብ ሊቃወማቸው ይገባል፡፡ እዚህ ጋ ቁሙ ከላላቸው ዛሬም በትቢትና በእብሪት ይቀጥላሉ፡፡ ምርጫ ቦርድ ኃላፊነቱ በገለልተኝነት እየተወጣ አይደለም፡፡ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት ኢህአዴግን ለማግዘፍ ነው፡፡ ለተቃዋሚዎች ሦስት ሺ ብር ሰጥቶ ከውጪ ኦዲተር 20 ሺ ብር ክፍላችሁ ሂሳባችሁን አስመርምራችሁ አሳውቁኝ፡፡ ይህንን ካላደረጋችሁ እሰርዛችኃላሁ የሚልተቋም ነው፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ሁለተኛ ድምጽ ያገኘ ፓርቲን አግልሎ ለሌሎች የአየር ሰዓት ሲሰጥ ዝም ብሎ የሚመለከት ነው፡፡

➢ ሐሳቦን ጠቅለል አድርገው በመጨረሻ ላይ ሊገልጹት የሚፈልጉት ሐሳብ ይኖራል?

በአገር ውስጥም በውጪ አገርም የምትኖሩ ኢትዮጵያኖች በጠቅላላ እባካችሁን ቆም ብለን እናስብ፡፡ በነገው ትውልድ እንዳንጠየቅ፡፡ ታሪክ ይቅርታ የሌለው ቅጣት እንዳይቀጣን፡፡ የግል አጀንዳ ይቁም፡፡ ቁጭ ብለን የመነጋገር ቁርጠኝነት ይኑረን፡፡ እኔ አውቅልሐለሁ፤ አንተ አታውቅም የሚለው አስተሳሰብ ይቁም፡፡ ምን ቸገረኝ፤ ዛሬ የፈለኩትን ነገር ካገኘሁ፤ በኮብራ ከተጓዝኩ፣ ፎቅ ከሠራሁ፣ ልጆቼን ፈረንጅ አገር ከላኩ፣ ስለሌለው አያገባኝም የሚለው አስተሳሰብ ለማንም አይጠይቅም፡፡ ጉዳቱ በምንም የሚለካ አይደለም፡፡ በጉድፍ የተሞላውን የአገራችን የፖለቲካ ጉዞ እንግታው፡፡ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ፖለቲካ እናስብ፡፡ ህዝብ በአገሩና በራሱ ጉዳይ ያገባዋል፡፡ በስሙ የሚነግዱትን፣ ወንጀል የሚፈጽሙትን በቃችሁ ሊላቸው ይገባል፡፡ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

# የአቶ መለስ እዉነተኛ . . .

ከገፅ 15 የዞረ

የአቶ መለስ እዉነተኛ የሥልጣን መሠረቶች

እንደ ጸሐፊዉ ሀሳብ የመጀመሪያዉ የአቶ መለስ የሥልጣን መሠረት የአንድ ብሔረሰብ አባል የሆኑ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች ናቸዉ፡፡ በእኔ ሀሳብ ግን እዉነተኛዉ የአቶ መለስ የሥልጣን መሠረቶች ፕሮፓጋንዳ እና የኃይል አገዛዝ ናቸዉ፡፡

የእነዚህን ሀሳቦች ትክክለኛነት ሰሜን አፍሪካ ላይ በቅርብ ከተደረጉትና በመደረግ ላይ ካሉት አብዮቶች ያየነዉና እያየንም ያለነዉ ቢሆንም፣ ከዚሁ ሀገራችን ተመልሰን ብዙ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ የሊቢያና የሶሪያ ሁኔታዎች ለየት ያሉ በመሆናቸዉ፣ የዚህን ልዩነት መሠረት ማየት አንድ ብሔረሰብ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያለዉ እዉነተኛ ተፅዕኖ እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመገንዘብ ስለሚረዳ መጀመሪያ እሱን ላስረዳ፡፡

በሊቢያ እና በሶሪያ የታየዉ የኃይል አገዛዝ ወይም አምባገነንነት በብሔረሰቦች ልዩነት ወይም አንድ የብሔረሰብ አባላት የመንግሥትን ሥልጣን በመቆጣጠራቸዉ ሳይሆን፣ የየሀገሮቹ መንግሥታት መሪዎች፣ ማልትም የጋዳፊ እና የሀፌዝ አልአሳድ፣ ቤተሰቦች እና ዘመዶች ሥልጣኑን በመቆጣጠራቸዉ ነዉ፡፡ ይህም በመሆኑ በሊቢያ አብዮት ማግሥት ሕዝብ በተባበረ ኃይሉ የጋዳፊን አምባገነን መንግሥት ሲለዉጥ፣ የሥልጣን ተጋሪ ቤተሰቡን እና ዘመዶቹን አይቀጡ ቅጣት ቀቷቸዋል፡፡ በታሪክ እንደተረጋገጠዉ፣ ምን ጊዜም ሕዝብ ቆርጦ ሲነሳ አሸናፊ ነዉና፣ በሊቢያ የደረሰዉ፣ ዉሎ አድሮ፣ በሶሪያም ይደገማል፡፡

ችግሩ፣ አምባገነኖች በወቅቱ የሕዝብን የለዉጥ ፍላጎት ተገንዝበዉ፣ ለሰላማዊ የመንግሥት ሽግግር ዝግጁ መሆናቸዉን በተግባር ለመግለጽ አለመፈለጋቸዉ ወይም እጅግ ከፍተኛ ጉዳት በሕዝብ ላይ ካደረሱ በኋላ የለበጣ ማሻሻያ ፖሊሲ ለማቅረብ ዝግጁ መሆናቸዉን የሚገልጹ መሆኑና፣ ሕዝቡ እና ተቃዋሚዎች ግን የማይቀበሉ(በበቂ ምክንያቶች፤ ለምሳሌ ብዙ የሕይወት መጥፋት ካደረሱ በኋላ) በመሆኑ፣ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በአምባገነን መሪዎች የሚገዙ ሀገሮች ሕዝብ የሚከፍለዉን ከፍተኛ መስዋዕትነት የመቀነስ ኃላፊነት፣ በሕዝብ ወገኖች እና በሕዝቡ ትከሻ ላይ የወደቀ ይመስላል! ይህንን ወደ ኋላ ገደማ እናየዋለን፡፡ ለጊዜዉ ወደ ተነሳንበት የአቶ መለስ የሥልጣን መሠረቶች እንመለስ፡፡

አቶ መለስ እና ፓርቲያቸዉ የኢትዮጵያን መንግሥት ሥልጣን የጨበጡት በመድበለ ፓርቲ ስም እንጂ፣ አንድን ብሔረሰብ በሚወክል፣ በሕወሓት ስም፣ አይደለም፡፡ እነዚህም መድበለ ፓርቲዎች እንደሚታወቁት፣ ሕወሓት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድ እና ደሕዴን(ዘግይቶ የተወለደ ቢሆንም) ናቸዉ፡፡

ምንም እንኳ እነዚህ ፓርቲዎች በብሔረሰቦቻቸዉ ዘንድ ጠንካራ መሠረት እንደሌላቸዉ ቢታወቅም፣ ሕወሓት-ኢህአዴግ ሥልጣንን የሙጥኝ ብሎ እያቆየ ያለዉ በእነዚህ፣ የእርሱ ፈጠራ ዉጤት በሆኑት፣ ድርጅቶች አማካይነት መሆኑ የሚታወቅ ነዉ፡፡

እነዚህ አራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች ደግሞ ዋነኛዉ መሣሪያቸዉ ካድሬዎች ናቸዉ፡፡ ካድሬዎች በሕዝብ ላይ በሚፈጽሙት ተፅዕኖ፣ ጫና እና በሚጠቀሙት ኃይል ምክንያት ሕዝቡ መፈናፈኛ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ካድሬዎቹ ሲሆንላቸዉ ሕዝቡን በመሸንገል፣ ካልሆነላቸዉም በማስፈራራት እና የዕለት ጉርሱን እና መተዳደሪያዉን በመቆጣጠር፣ ሕዝቡን ከፍላጎቱ ዉጭ ያስገድዱታል፡፡

ከዕለት ጉርሱ ጀምሮ እስከ ዘላቂ መተዳደሪያዉ ሲያዋክቡት፣ ሲያስሩት እና መሬቱን ሲቀሙት፣ ሕዝቡ ፋታ አግኝቶ በዉል በዘላቂ ፍላጎቱ ላይ ማተኮር አልቻለም፡፡ ስለዚህም እዉነተኛ የአቶ መለስ የመንግሥት ሥልጣን መሠረት የአራቱ ፓርቲዎች ካድሬዎች እንጂ ፓርቲዎቹ እንወክላቸዋለን የሚሉት ብሔረሰቦች አይደሉም፡፡

የአራቱ ፓርቲዎች ካድሬዎች ተፅዕኖ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሁሉ በላይ ግን ሕወሓት-ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ሲወጣ፣ የበረሐ ፕሮፖጋንዳዉ የሕዝብን ሥነ-ልቦና እንደሳበለት ሁሉ፣ አሁንም ፕሮፖጋንዳዉ በሕዝብ ላይ በማሳደር ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ ለዚህም ተፅዕኖ ዋነኛዉ መሣሪያዉ፣ መንግሥታዊ ጋዜጦች የራሳቸዉ አስተዋጽኦ እንዳላቸዉ የታወቀ ቢሆንም፣ የስርጭታቸዉ ስፋት ሀገር-አቀፍ ከመሆን አንፃር፣ ተነባቢነታቸዉ ደካማ ነው፡፡ ከጋዜጦቹ ይልቅ፡፡ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ዋነኞቹ ናቸዉ ቢባል ማጋነን አይመስለኝም፡፡ ጠዋት፣ ቀንና ሌሊት ሳይባል የሀሰት፣ ግን ለሕዝብ አሳች እና ማደናገሪያ የሆኑ የመንግሥት ፕሮፖጋንዳ ይነዙለታል፡፡ ሃይ የሚላቸዉም አልተገኘም!

የአቶ መለስ የመንግሥት ሥልጣን መሠረቶች የአራቱ ፓርቲዎች ካድሬዎች የኃይል አገዛዝ፣ ፕሮፖጋንዳቸዉ እና የፕሮፖጋንዳ መሣሪያዎቻቸዉ መሆናቸዉን እንደምንስማማ ተስፋ እያደረግሁ፣ ጸሐፊዉ ያነሱትንም ሀሳብ ማየት ሀሳባችንን የተሟላ ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ ጸሐፊዉ እንዳሉት ሕወሓት በአንድ ብሔረሰብ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች መሠረትነት የሚንቀሳቀስ ፓርቲ እና መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ በማናቸዉም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተመሳሳይ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረጉ፣ የአንድ ብሔረሰብ ባለሙዋሎች ጠቅላላ የሀገሪቱን ሥራ እና ሠራተኞች እየተቆጣጠሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ባሉት ሁለት ሥርዓቶች ካየነዉ የባሰ መሆኑን ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያዉቀዉ ነዉ፡፡

ይህንን ስልት ሕወሓት የሚጠቀመዉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመቆጣጠር ብቻ ሳይሆን የርሱንም አባል ድርጅቶች እና ባለሥልጣኖች ጭምር ለመቆጣጠር ነዉ፤ የተሳካለት ባይመስልም! ሥልጣኑን ከድተዉ በእየ ጊዜዉ ወደ ዉጭ ሀገር ተልከዉ የማይመለሱትና እዚያዉ በሄዱበት ሀገር ተሰድደዉ የሚቀሩትን ባለሥልጣኖች፣ እንዲሁም በቅርቡ በራሳቸዉ በአቶ መለስ የተነገረዉ፣ ሕዝቡ ግን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲጮህ ስለነበረዉ፣ የመንግሥት ሌቦች እና የግል ሌቦች ያስታዉሰዋል፡፡

የሕወሓት ተግባር እንደሚያሳየዉ፣ በእሱ እምነት ታማኝ የሆኑት የርሱ ብሔረሰብ አባላት ብቻ ናቸዉ፡፡ ሕወሓት ለጊዜያዊ ጥቅም አልሞ ወይም በሚገባ ባለማጤኑ ነዉ እንጂ፣ የታማኝነት መሠረት ብሔረሰብ ወይም ሃይማኖት ወይም ሁሉቱ ሳይሆኑ የግለሰቦች (የቡድን) ዓላማ እና ጥቅም ናቸዉ፡፡

የሰሜን አፍሪካ አብዮቶች፣ ከቱኒዚያ ጅምሮ፣ በግብጽ፣ በሊቢያ፣ እንዲሁም በሶሪያ እየታየ ያለ ነዉ፡፡

በቱኒዚያ እና በግብጽ የመከላከያ፣ የደህንነት፣ የፖሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪል መሥሪያ ቤቶች ባለሥልጣኖች ገና በጅምሩ አብዮቱን የተቀላቀሉ በመሆኑ የሕዝቡን እና የራሳቸዉን መስዋዕትነት ሊቀንሱ ችለዋል፡፡ በሊቢያ ግን ዘግይተዉ በመቀላቀላቸዉ ከሁሉም ወገን የተከፈለዉ መስዋዕትነት የማይገባ ከፍተኛ እንደሆነ ሁላችንም የምናስታዉሰዉ ክስተት ነዉ፡፡

ይሁንና የማንም ሕዝባዊ ንቅናቄ ዓላማ የማናቸዉንም ወገን መስዋዕትነት እና የንብረት መዉደም መቀነስ ነዉ ለማለት እገደዳለሁ፡፡ ለዚህ ግብ መምታት፣ ዋናዉን ወሳኝ ኃላፊነት የሚሸከሙት፣ የሕዝብ ወኪል የሆኑ ጥቂት የመከላከያ፣ የደህንነት፣ የፓሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪል መሥሪያ ቤቶች ባለሚሎች፣ ባለሥልጣኖች እና መላዉ የተማረዉ ክፍል እና ራሱ ሕዝብ ነዉ፡፡

የኢትዮጵያችንን ሁኔታ ስንመለከት እነዚህ ኃይሎች የሕዝብ ብሶት የእነሱም እንደሆነ ይገነዘባሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ከሕዝቡ ጋር በብዙ ገመዶች የተሳሰሩ ከመሆናቸዉም በላይ፣ ከእነሱ መካከል የዋጋ ዉድነት፣ የኤሌትሪክና የዉሀ አገልግሎት በእየጊዜዉ መቋረጥ ሥራዉን ያላቋረጠበት፣ ያላሰለቸዉና ያላሳዘነዉ ማን አለ? ሥራ አጥነትስ፣ የወጣቱ እና የሴቱ ሕጋዊ ቦዜኔነትስ፣ እኒያ “አደገኛ ቦዘኔ” ሲባሉ የነበሩት ሥራ አጦች ችግር፣ የማንን ቤት አላንኳኳም?

እነዚህ ኃይሎች ለጊዜዉ በሚያገኙት ትንሽ ጥቅም፣ የወቅቱ ችግር የብዙሐኑን ያህል አይሰማቸዉ ይሆናል! በተለያዩ ምክንያቶችም ሊዘናጉ ይችሉ ይሆናል! ሆኖም ችግሩ በሕዝብ አሸናፊነት መደምደሙ የማይቀር የታሪክ ሐቅ በመሆኑ ቶሎ ነቅተዉ ሚናቸዉን ይለያሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ይህ ባይሆን፣ ከግለሰቦች ባሻገር፣ በህብረተሰቡም ዉስጥ በቀላሉ የማይሽር ጠባሳ ትቶ እንደሚያልፍ ማስተዋል ሊቅ መሆን አይጠይቅም፡፡

የጠባሳዉ ምልክት፣ ለሕዝብ አላሰፈላጊ ደም መፍሰስ፣ ተጠያቂ መሆን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለሕዝብ ደም ተጠያቂ ላለመሆን ደግሞ እያንዳንዱ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪል መሥሪያ ቤቶች ባለሙዋሎች እና ባለሥልጣኖች ጊዜዉ ሳይመሽ ለሕዝብ ፍላጎት ተገዝተዉ ከሕዝብ ጎን መሰለፍ የግድ ይላል፡፡ የአምባገነኖች ፕሮፖጋንዳ እና የተለያዩ የሽንገላ ዘዴዎች ሊያሳስቷቸዉ ወይም ሊያዘናጓቸዉ አይገባምና!

ከጠባሳዉ በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዥ መኮንኖች እና ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪል መሥሪያ ቤቶች ባለሙዋሎች እና ባለሥልጣኖች ሊያስቡበት የሚገባ ሌላም ብርቱ እዉነት አለ፡፡ግለሰብ እና ፓርቲዉ እንዲሁም መንግሥት ልዩ መሆናቸዉን፣ እስካሁን ካላስተዋሉ፣ ቶሎ ለመገንዘብ የበኩላቸዉን ጥረት ማድረግ የግድ ይላቸዋል፡፡ ስለዚህ

ወደ 5 ዞሯል

# ግልጽ ደብዳቤ ለአርቲስት ደበበ እሸቱ



ከአሥራት ጣሴ

አዲስ አበባ

ይህ ደብዳቤ ከአንድነት ፓርቲ ሆነ በፓርቲው ውስጥ አሁን ካለኝ የሥራ ኃላፊነት ጋር የሚያይዘው ምንም ነገር የለም፡፡ ደብዳበው የግሌ ነው፡፡ ደብዳቤውን እስከ ዛሬ ያዘገየሁት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ድንቅ አርቲስትነትዎን በአሳዩበበት የአኬልዳማ ድራማ ማግሥት ብጽፍሎት በሞራልዎ ላይ ጉዳት አደርስ ይሆን ብዬ በመፍራትና በማዘንም ጭምር ነው፡፡ ሆኖም የማውቀውንና በውስጤ ያለውን እውነታ ለሕዝብ ሳላሳውቅ ብቀር ደግሞ ከህሊና ወቀሳ ባሻገርም በሀቅ አምላክና በታሪክም የሚያሰጠይቅ ነው ብዬ በማመኔ ደብዳቤውን ለመፃፍ ተገድጃለሁ፡፡

አርቲስት ደበበ እሸቱ!

በመጀመሪያ እርስዎም ሆኑ ሌሎች አንባቢያን እንዲረዱልኝ የምፈለገው አንድ ሃቅና ቁምነገር አለ፡፡ የዚህ ግልጽ ደብዳቤ ዋና ዓላማ እርስዎ ታአማኒነት የሚጎድሎት መሆኑን ለማሳየት፣ እውነት የመናገር ችግር እንዳለበዎት ለማስረዳት ነው፡፡ በመሆኑም በማንኛውም ቦታ ሆነ ጊዜ የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ‹‹የአኬልዳማውም›› ጭምር ታአማኒነት የሚጎለውና ክፍተት ያለበት፤ መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ ከዚህ ያለፈ ምንም ዓላማ የለውም፡፡

የማውቃቸው እውነቶች

መጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በሰሜን አሜሪካ ለሚገኘው የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ሰጪ ኮሚቴዎች ሊቀመንበር ለአቶ አክሎግ ልመንህ ስልክ ደውለው

1. ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው
2. ዶ/ር ኃይሉ አርአያ እና
3. አቶ አስራት ጣሴ

የጎግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆኑት አቶ ውብሸት ታዬ ቢሮ ድረስ በመሄድ ‹‹ደበበ እሸቱ የግንቦት 7 ንቅናቄ ወኪል ነው›› ብለን እንደወነጀልንዎ ለዚህም ማስረጃ እንዳለዎት ገለጹላቸው፡፡

አቶ አክሎክ ልመንህም በእለቱ ጉዳዩን ለኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው በስልክ በገለፁላቸው ወቅት እኔም አካባቢው ስለነበርኩ የዚህን አስደንጋጭ ወሬ ለመስማት ችያለሁ፡፡ ሁለታችንም በነገሩ በጣም ተደናገጥን፡፡ ነገሩ ታአምር ሆነብን፡፡ በማግስቱ ሦስታችንም ተከሳሾች ቢሮ ተገናኝተን የተካሄደው የስም ማጥፋት ዘመቻ በጣም ከባድ በመሆኑ ክሱ በአስቸኳይ እንዲጣራ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውም እርስዎን እንዲያነጋግሩና ማስረጃዎቹዎን በአስቸኳይ እንዲያቀርቡ ስምምነት ላይ ደርሰን ተለያየን፡፡

እንደሚያስታውሱቱ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውና እርስዎ አምስት ኪሎ በሉሲ ሬስቶራንት ማክሰኞ መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓም ተገናኝታችሁ ስትነጋገሩ አንድ አዲስና ሌላ ታአምር ነገር ተከሰተ፡፡ ኢ/ር ግዞቸው ሽፈራው ከተከሳሾቹ መካከል የሌሉ መሆናቸውን በእሳቸው ቦታ ክስ የቀረበባቸው ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም መሆናቸውን ገለፁላቸው፡፡ በሁለት ቀን ውስጥ እንዲህ አይነት ለውጥ ከታአምር ውጭ ምን ሊባል ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ለአቀረቡት ክስ ያሎትን ማስረጃ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደሚያቀርቡ ቃል ቢገቡም አንዴ የመኪና አደጋ ደረሰብኝ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ እዚህ ግባ የማይባሉ ምክንያቶችን እየደረደሩ ከጉዳዩ መሸሽን መረጡ፡፡ በዚህም እውነት የሌሎትና ሁሉም ነገር የውሸት ክምር መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጣ፡፡ እስቲ ይመልከቱ! እነዚህ አዛውንቶች እርስዎን በግንቦት 7 ወኪልነት ለመወንጀል ጎግል ቢሮ ድረስ ተያይዘው ሲሄዱ ምን አይነት ከአስተዋይነትና ከእውት የመጣላት አባዜ እንደሆነ አንባቢ ይፍረደው፡፡

አርቲስት ደበበ እሸቱ!!

ከላይ የጠቀስኩት ጉዳይ አንድ መልክ ሳይዝ ወይም እልባት ሳያገኝ ሌላ በአይነቱ ‹‹አኬልዳማን›› የሚመስል ድራማ ሰሩ፡፡ እስቲ እረስተውት እንደሆነ ላስታውስዎ፡፡ ሚያዚያ 3 ቀን 2001 ዓም በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የብሔራዊ ምክር ቤት ላይ በእኔ ላይ በአምስት ወንጀሎች ክስ ቀረበ፡፡ ለክሶቹ 10 ምስክሮች ቀርበዋል፡፡ 10 ምስክሮች በአጠቃላይ 21 ጊዜ መስክረዋል፡፡ አንድ ምስክር በአራት ክሶች ላይ ሦስት ምስክሮች በሦስት ክሶች ላይ ሁለት ምስክሮች በሁለት ክሶች ላይ ሲመሰክሩ እርስዎን ጨምሮ አራት ምስክሮች በአንድ ክስ ላይ መስክረዋል፡፡ የሁላችሁም ፊርማ ያለበት የክሱ ሰነድ ዛሬም በእጄ ይገኛል፡፡ መስካሪዎቹ በሙሉ እርስዎ ጭምር ኋላ ላይ እራሳችሁን ‹‹ዝም አንልም›› ወይም ‹‹መርህ ይከበር›› ብላችሁ መሰየማችሁም የሚዘነጉት አይመስለኝም፡፡

በዚህ ግልጽ ደብዳቤ የማተኩረው እርስዎ በአቀረቡት አንድ ክስና በምስክርነት በቀረቡበት ሌላ አንድ ክስ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ በክሱ ተቁ 5 ላይ እንዲህ የሚል ውንጀላ አቅርበው ነበር፡፡

‹‹አቶ አሥራት ጣሴ በ11/07/2001 የጎግል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ድረስ በመሄድ ለጋዜጣው ዋና አዘጋጅ አቶ ደበበ አሸቱ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር እየተገናኘ የግንቦት 7ን ዓላማ በፓርቲያችን ውስጥ ለማስፈፀም በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ነው›› የሚል ነ፡፡ ለዚህም ክስ ሦስት ምክስሮችን አቅርበዋል፡፡ እስቲ ሁኔታውን በሰከነ አእምሮ ይመልከቱት፡፡ በመጋቢት 18 ቀን በዚሁ ጥፋት እኔን ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውንና ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ከሰሱ ከሁለት ቀን በኋላ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውን ነፃ አውጥተው ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያምን በእሳቸው ቦታ ተኩ፡፡ ከ14 ቀናት በኋላ ሁለቱን ተከሳሾች ትተው ሙሉ ክሱን በእኔ ላይ ጫኑት፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ ሁለቱ ተከሳሾች ነፃ ናቸው፡፡ ‹‹ተሳስቼ ነበር ይቅርታ እጠይቃለሁ›› እንኳ አላሉም፡፡ ይህ ምን ያህል የተዓማኒነት ችግር እንዳለበዎት ከማሳየቱም ባሻገር እኝህ ሰው የሚናገሩትንና የሚሰሩት በእውን ያውቃሉን? የሚያሰኝ ነው፡፡ ከፍተኛ የእውነት ችግር አለበዎት፡፡ ምስክርነቶ ሁሉ ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገባ ነው፡፡

እስቲ ምስክር ሆነው የቀረቡበትን በተቁ 3 ስለአለው ክስ ላስታውሰዎ! ‹‹አቶ አስራት ጣሴ ለፓርቲያችን የሚሰሩ እየመሰሉ ፓርቲውን ለማፍረስ ኢህአዴግ ገንዘብ እየከፈላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን ፓርቲው ጽ/ቤት የሚውሉ አባላት ስለ መኖራቸው ተጨባጭ ማስረጃ እንዳለው በተደጋጋሚ ተናግረዋል›› ለሚለው ነው፡፡

ተጨባጭ ማስረጃ ካለኝ ለምን ለፓርቲው አቅረቤ በሰዎቹ ላይ እርምጃ አላስወሰድኩም? ተጨባጭ ማስረጃ ሳይኖረኝ ግን እንዲህ ዓይነት ቋንቋ በፍፁም አልጠቀምም፡፡ ልጠቀምም አልችልም፡፡ ያስጠይቃልም፡፡ ቢኖረኝ ደግሞ ወደ ኋላ የማልል ለሀቅ የምቆም የሚታገል መሆኔን የሚያውቁ ይመስለኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ ብዙ ዋጋ ከፍየበታለሁ፡፡ ወደፊትም ለመክፍል ዝግጁ ነኝ፡፡ የእርሶ ምስክርነት የሀሰት ምስክርነት ነው፡፡ ለመሆኑ በየጊዜው በሥራ አስፈፃሚ ስብሰባ ላይ ውይይት የተደረገባቸው ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮች በኢትዮቻናል ጋዜጣ ላይ ይወጣ እንደነበረ አያስታውሱም?፡ ለኢፌዴሪ ፕሬዚደንት ለክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር በ08/08/2004 ዓም የተፃፈ ደብዳቤና ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚያውቁት ሰነድ መንግሥት እጅ መድረስ ከሚገባው ቀን በፊት ለመንግሥት እንደደረሰ ዘነጉት ወይ? የሚገርም ነገር ቢኖር ኢህአዴግ አደረገ ያልኩትን ባያደርግ ነው፡፡

ያስታወሱ እንደሆን የቀረቡብኝን ክሶች በሚመለከት ብሔራዊ ምክር ቤቱ አጣሪ ኮሚቴ አቋቁሞ በእኔና ሌሎች በፓርቲው ውስጥ አሉ ስለተባሉ ጉድለቶች አጣርቶ ሪፖርቱን ለምክረ ቤቱ አቅርቧል፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ የቀረቡብኝ ክሶች ተጨባጭነት የሌላቸው ሀሰተኛ ክሶች መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ እንደሚያውቁት ሌላውና ወሳኝነት ያለው ምስክርነቱን የሰጠው ደግሞ የማከብረው የጎግል ዋና አዘጋጅ የነበረውና በኋላ ላይ የአውራምባ ታይምስ ም/አዘጋጅ የሆነው አቶ ውብሸት ታዬ ነው፡፡ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውና ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በእኔ ላይ የቀረበው ክስ በጽሑፍ ስለ ነበር ዋና አዘጋጁን አንድነት ቢሮ ድረስ አስጠርተው ጠይቀውታል፡፡ አቶ ውብሸት ታዬም እኔ የጎግልን ቢሮ የማላውቀው መሆኑን እርስዎን አስመልክቶ አንድም ቃል ለእሳቸው ያልወጣኝ መሆኑን በመግለጽ እንደዚህ ዓይነቱ አሉባልታና ውሸት በእኔ ላይ መሰንዘሩና እሳቸውም የዚህ ጉዳይ አካል ሆነው መጠቀሳቸው ያሳዘናቸው መሆኑን ገልጿል፡፡

አርቲስት ደበበ እሼቱ !

መቼም እርሶ ሀሰት መናገርን እንደ ችግርና ነውር የሚያዩት አይመስልም፡፡ ‹‹በአኬልዳማ›› ድራማ ውስጥ ደግሞ አንድ አስገራሚ ነገር ይዘው ብቅ አሉ፡፡ የግንቦት 7ትን ጋዜጣ በኢ-ሜይል ለነማን ልከዋል ተብለው ሲጠየቁ ከዘረዘሯቸው የሰዎች ስም ዝርዝር መካከል ለአሥራትም መላክዎን ገልፀዋል፡፡ አረ! እግዚአብሔርን ይፍሩ እኔና እርስዎ ክሱን ከአቀረቡብት ሰዓት ጀምሮ ተነጋግረንም ሆነ ተገናኝተን አናውቅም፡፡ በምን ምክንያት ነው የግንቦት 7ን ልሳን ለእኔ የሚልኩልኝን እንዳላኩልኝ? ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡ በመጨረሻ የመጽሐፍዎን ርእስ ‹‹ የሕሊናዬ ፈተና›› የሚለውን ቃል ልዋስዎና ለዚህ ግልጽ ደብዳቤ የሚሰጡኝ መልስ የሕሊናዎ ፈተና እንደሚሆን እገምታለሁ አምናለሁም፡፡

ከሠላምታ ጋር

## የሙስና ነገር. . .

ከገፅ 12 የዞረ

ከፓርላማ እስከ ቀበሌ አሸባሪ የሚል ቃል እንደፋሽን ሆኗል፡፡ ይህም ለፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ለገለልተኛው ህዝብ ሁሉ አስደንጋጭ ቃል ሆኗል ፡፡ የሆነ ሰው የሆነ ተራ ስህተት ቢፈፅም መጠርያው አሸባሪ ነው፡፡ጉዳዩ ራሱ ሽብር ሆኖዋል ፡፡

የግል ብዙሃን መገናኛን በሚመለከት

የህወሓት ኢህአዴግ መንግስት የግል ብዙሃን መገናኛን በጠላትነት በመፈረጅ እንዲከስሙ ሲሰራ 20 ዓመት አስቆጥሯል፡፡ ይህ ደግሞ ህዝቦች ሚዛናዊ እውቀት እንዳያገኙ ከማድረጉም አልፎ ሃሳባቸውን እንዳይገልፁ እሚያደርግ አፋኝ ድርጊት ነው፡፡ በመሆኑም በኔ እምነት ማሰር፣ ጋዜጦች እንዲከሰሱ፣ እንዲዘጉ ማድረግ አገርን ለእድገት ወደኋላ ጐታች ከመሆኑም አልፎ ህወሓት /ኢህአዴግ በትግሉ የጣላቸውን የአፄ ኃይለ ሥላሴና ደርግ ስርአቶች መልሶ ፀረ ነፃ ብዙሃን መገናኛ ሆኖ አረፈው፡፡ ይህም በህዝብ ትግል የመጣ የነፃ ብዙሃን መገናኛ መብት መከበር አለበት፡፡ ለህወሓት ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊነትና የተሻለ ሆኖ መምጣትም መመዘኛውም ይህ ነው፡፡

## ቫት ሲተለተል ! !

ኑሮን ካስወደዱት ነገሮች አንዱ የቫት አሰባሰብ እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ቫት የሚጐዳው ነጋዴውን ሳይሆን ተጠቃሚውን ነው ይባላል። ለምሳሌ ስኳር ከፋብሪካው ሲወጣ የጨረታ አሸናፊው ቫት ይከፍልበታል። ስኳሩን ከተረከበ በኋላ የገዛበትን ዋጋ፣ ለቫት የከፈለውን፣ ትራንስፖርት ያወጣውን፣ የሚፈልገውን ትርፍ ደምሮበት ለየአካባቢው አከፋፋዮች ይሸጣል። የየአካባቢው አከፋፋይ ዋጋውን ከፍሎ ተጨማሪ ቫት ከፍሎበት ስኳሩን ይረከባል። ስኳር እስከአሁን ድረስ ሁለት ጊዜ ቫት ተከፈለበት ማለት ነው። የአካባቢው አከፋፋይ የገዛበትን ዋጋ፣ የከፈለውን ቫት፣ የትራንስፖርት የሚፈልገውን ትርፍ ደምሮ ለቸርቻሪ ይሸጣል። ቸርቻሪም እንዲሁ ቫት ከፍሎ ይገዛል። እሱም የራሱን ሰርቶ ለባለ ሆቴሉ ለባለሻይ ቤቱ ይሸጣል። ባለ ሆቴሉ ቫት ጨምሮ አፍልቶ ይሸጠዋል። በአንድ ምርት አራትና አምስት ቦታ ቫት ይከፈልበታል።

የሚገርመው ነገር እያንዳንዱ ቫት ሰብሳቢ በየወሩ የሰበሰበውን ቫት ሲያስገባ ሲገዛ ለቫት የከፈለውን ቀንሶ ያስገባል። ነጋዴው ቫት በመክፈሉ ወይም በመሰብሰቡ ከኪሱ የሚከፍለው አንድ ሳንቲም የለም። አራትና አምስት ቦታ የተከፈለው ቫት የእቃውን ዋጋ ከፍ አድርጐ እዚህ አድርሶታል፡፡ መንግስት በአንድ እቃ ተደጋጋሚ ቫት መሰብሰቡ ልማታችን ያመጣው ችግር ይሆን? በመንግስት የተሳሳተ ፖሊሲ አንድ የሻይ ተጠቃሚ በአንድ ጊዜ አምስት እጥፍ ቫት ይከፍላል። ለማን አቤት ይባል?

## መሬታችን የሚታጠረው በማን ቆርቆሮ ነው?

በጋራ አገራችን በአድ ሆነን ገዢዎቻችን በጠመንጃ አፈሙዝ እያስገደዱን መሬታችንን እየነጠቁን ነው፡፡ "የፋሲካው በገናው በግ ይስቃል" እንደሚባለው ያልደረሰበት በደረሰበት ሲስቅ እያንዳንዱ ቤት እየተንኳኳ ነው። ህወሓት /ኢህአዴግ/ ከሠፈራችን፣ ከእድራችን፣ ከጐረቤቶቻችን፣ ከአብሮ አደጐቻችን እየነጠለ አባሮናል፡፡ እባካችሁ ብለን ስንለምናቸው "ልማት የማትወዱ ፀረ-ልማቶች" እያለ በእንትኖቹ ያሰድበናል፤ ያስረግጠናል። እምባችንን፣ ቁስላችንን፣ ሲያዩ ርካታ ይሰማቸዋል። ጀግንነትን ይላበሳሉ። በድላቸው ይኩራራሉ። በሌላ በኩል ከአገሪቱ ባንክ አበዳሪም፤ ተበዳሪም ሆነው የነጠቁንን መሬታችን ሻጭም ገዢም ሆነው በብዕር ስማቸው ይቀይሩታል። ይሁና።

እኔ አሁን ያልገባኝ ነገር ይህ አይደለም። መሬታችንን ማን እንደነጠቀን ለማን እንደተሰጠ አይደለም። ይህ ግልጽ ነው። መሬታችንን ነጥቀው ካበረሩን በኋላ ለእፎይታ ጊዜ ዙሪያውን በቆርቆሮ አጥር ይታጠራል። ቆርቆሮው ከአንድ ፋብሪካ የወጣ እንደሆነ ይታወቃል። ለመሆኑ የተነጠቀው መሬታችን የሚታጠርበት ቆርቆሮ ፋብሪካ የማን ይሆን? ጉድ ሳይሰማ አይመሽም አሉ።

## አልሞቱምን ምን አመጣው?

የአንበሳው አመጣጥ ያለማራት ጦጣ ሮጣ ዛፍ ላይ ወጥታ እያአንበሳን ቁልቁል ትመለከተው ጀመር። አንበሳው ዛፉ ሥር ደርሶ ዛፉን ተዘዋውሮ ቢመለከተው እንደማያስወጣው ይረዳል። ጦጢት አልበላሽም ነይ ውረጂ ይላታል። አልበላሽምን ምን አመጣው አለቺው ይባላል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ አካባቢ "ያለምንም ደም እንከኗ ይውደም" የሚል መዝሙር ሲያዘምር የሰሙ አንድ አዛውንት "ደምን ምን አመጣው" አሉ። ይባል ነበር። አዛውንቱ እንደፈሩት ቀይ ሽብር ታወጀና አገሪቱ በጠቅላላ ደም በደም ሆነ።

ሰሞኑን የመንግስት ሚዲያ "ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ አልሞቱም" የሚል ዜና የሰሙ አንድ አሮጊት "አልሞቱምን ምን አመጣው" ብለው ሰውን ፈገግ አድርገውታል። ከዚያ ወዲያ ያለው ወሬ ሁሉ ደስ አይልም፡፡ "ምነው ሚኒሊክ ሞተው ሦስት ዓመት ተደብቆ የለ፡፡ ማን ከማን ያንሳል። የሳቸው ሞት ለአንድ ወር ቢደበቅ ምን አለበት?" እያሉ ሲያሽሟጥጡ ቅር ብሎኛል። ማንን እንመን? መንግስትን እንዳናምን ብዙ ጊዜ ዋሽቶናል፡፡ በየካፌው የሚወራውን እንዳናምን ማስረጃ አጣን? ለማንኛውም ሁሉንም ነገር ወደፊት እናየዋለን። ለመሆኑ አያርግባቸው እና የምርጫ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ ቢሞቱ እንዴት እንደሚተካና ማን እንደሚተካ አገሪቱ ህግ አላት? ምን ጣጣ መጣብን ደግሞ?

# የዓለም ደቻሳ ሞት አነጋጋሪ ሆነ

ብሥራት ወ/ሚከኤል

በሊባኖስ መዲና ቤሩት በቤት ሰራተኝነት ከኢትዮጵያ የሄደችው የ33 ዓመቷ ዓለም ደቻሳ አሟሟት አነጋጋሪ ሆነ፡፡ ዓለም ደቻሳ ቤሩት ከሄደች ገና ሦስተኛ ወሯ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን አሰሪዋ አሊ ማህፉዝ ያሰቃያት እንደነበር ተጠቁሟል፡፡ ዓለም ስቃይ ሲበዛባት ወደ ሀገሯ ኢትዮጵያ መመለስ እንደምትፈልግ ለአሰሪዎቿ በተደጋጋሚ ትገልፅ እንደነበርና ይህንንም ቤሩት ለሚገኘው ለኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ማሳወቋን ምንጮቻችን አስታውሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ አሳሪዎቿ ፓስፖርቷን በመያዝ ሲከለክሏት ጠፍታ ወደ ኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ለመግባት ካልተሳካም ለፖሊስ እጅ በመስጠት ወደ ሀገሯ ለመምጣት ስትሞክር አሰሪዋ አሊ ማህፉዝ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን ቤሩት በሚገኘው ኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ፊት ለፊት አስገድዶ በመኪናው ውስጥ ሲያስገባ የተቀረፀው ምስል በሊባኖስ ብሮድካስት ኮርፖሬት ቴሌቪዥን ተሰራጭቷል፡፡ ከዚያም አልጀዚራ ቴሌቪዥንና የተለያዩ ድህረገፆች ጉዳዩን ለዓለም ማኅበረሰብ አዳርሰውታል፡፡ ይህም የተፈፀመው ረቡዕ መጋቢት 5 ቀን 2004 ዓ.ም ነበር፡፡

አሰሪዋም የአእምሮ ህመምተኛ ነች ብሎ ደየር አል ሳሊብ በሚገኘው ዲ ላ ክሮየክ የስነ አእምሮ ሆስፒታል ወስደዋት እንደነበርና ህገወጥ ናት በማለት በቤሩት የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አሳምነው ደበሌ ቦንሳ ሐኪሞች ነግረውኛል ሲሉ ለደይሊ ስታር እንደተናገሩ መዘገቡ ይታወሳል፡፡

በመጨረሻም ዓለም ደቻሳ በአሳዛኝ ሁኔታ በራሷ አልጋ ልብስ ራሷን አጥፋታለች የማለው ወሬ ከተሰማ በኋላ የሊባኖስ ዜጐችም ለህይወቷ መጥፋት ምክንያት የሆነው ግለሰብ ለፍርድ እንዲቀርብ መጠየቃቸው ተጠቁሟል፡፡ በሊባኖስ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም የዓለም አሟሟት እንዳሳዘናቸው በመግለፅ ጉዳዩ በአስቸኳይ ለህግ እንዲቀርብ ጠይቀዋል፡፡

በሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት ከሚኖሩት መካከል ወ/ት ማህሌት ጌይቶም፣ወ/ሮ ሰዓዳ ቃሲም፣ወጣት ብሩክ ረጋሳ፣ወ/ት ሰናይት እንዳሻው፣ወ/ት ፈቲያ አደምና አንድ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ ኢትዮጵያውያን እንደገለፁልን ከሆነ ዓለም ደቻሳ ስቃይ ሲበዛባት ቆንስላ ጽ/ቤት ሄዳ እንደነበርና መፍትሄ ሳይሰጧት አሰሪዋ ይዟት እንዲሄድ በማድረጋቸው በጽ/ቤቱ ፊት ለፊት አሰቃቂ ድርጊት እንደተፈፀመባት ገልፀውልናል፡፡ አያይዘውም የዓለም ደቻሳ ጉዳይ ፊትለፊት ስለወጣ እንጂ ብዙ ኢትዮጵያውያን በአሳሪዎቻቸው ስቃይ እንደሚደርስባቸውና ጉዳዩንም ለቆንስላ ጽ/ቤት ሲያሳውቁ "ትሰሩ እንደሆን አርፋችሁ ስሩ፣አምናችሁ የመጣችሁበት ጉዳይ ነው፣ የራሳችሁ

ወደ 11 የዞሯል

# የመምህራን ደሞዝ ጭማሪ . . .

ከገፅ 1 የዞረ

በአባልነት አልተቀበሉትም፡፡ ይኸው ዛሬ የመምህሩን ጥቅም ስለአስከበርኩ በአባልነት ተቀበሉኝ ብሎ ለማታለል የቀረበ ተራ ድራማ ነው፡፡ በዚህ የሚታለል የለም፡፡ ከንቱ ጥረት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት የማስመሰያ ሥራ ከመስራት አንድም የመምህሩን መብትና ጥቅም ማስከበር ያለበለዚያም እንደተለመደው መንግስትን እያንቆለጳጰሱ ይቀመጡ" በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አንዳንድ መምህራን እንደሚሉት "የደሞዝ ጭማሪው ፍጹም ስህተት ነው፡፡ ያለውን ጥያቄም የመለሰ አይደለም፡፡ የበለጠ የሞያና የሥራ ሞራል የሚጐዳ ስለሆነ ሊወገዝ ይገባዋል፡፡ በዚሁ ምክንያት ጭማሪውን በመቃወም ፊርማ እያሰባሰብን ነው፡፡ ፊርማውን አሰባሰበን እንደጨረስን ለሚመለከተው አካል እናስገባለን፡፡ ጥያቄው የማይመለስ ከሆነ እስከ ሥራ ማቆም አድማ ድረስ እንሄዳለን፡፡ ዛሬ አመራር ላይ ያለው ኢመማ የመምህሩን መብትና ጥቅም የሚያስከብር አይደለም፡፡ ስለዚህ የእሱን አመራር ሳንጠብቅ መብታችንን እናስከብራለን" ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል፡፡

መምህራኑ በትላንትናው ዕለት አጭር የሞባይል መልዕክቶችን ሲለዋወጡ ውለዋል፡፡ መልዕክቱም The gov't dis dainfully disrespect our noblest profession we are ashamed with the fake salary increment. Let's stand together against this! Trust me we min send this to fixe friends. "መንግሥት ክቡር የሆነ ሙያችንን ስያራክስ በኩራት ሆኖ ነው፡፡ በተደረገው የፎገራ የደሞዝ ጭማሪ አፍረናል፡፡ በዚህ ላይ ለመነሳት በጋር መቆም አለብን! እነኙኝ እናሽንፋለን፡፡ ይህን መልዕክት 15 ጓደኞችህ ላክላቸው፡፡" በቅርቡ ለመምህራን ለርዕስ መምህራንና፣ ለሱፐርቫይዘሮች በተደረገው የደሞዝ ጭማሪ የትምህርት ሚኒስቴር ሁለቱ የሚኒስቴር ዲኤታዎች ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ የደሞዝ ጭማሪውን "መምህራንን ወቅቱ የሚጠብቀው ደረጃ ላይ ለማድረስ ተገቢና ወቅታዊ ነው፡፡ የትምህርት ፖሊሲው ብቁና ችግር ፈቺ ትውልድ መቅረጽ የሚያስችል ብለውታል፡፡" የመምህራኑን የደሞዝ ጭማሪ ሲዘረዝሩም "የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ዲፕሎማ መያዝ ያለባቸው ሲሆን ደሞዝ 1233-4343 ብር (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር እስከ አራት ሺህ ሦስት መቶ አርባ ሦስት ብር) ሁለተኛ ደረጃ መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ መያዝ ያለባቸው ሲሆን ደሞዝ 1,644-5,554 ብር (ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ አርባ አራት ብር እስከ አምስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ አራት ብር)መሰናዶ መምህራን ሁለተኛ ዲግሪ መያዝ ያለባቸው ሲሆን ደመወዝ 2,151-4,160 ብር ድረስ ሊከፈላቸው የሚችል ሲሆን ውጤት ያመጡ መምህራን እስከ 6,225 ብር ድረስ ሊከፈላቸው ይችላል፡፡ ለርዕስ መምህራንና ለሱፐር ቫይዘሮች ደሞዝ 4,734 7,768 ብር ድረስ ይከፈላቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ከ5-7 ዓመት 6 ደረጃ ያድግ የነበረው አሁን ተሻሽሎ በሦስት ዓመት 7 ደረጃ ማደግ የሚቻል ሲሆን የርዕሳነ መምህራንና ሱፐር ቫይዘሮች ደረጃ ከ12 ወደ 14 እንዲያድግ ተደርጓል" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በሌላ በኩል ባለፈው ሁለት ሳምንታት የግል ት/ቤቶች መምህራን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ሥልጠናውን ተከታትሎ ያላጠናቀቀ በየትኛውም ት/ቤት እንደማያስተምር ማስጠንቀቂያ መስጠቱን የዜና ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "ሥልጠናው ለሁለት ቅዳሜና እሁድ በተከታታይ እንደሚሰጥ የተገለፀና ለሁለተኛ ሳምንት ትምህርቱ ቢሰጥም የሥልጠናው ዓላማ ግልጽ አይደለም" ይላሉ፡፡

በተለይ በአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የግል ት/ቤቶች የተውጣጡ መምህራን እንደሚሉት "ሥልጣናው ተጀመሮ የተጠናቀቀ ቢሆንም አሠልጣኝ ተብለው የመጡት ከመምህሩ እውቀት ያነሱ ከመሆናቸውም በላይ ዝግጅት አድርገው የማይመጡ በመሆኑ የሥልጠናው ዓላማ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ ተገደናል፡፡" ይላሉ "በተደጋጋሚ በሥልጠናው ላይ ይህንን ሥልጠና ያልተከታተለና ያላጠናቀቀ የትም ት/ቤት አያስተምርም!! እየተባለ የሚሰጠው ማስጠንቀቂ ምን ለማለት ፈልገው ነው? ምን አስበው ነው? እያልን እንድናስብ አድርጐናል" በማለት ይናገራሉ፡፡ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ በሚል ስም ለሁለት ሳምንት ቅዳሜና እሁድ ሥልጠናው ተሰጥቶ የተጠናቀቀ ቢሆንም "መምህራኑ ምንም አዲስ እውቀት ያልተገኘበት ሥልጠና እንደሆነ" ይናገራሉ፡፡

ሠልጣኝ መምህራኑ እንደሚሉት "ከተለያዩ ት/ቤቶች የተውጣጡ 750 መምህራንን በአንድ መጋዘን አጉሮ እቅድና ዝግጅት ባልተደረገበት የተሰጠው ሥልጠና ውጤታማ አልነበረም ብለውታል፡፡ አሠልጣኝ ተብለው የተመደቡት ዝግጅት ያላደረጉ ስለነበረ ክፍል ገብተው እያነበቡ ያስተምሩ ነበር" ሲሉ ተችተውታል፡፡ ሥልጠናው ከትላንት በስቲያ የተጠናቀቀ ሲሆን በተለይ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቢሮ ተወካይ ሥልጠናውን ለመዝጋት በመጡበት ዕለት ባደረጉት ንግግር "መምህራኑ የመሰልጠን ፍላጐት እንደሌላቸው ወቅሰው ሥልጠናው የዲሲፕሊን ጉድለት እንደነበረበት" ጠቅሰዋል ተብሎአል፡፡

መምህራኖቹ በበኩላቸው "የሥልጠናውን መዝጊያ ንግግር ሊያደርጉ የመጡት ኃላፊ የግል ት/ቤት አስተማሪውንም እንደ መንግስት ት/ቤት መምህር ለማስፈራራትና አንገት ለማስደፋት ሞክረው ነበር፡፡ መምህራኑ ሲናገሩ በማጨብጨባችን ጭብጨባ የፊልም ቤት ባህርይ ነው ብለው ያልተገባ ቃል ተናግረውናል፡፡ ጭብጨባ የውስጥ ስሜት መገለጫ በመሆኑ የመከልከል መብት እንደሌላቸው አስተምረናቸው ደጋግመን አጨብጭበናል፡፡" ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም መምህራኖቹ ስለሥልጠናው ሲናገሩ "ሥልጠናው በክረምት ወቅት በእቅድና በዝግጅት መደረግ ነበረበት፡፡ አሁን የመምህሩን የሥራና የዕረፍት ጊዜ ተሻምቷል፡፡ ሥልጠናው ትርጉም የሌለውና መምህሩን የራሳቸው ሎሌ ለማድረግ የታቀደ ነው፡፡" ሲሉ አጣጥለውታል፡፡ የመምህራን ማህበር ተጠሪዎችን ለማነጋገር ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡

# ከሰዉ ፖለቲካ የተፈጥሮን እናስቀድም

ሰለሞን ስዩም
era4st@yahoo.com

ባለሁባቸው የሕይወት ጊዜያት ከተፈጥሮ ጋር ስላለኝ የማይነጠል ቁርኝት ግንዛቤ እየጨመርኩ ሄጃለሁ፡፡ በአንፃራዊነት የተሻለ የተፈጥሮ ደህንነት ከነበረበት የህፃንነት ዕድሜዬ እስከ አሁን ድረስ ተፈጥሮ ሲሟሟ አይቻለሁ፡፡ ስመ-ጥሩ ግሪካዊ ፈላስፋ ፕላቶ ስለ አቲካ ተራራ መጎሳቆል ከአንድ ሰው ሰውነት መከዳት ጋር የያዘበት ሁኔታ ከጊዜዉ የቀደመ አስተሳሰብ የሚባለዉ አይነት ነበር፡፡ "አቲካ ታሞ ሰውነቱ የከዳው ሰው ይመስለኛል" ብሎ ነበር፡፡ በፕላቶ ዘመን ስለ አካባቢ ጥበቃና መጎሳቆል የሚወራው ባላቸው የካርቦን ኤሚሽን፣ ግሎባል ዋርሚንግ፣ ግሪን ሀውስ ጋስ እና አልትራ ቫዮሌት ረይስ እዉቀት አይመስለኝም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እያለሁ፣ እኔም ቢሆን ደመ ነፍሳዊ ተቆርቋነት እንዲሁም ለስነ ውበት የመጨነቅ ሁኔታ ነበረኝ፡፡ የትኛውም የተጎሳቆለ ቦታ ለዓይን ሲታይ አያስደስትም፡፡ የሆነ የመረበሽ ሁኔታ አለው፡፡ ለጭንቀት የሚደርግ ነዉ፡፡ ታዲያ በየማሳችን መሃል ያሉት ያገጠጡ ቦታዎች ቁጭት ይፈጥሩብኝ ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በስነ ህይወት ትምህርት ትርጉም መፍጠር ጀምሬ ኑሮ ስለ ጤና ነክ ጉዳዮች በማንሳት ከአከባቢ መራቆት ጋር አገናኝቼ እጨነቅ ነበር፡፡ እንግዲህ አልትራ ቫዮሌት ጨረር እንዳያርፍብኝ አብዝቼ እጨነቅ ነበር ማለት ነው፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ደህንነት መላላትና የብዝሃ ህይወት መጥፋት የጤና ችግር እንዳለው በዚህ ዘመን ይታወቃል፡፡ «ይህ የማንኛዉም ሰዉ የአከባቢ ጥበቃ አዉቀት አጨማመር ነዉ» ይላሉ ጉዳዩን የሚያጠኑ ምሁራን፡፡ የአካባቢ ደህንነት ተመራማሪዎች ለአካባቢ ጥበቃ የሚያነሳሳን የመጨረሻ ምክንያት የዓለም ዜግነት ጥያቄያችንን ለመመለስ የምናደርግ ጥረት ነው የሚል ነዉ፡፡ በእኔ እምነት ግን ከዚህ ደረጃም አንድ እርከን ከፍ ብለናል፡፡ በመሆኑም ከዓለም ነዋሪነት ጥያቄ ውጭም ዓለም በመጨረሻዎቹ የአደጋ ቀጠና ውስጥ የገባችበት የአካባቢ ደህንነት ሁኔታ በመከሰቱ "የሞት ሽረት" ደረጃ ላይ ነን ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም ከዚህ መስመር ያለፈ የአካባቢ መራቆት ከማይመለስበት ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ ያ ማለት ሞት ነዉ፤ ደግሞም ጅምላ ሞት ነዉ፡፡ የሰዉም፣ የእንስሳት ሁሉ፣ የእፀዋት ሁሉ ሞት፤ ህይወት የማይታይባት ምድርም ሙት ነት፡፡

ድሮ ድሮ፣ ልጅ ሳለሁ ከየትኛውም ሙያዬ በተጨማሪ የፖሊስ አጋዥ (Co-police) መሆን እመኝ ነበር፡፡ አሁን ብጠይቅ የፖሊስ አጋዥ ብሎ ነገር የለም ተባልኩ፡፡ በነገራችን ላይ በየመንገዱ የሚጣሉና የሚደባደቡ ሰዎችን ባየሁ ቁጥር ምኞቴ ሁሉ በጉልበቴ መገላገል አይደለም፡፡ ትንሽዬ የፖሊስ ሥልጠና ቢኖረኝና የፖሊስ አጋዥነት ሕጋዊ መታወቂያ ባገኝ በሕጋዊነቴ ብቻ እነዚህን ሰዎች ከአካል ጉዳት፣ ከህግ ፍርደኝነት ልገላግላቸው በቻልኩ፡፡ አሁን አሁን ግን ለሰዎች በጥቂቱም ቢሆን የሰው ፖሊስ አሏቸው፡፡ ለተፈጥሮ ግን ሰው ጠላቷ ሆነ፡፡ «ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ስር እናዉላለን» በማለትም ዳክረን ነበር፡፡ ተፈጥሮን ባሸነፍነው መጠን እንደምንሸነፍ አናዉቅም ነበር? አጥፍቶ የሚጠፋን ሰው በኛና ተፈጥሮ ላይ በምናደርሰው ጥፋት መካከል በሚፈጠረው ሁኔታ ጋር መመሰል ይችላል፡፡ ተፈጥሮን ባጠፋን መጠን እንጠፋለን፡፡ አሁን በማያቸው የተጎሳቆሉ ቦታዎች ሁሉ አይኔ ፀፀትን ይረጫል፡፡ እኔ ግን ሳስብ ጉዞዬን እዚህ ጋር እቆማለሁ፡፡ ወደ ጨለማ አልሄድም፡፡ እናንተን ይዤ ተፈጥሮን በመንከባከብ ራሴንም እንከባከባለሁ፡፡

የስነ ልቦና ባለሙያዎች ስኬት የአጋጣሚዎችና አጋጣሚዎችን የመጠቀም ቁርጥ ውሳኔ ነው የሚል ፍልስፍና ያራምዳሉ፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች የመጡልንን ሁኔታዎች አልተጠቀምንም፡፡ ለምሳሌ ሀገራችን ከበረሃ እስከ ውርጭ ድረስ የሚደርሱ የአየር ንብረት ካላቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ ነበረች፡፡ በዚህ ያልቀና የሉል ሀገር የለም፡፡ አሁን ግን በነዚህ መካከል ያሉትን ባጠቃላይ በረሃማነት ብቻውን እየያዘብን ነው፡፡ መንግስት ሌቦች ናቸዉ ከሚላቸዉ የመሬት ቸርቻሪዎችም በላይ፣ ከጥገኛ የሪል እስቴት አልሚዎችም በላይ፣ ከጨረቃ ቤቶችም በላይ መሬታችንን እየነጠቀን ያለዉ በረሃማነት ነዉ፡፡ ተፈጥሯዊዉን የስነ ህይወት ርቢ እንኳን እየነጠቀን ነዉ፡፡ ለማንኛው ሰዎች ያልፋሉ፣ አስተዳዳሪዎችም ያልፋሉ፣ ሕዝቦች ግን ቢያንስ ቢያንስ ቶሎ አያልፉም፡፡ ስለዚህ እኛ የምናልፍ ሰዎች ምን መልካም ነገር እናኑር? አንድ ሰው ለማበርከት ከወሰነ ለራሱ ይረካል፡፡ ስሙን ከመቃብር በላይ ይተዋል፣ለትውልድ አንድ ነገር ይተዋል ማለት ነው፡፡ ይህን የወሰነ ሰው ውስጡ ይጠነክራል፡፡ አቅመ ቢስነት ሆኖ ሲያመው የነበረው ምንም ያለማበርከት ታሪክ መትነን ይጀምራል፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነቱን የማበርከት ነገር በሰማን ቁጥር ጉዳዩን የአጋጣሚ ብቻ ሳይሆን የውሳኔም ጭምር በማድረግ ነገሮችን እንግፋበት፡፡

ከዓመታት ቀናት ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ከተፈጥሮ ጋር ነን፡፡ ለማንኛውም ያለንን ሁሉ ለተፈጥሮ እንክብካቤ መስዋዕትነት ለማቅረብ እንወስን፡፡ ተፈጥሮ ፖለቲካ ነው፡፡ ተፈጥሮ ኢኮኖሚ ነው፤ተፈጥሮ መዝናኛ ነው፤ ተፈጥሮ ማህበራዊ ነው፤ ከምንም በላይ ተፈጥሮ ህይወት ነው፡፡ ይህን ሳስብ ተፈጥሮን ወደ አቋሟ ለመመለስ የከፈልነዉ የሁሉም ነገር መስዋዕታችን ፍፁም እንዳልሆነ ስለምረዳ የሎሬት ፀጋዬን "የቴዎድሮስ ስንብት" ውስጥ ከተካተቱት ሀረጎች "ከሞከርነው ይልቅ ያልሞከርነው የሚቆጨኝ" ይታወሰኛል፡፡ ተፈጥሮን ለመንከባከብና ወደ ቀድሞ ቦታ ለመመለስ ሁሉን አላደረግንም፡፡ ይህም ያፅናናል እንጂ አይቆጨንም፡፡ ገና የምንከፍለው የምንሰዋው ቀሪ ነገር አለን ማለት ነው፡፡ እኛ በህይወት አለና፡፡ በመሆኑም ምንም ነገር ተስፋ አያስቆርጠንም፡፡ ቶማስ ኤዲሰን "እኔ ተስፋ አልቆርጥም፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ያልተሳካና የስህተት ሙከራዬ አንድ ርምጃ ወደ ፊት ነውና" ብሏል፡፡ ተፈጥሮን በተመለከተ ከተሰጠን (given) መቶኛ የማይሳኩልን / የስህተት/ ሙከራዎች ቢያንስ ብዙውን ተሳስተን ጨርሰናል፡፡ ብዙ ደግሞ ተምረንበታል፡፡ ስህተት ለሚማርበት ሰዉ እንደ ኩፍኝ ነው፡፡ እንዴ ከተሳሳተ ይወጣለታል፡፡ መልሶ ያንኑ አይሳሳትም፡፡ ስለዚህ በቀጣዮቹ ከተሰጡን መቶኛ ስህተቶች ዉስጥ አብዛኛዉን ተሳስተን በማጋመሳችን እንደ ከዚህ ቀደሙ አይበዛም፡፡አፈር ውኃ እና ደን በትስስር ከተጠበቁ ሠላም፣ደህንነት፣ጤና የሰው ልጅ ቀጣይነት ይቻላል፡፡ በዚህ ውስጥ አሻራችን ካለ በተፈጥሮ ውስጥ እኛ አለን፡፡

# ሕጋዊ የፍርድ ሂደትን ባልተከተለ ሁኔታ የታሰሩ ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ መኢአድ ጠየቀ

"አንዳች መረጃና ማስረጃ ሳይቀርብባቸው፤ተከላከሉ ሳይባሉና መከላከያቸውን ሳያሰሙ መቃወሚያቸውን ሳያቀርቡ ሕጋዊ የፍርድ ሂደትን ባልተከተለ ሁኔታ የተወሰነባቸውን የፍርድ ሂደት አጥብቀን እናወግዛለን! በአስቸኳይ እንዲፈቱም እንጠይቃለን!" ሲል መኢአድ አስታወቀ፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ይህንን ያስታወቀው ባለፈው ዓርብ ከሰዓት በኋላ በጽ/ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ነው፡፡

"በደቡብ ክልል የሚፈፀሙ አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንዲቆሙ እንጠይቃለን" በማለት ባወጣው ባለ ሁለት ገጽ መግለጫው እንደዘረዘረው፡- በደምባ ጎፋ ወረዳ ፍርድ ቤት አቶ ያዳ ማቶ ችሎት እንደቀረቡ ወዲያውኑ ስድስት ወር ተፈርዶባቸዋል፡፡ ሌሎች 8 ሰዎች በ10/07/2004 ዓ.ም ለፍርድ በቀጠሮ ላይ ናቸው፡፡ በዛላ ወረዳ፡- አቶ ካሳዬ ካሌሌ ለአንድ ወር በፖሊስ ጣቢያ ከታሰሩ በኋላ ዘጠኝ ወር ተፈርዶባቸዋል፡፡ በአይዳ ወረዳ 8 ሰዎች ለፍርድ በቀጠሮ ላይ ናቸው፡፡ በገዜ ጎፋ ወረዳ 12 ሰዎች ከ30/06/2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡ በዘንጋ ቀበሌ አስር አባላት በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ ደምቤ ቀበሌ ስምንት አመራሮች ለፍርድ ተቀጥረው ይገኛሉ፡፡ በጋይላ ማሴቦ ቀበሌ ስምንት አመራሮች በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡ በቦርዳ ቀበሌ አስራ አንድ አባላት ታስረው ይገኛሉ፡፡የሀሰት ክስ በመመስረት፤ከሳሽም፤ምስክርም ራሳቸው የመንግሥት ካድሬዎች ሆነው፤ለተከሳሾቹ የመከላከልም ሆነ የእምነት ክህደት ቃል የመስጠት መብታቸው ሳይከበርላቸው ከዘጠኝ ወር እስከ ስድስት ወር የተፈረደባቸዉ ሲሆን የተቀሩትም ለፍርድ በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ ክሱ "ጸረ-ልማት" የሚል በመሆኑ ሐሳብን የመግለጽ መብታቸውን የነፈገ ነዉ፡፡ እዚህ በእስር ላይ የሚገኙት የተመሰከረላቸውና ስነ-ምግባር ያላቸው ዜጎች ሲሆኑ፤ኢህአዴግ እነዚህን ዜጎች "ጸረ-ልማት ናቸው ለማለት የሞራል ብቃት ሊኖረው ከቶውንም አይችልም" በማለት ያብራራል፡፡

መግለጫው በመጨረሻም ሲደመድም "በመሆኑም አምባገነናዊው የኢህአዴግ መንግሥት በፓርቲያችን አባላትና ደጋፊዎች ላይ አጠናክሮ የያዘውን የጅምላ እስርና አግባብነት የሌለውን የፍርድ ሂደት ተከትሎ የተወሰነባቸውን ውሳኔ በአስቸኳይ እንዲያነሳ እንጠይቃለን፡፡ ... አስከፊ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብት ረገጣ እንዲያቆምና የፖለቲካ እስረኞችን እንዲፈታ በድጋሚ እንጠይቃለን፡፡ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ይህንን የገዢውን ፓርቲ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ረገጣ የጅምላ እስራት አፈናና ጭፍጨፋ እንዲያወግዝ እንዲሁም በመንግሥት ላይ ጫና እንዲፈጥር እንጠይቃለን፡፡" ሲል ጥሪውን በማቅረብ ነዉ፡፡

በተያያዘ ዜና መኢአድ በዚሁ ዕለት "መንግሥስት ከድርጊቱ ሊታቀብ ይገባል" በሚል ርዕስ ባወጣው ሌላ ባለ አራት ገጽ መግለጫው "በደቡብ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ እጅግ የከፋ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊት በዜጎች ላይ እየፈፀመ ነው፡፡" ሲል ከሷል፡፡ መኢአድ በመግላጫው ላይ እንደዘረዘረው፡- "በቤንች ማጂ ዞን በጉራፉርዳ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሃያ ሁለት ቀበሌዎች ከሰባ ስምንት ሺህ (78,000) በላይ ሕዝብ እንደሚኖር ይታወቃል፡፡ ይህም ሕዝብ ከሰሜኑ የአማራ ክልል ወደ ደቡብ ክልል በተለያየ ጊዜ በንግድና በተለያየ የሥራ ሁኔታ አማካኝነት በመውረድ ኑሮውን ከአስራ ሁለትና ከአስራ አምስት ዓመት በላይ በዚያው ያደረገ ሕዝብ ነው፡፡

ሕጋዊ በሆነ መንገድ ከመንግሥት መሬት ተሰጥቷቸው በግብርና ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች ቤተሰብ የመሰረቱ፣ልጆች ያፈሩ፣ሀብት ያፈሩ የተለያዩ ተቋማትን ማለትም ቀበሌዎችን፣ቤተክርስቲያናትን ወዘተ በመመስረት ማህበራዊ ኑሮን መሥርተው የሚኖሩ ዜጎች ናቸው፡፡ የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በሰጡት ቀጠተኛ ትእዛዝ እነዚህ ዜጎች ክልሉን ለቀው እንዲወጡ እየተደረገ መሆኑን የጠቆመዉ መኢአድ የቀሩትም ያለሙትን መሬትና የተከሉትን ቋሚ ንብረት ያለአግባብ እየተነጠቁ ነው፡፡ መኢአድ በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ቀጥታ ጥእዛዝ የሆነዉን የዜግነት ክብርን የሚያዋርድ፤የሰብአዊ መብት ረገጣ በመሆኑ እንዲቆም በተደጋጋሚ ጠይቋል፡፡ በርካታ ዜጎችም የሚፈጸምባቸውን ግፍና በደል ሽሽት ወደ ጋምቤላ ክልል በመሰደድ ላይ ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ኃላፊዎች ለድርጊታቸው መነሻ የሆናቸውን ምክንያት ለሕዝቡ ሲገልጹ ቂም በቀል መሆኑን ይናገራሉ፡፡

በ1997 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም በተደረገው አገር አቀፍ ምርጫ «መሬት የሰጣችሁን መንግሥት መምረጥ ሲገባችሁ ተቃዋሚን መረጣችሁ» የሚል ሲሆን ለቀጣይ እንዳይደገም መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም መነሻነት ሕዝቡን በሕገወጥነት ፈርጆ ከክልሉ ማሰናበት እንዲቻል ከቀበሌ ካድሬዎች ጀምሮ እስከ ርዕሰ መስተዳድሩ ድረስ በርካታ ምክክሮች እንደተደረጉ ሰነዶች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም ከየካቲት 28/2004 ዓ.ም ጀምሮ አንድ መቶ ሃምሳ አባወራዎች ከየቤታቸው ሌሎች ሰባ ሶስት የሚሆኑ አባወራዎች ደግሞ ከወፍጮ ቤቶችና ከእርሻ ቦታዎች ላይ በፖሊስና በታጣቂዎች ታፍሰው በአይሱዙ መኪና ተጭነው ወዳልታወቀ ቦታ ተወስደዋል፡፡ በለቱ ሁለት መቶ ሃያ ሦስት አባወራዎች የታፈሱ ሲሆን አርባ ስምንቱ ከሚኖሩበት አካባቢ ታፍሰው ከተወሰዱ ከሁለት ቀን በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ብሔራዊ ሙዚየም አካባቢ ሲገኙ ሌሎች ሃምሳ የሚሆኑ አባወራዎችን ሌሊት ወደ አዲስ አበባ እንደገቡ በፖሊስ ተይዘው በአራዳ ክፍለ ከተማ ውስጥ በሚገኝ በአንድ መጋዘን ውስጥ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሆኖም በሦስተኛው ቀን በፌደራል ፖሊስ ተከበው ወደ መጡበት ክልል ተመልሰው በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ በጅምላ ታስረው ይገኛሉ፡፡ ወደ አዲስ አበባ ያልገቡትን የት እንደደረሱ ለማወቅ መኢአድ ክትትል እያደረገ እንደሚገኝ በመግለጫዉ ተጠቁሟል፡፡

መግለጫው በመቀጠልም ሲዘረዝር "መንግሥት... አፈሳ ሲያካሂድ በከፍተኛ ድብደባ እንግልትና ወከባ በመሆኑ ምክንያት የእነዚህ አባወራ ቤተሰቦች በከባድ ፍርሃትና ጭንቀት ውስጥ ወድቀዋል፡፡ በርካታ አባወራዎችም ... ተደብቀው ይገኛሉ፡፡ አባወራዎቹ ታፍሰው ወደ አዲስ አበባና ወደ ተለያየ ቦታ ሲወሰዱ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው በዚያው በቤንች ማጂ ዞን በጉራፉርዳ ወረዳ እንዲቀሩ በመደረጉ ቤተሰቦች አባቶቻቸውና ባሎቻቸው የት እንደ ደረሱ ለማወቅ እንኳን አልቻሉም፡፡ መንግሥት በዚህ ሳያበቃ "ባሎቻችሁ ከወጡ እናንተ ምን ትሰራላችሁ? በአስቸኳይ ውጡ" በማለት ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን በማሳቀቅና በማስፈራራት ላይ ይገኛል፡፡ ከጅምሩ "ከመንግሥት የተረከብኩትን መሬት በፈቃዴ መልሼ ለመንግሥት አስረክቤአለሁ፤ይህንንም በፊርማዬ አረጋግጣለሁ" የሚል አስገዳጅ ሰነድ እንዲፈርሙ ተገደዋል፡፡ አንፈርምም ያሉት እስከ አሁን በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡ ተገደው እንዲፈርሙ የተደረጉት እስከ መጋቢት አስር ድረስ ንብረታቸውን ሸጠው እንዲወጡ የወረዳው ፍርድ ቤት አቃቤ-ሕግ ኃላፊ እና የወረዳው የጽ/ቤት ኃላፊ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል፡፡ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ክልሉን ጥሎ በማይወጣ ማንኛውም ግለሰብ ላይ ኃይል በመጠቀም ርምጃ እንደሚወሰዱም ደጋግመው በማሳሰብ ለሕዝብ ያላቸውን ንቀት ገልፀዋል፡፡ ይህ ተግባር ለሕዝብ ቆሜአለሁ ከሚል መንግሥት የማይጠበቅ ኢ-ሰብአዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊት በመሆኑ መኢአድ መንግሥት ከደርጊቱ እንዲታቀብ ይጠይቃል" ብሏል፡፡ መግለጫው በማየያዝም የአሠራሩን ኢፍትሃዊነት ሲዘረዝር "በህጋዊ መንገድ ከመንግሥት መሬት የተረከቡ ዜጎችን ሕገወጦች በማለት መፈረጅ ህጋዊ ግብር ከፋይ ዜጎችን አናውቃችሁም፤ በማለት ቀጣዩን ግብር እንዳይከፍሉ መከልከል፣ እንዲሁም ሕጋዊ ሰነዶችን በመደበቅና በማጥፋት በህገ ወጥነት መወንጀል መታወቂያ መንጠቅና መቅደድ፤ ያለመታወቂያ ሲንቀሳቀሱ እንደ ወንጀለኛ መያዝ፣የተጠመዱ በሬዎችን ፈትቶ መልቀቅ፣ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቤት መበርበር፣በአስቸኳይ ካልወጣችሁ በሽብርተኝነት እንከሳችኋለን በማለት ማስፈራራት፣ደን ጨፍጭፋችኋል፤አውድማችኋል ብለን እንከሳችኋለን በማለት ማስፈራራት ፤እስራት፣በታጣቂዎች የሚፈጽም ድብደባ፣ማሰደድ /ከአካባቢው ማስወጣት/፣ሴቶችንና ህጻናትን ማጎሳቆል፤ማስፈራራትና ዛቻ መፈጸም፣ንብረቶቻቸውን በተራ ዋጋ እንዲሸጡ ማስገደድ፣ በመሬት ላይ የተከሏቸውን እንደ ቡና ፓፓያ ወዘተ የመሳሰሉ ቋሚ ተክሎችን መውረስ . . . በማለት አግባብ አለመሆኑን ያብራራል፡፡መግለጫው በመጨረሻም "መንግሥት በክልሉ ውስጥ የሚፈጽማቸው የሰብአዊመብት ጥሰቶች ሲሆኑ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት / መኢአድ/ እነዚህን መንግሥት የሚፈጽማቸውን የመብት ጥሰቶች እንዲያቆሙ ይጠይቃል፡፡ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም ክልል የመኖር፤ሃብት የማፍራት፤የዜግነት መብትን መንግሥት አሳጥቷል፤በአጠቃላይ የዜግነትን ክብር አዋርዷል፡፡ ሰርተውና፤ሀብት አፍርተው፤እራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን በአግባቡ የሚመሩና የሚመግቡ ዜጎችን በማፈናቀልና በማሰደድ መንግሥት ራሱ እነዚህን ዜጎች ለተረጂነትና ለረሃብ እንዲሁም ለመጠለያ እጦት አጋልጧቸዋል፡፡ ተለዋጭ የመኖሪያ ቦታና የእርሻ ቦታ ሳይሰጣቸው ዜጎች ወደ ባዕዳን አገር ተሰደዋል፤ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለዋል፤ ተለዋጭ የመኖሪያና የርሻ ቦታ ሳይሰጣቸው እንደ ባእዳን አገር ሕዝብ ዜጎች ተሰደዋል፤ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለዋል፡፡ ያለሙት ቦታ ለሌላ ለልማት ይፈለጋል ቢባል እንኳን፤እነዚህ ዜጎች በህጋዊ መንገድ ከመንግሥት ተረክበው ያለሙትና፤ሀብት ያፈሩበት መሬት በመሆኑ ምክንያት ላፈሩት ሀብትና ንብረት እንዲሁም ለተከሏቸው ቋሚ ተክሎች ተገቢው ካሳ ሊከፈላቸው በተገባ ነበር፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ እነዚህን ዜጎች በማፈናቀል መንግሥት ሕገወጥ ሥራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ መንግሥት እየተከተለ ካለው ህገ-ወጥ አካሄድ እንዲታቀብ ይጠይቃል፡፡ ታፍሰው ፤ከቤተ-ሰቦቻቸው ተለይተው በአዲስ አበባና በሌሎች ክልሎች እንዲበተኑ የተደረጉ ሁለት መቶ ሃያ ሦስት አባወራዎች አሁን በጅምላ ታስረው ከሚገኙበት ወደ መኖሪያ ቀያቸው አንዲመለሱ፤ከቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉና ሠላማዊ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡

"ዛፍ አድርቃችኋል" ተብለው በሐሰት ተከሰው በዞኑ ፖሊስ መምሪያ በእስር ላይ የሚገኙት ሰላሳ ስድስት አባወራዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ መኢአድ ይጠይቃል፡፡ እነዚህ ሰዎች ውጡ ተብለው አንወጣም ያሉና በአስገዳጁ ቅጽ ላይ አንፈርምም ያሉ ሲሆን በእነዚህ ዜጎች ላይ የተጀመረው የሐሰት ክስ እና እጅ ጥምዘዛ እንዲቆም እንጠይቃለን፡፡

መረጃ አውጥታችኋል ተብለው ከየቤታቸው ተየዘው የታሰሩ አስራ ስድስት አባወራዎችም እንዲፈቱ እንጠይቃለን፡፡ መንግሥት የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዲያከብር እንጠይቃለን፡፡ መንግሥት የዜጎችን ዜግነታዊ ክብር እንዲያከብር እንጠይቃለን" በማለት ጥሪውን በማቅረብ ይደመድማል፡፡

በፓርቲው ጽ/ቤት መግለጫውን ለጋዜጠኞች የሰጡት የፓርቲው ተ/ም/ፕ የሆኑት አቶ ወንድምአገኝ ደነቀ የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚና የደቡብ ቀጠና ኃላፊ የሆኑት አቶ እንድርያስ ኤሮ የፓርቲው ሕዝብ ግንኙነት ም/ኃላፊ የሆኑት አቶ ጌታቸው አበበ ናቸው፡፡ ጋዜጠኞች የተለያዩ ጥያቄዎችን ያነሱ ሲሆን በተለይ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ «ነዋሪዎቹ ከአካባቢው እንዲባረሩ የክልሉ ፕሬዝዳንት በቀጥታ ማዘዛቸውን ምን ማስረጃ አላችሁ?» የሚል ይገኝበታል፡፡ አመራሮቹ ሲመልሱ "ላወጣነው መግለጫም ይሁን ለምንናገረው ሁሉ መረጃው በእጃችን ይገኛል፡፡ የክልሉ ፕሬዝዳንት ከሰሜን አማራ ክልል የመጡትን ከአካባቢው አስወጡ ብለው በጽሑፍ ያዘዙበት ደብዳቤ ቀሪ በእጃችን ይገኛል፡፡ በስልክ ስንጠይቃቸው ተፈናቃዮችን መንግሥት አያውቃቸውም፡፡ እናንተ ማን ነው ሰብአዊ መብት ተከራካሪ ያደረጋችሁ? ብለውናል፡፡ መሬቴን በገዛ ፍቃዴ ለቅቄ ሄጃለሁ እያላችሁ ፈርሙ እያሉ እያስገደዱ አስፈርመዋቸዋል፡፡ አንድ ትልቅ ሰንጋ በብር 700 እንዲሸጡ ተደርገዋል፡፡ ንብረታቸውን በርካሽ እየሸጡ እንዲወጡ ተገደዋል" ሲሉ መልሰዋል፡፡

# ኢ.መማ የኢትዮጵያን . . .

ከገፅ 13 የዞረ

እንዲተኙ ራሩላቸው፡፡ ከጥንት አባቶቻችን የወረስነው የመቻቻልና የመተሳሰብ መንፈስ ዛሬ በተነሱ አምባገነን ገዢዎቻችን ሊሸረሸር አይገባውም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደማንጨካከን ዓለም ያውቃናል፡፡ እንኳንስ ለራሳችን ወገን ለባዕዳንም ክብር የምንሰጥ ነን፡፡

ይድረስ ለተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን መምህራን

ኢ.መማ የአገሪቱን መምህራን በመወከል የመታገል አቅም ባላቸው አመራሮች እንዳልተዋቀረ ይገባናል፡፡ አልፎ አልፎ እንኳን ቢኖሩ የኢህአዴግ ሰለባ ነው የሚሆኑት፡፡ በቅርቡ በጎንደር አካባቢ መምህራን የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸው እስከ ዛሬም ለእስርና ለእንግልት የተዳረጉ መምህራን እንዳሉ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ አስነብባናለች፡፡ ይሁን እንጂ በፍርሃት ልጓም ተሸብበንና እጃችንን አጣምረን አንመለከትም፡፡ ይሄ ጥሩንባ የተነፋለት የደመወዝ ማሻሻያ እኛንና ሞያውን የውርደት ሸማ የሚያከናንበን ነው፡፡ ማህበሩም ይሁዳ ክርስቶስን አሳልፎ እንደሰጠ ለውርደት አሳልፎ ሰጥቶናል፡፡ እኛ ግን ሕገ መንግስታዊ መብታችንን ተጠቅመን በሰላማዊ መንገድ ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡

ዛሬ በአገራችን እየተከሰተ ያለው የኑሮ ውድነት ከቀናትም ባጠረ በሰዓታት ውስጥ ሲንር እያስተዋልን ነው፡፡ ጠዋት የገዛነው እቃ ከሰዓት በብዙ ፐርሰንት ይጨምራል፡፡ የእኛ ኑሮውን ለመቋቋም አለመቻል በትምህርት አሰጣጡና በጥራቱ ላይ የሚያሳድረውን ጫና የኢህአዴግ ሹማምንት ለምን መገንዘብ እንዳልቻሉ ግራ ያጋባል፡፡ ከአንድ ወር በፊት የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በአገራቸው የትምህርት እንቅስቃሴውን ለማሻሻል አበረታች እቅድ ለነደፉ ስቴቶች እስከ 5 ቢሊዮን ዶላር መመደባቸው አስተዋይና አርቆ አሳቢ መሪ መሆናቸው የሚመሰክር ነው፡፡ ምናልባት ፕሬዝዳቱ ይህን ዓይነቱን አበረታች እርምጃ የወሰዱት "በት/ቤት ውስጥ በጣም ተፈላጊው ሰው መምህሩ ነው፡፡" ሲል የሩሲያዊ ሶሻሊስት መሪ ቪላድሚር ኢሊያኖቭ ሌኒን ባንድ ወቅት የተናገረውን ከግምት አስገብተው ሊሆን ይችላል፡፡ የአገራችን መሪዎች ይህንን ለመኮረጅ ለምን ተሳናቸው? በፓርላማ የሚፀድቁ አሳሪ ህጎችን ከእንግሊዝ ከአሜሪካ፣ ካደጉ አገራት የቀዳነው ነው ይሉን የለም እንዴ? ለተንኮል ውጥናቸው ማሳኪያ ብቻ የሚመቻቸውን የሚኮርጅ ከሆነ አገር እየመሩ ሣይሆን እያፈረሱ ነው፡፡

ውድ መምህራን የነገይቱን ኢትዮጵያ የሚረከብን ትውልድ ማፍራት የሚቻለው በዛሬው መምህር እንደሆነ ለገዢዎቻችን የተሰወረ አይደለም፡፡ የመምህሩ የኢኮኖሚ ጥያቄ ከአገሪቱ አቅም አንፃር ምላሽ ከተሰጠው የዕውቀት ዘር ለመዝራት እጁን አያሳጥርም፡፡ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ ይተጋል፡፡ የተሻለ ትውልድ ለመፍጠር ይፍጨረጨራል፡፡ በርሃብና በእርዛት ውስጥ ሆኖ እየተሸማቀቀና ትንፋሽ እያጠረው አጥጋቢ ተግባር ይከውናል ብሎ ማሰብ ራስን መሸንገል ነው፡፡ በጩኸትና በመፈክር ድርደራ የትምህርት ጥራት አይመጣም፤ አገር አታድግም አትለወጥም፡፡ አንድ ሥልጣን የጨበጠ መንግስት የመጀመሪያ ተግባሩ የዜጎችን የኑሮ አቅም ማጎልበት ነው፡፡ ከአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ሕዝቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚ ማድረግ ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ ጠቅላይ ሚ/ር መለስ በየዓመቱ የፓርላማ ዲስኩራቸው የአገሪቱ ኢኮኖሚ በ11% አደገ እያሉን 60 እና 70 ብር የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ እውን ፍትሃዊ አሰራር ነውን? ብቁና ተመራማሪ ትውልድ ከማፍራት አንፃር የአገሪቱን የትምህርት ተቋማት (Educational sections) በበላይነት የሚመራው ትምህርት ሚኒስቴር በዚህ አካሄድ ትምህርት ከታቀደለት ግብ ይደርሳል ብሎ ሊያስብ አይገባም፡፡ የመምህራን ችግሮች ባልተፈቱበትና ጥያቄዎቻቸው ተገቢውን ምላሽ ባላገኙበት ሁኔታ ከቶም ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ዛሬ በመላ አጋሪቱ በሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች የሚማሩት የነማን ልጆች ናቸው? የድሃው ኢትዮጵያዊ ልጅ አይደለምን? በየደረጃው የሚገኙ ሹማምንቶችና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ጭምር ልጆቻቸውን የት ነው የሚያስተምሩት? አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ቻይና ወደ አገር ቤት ስንመጣ ዳግም ሳንፎርድ፣ ስኩል ኦፍ ቱሞሮው፣ ማጂክ ካርፔት፣ ራዲካል አካዳሚ ምን በወጣቸውና ከድሃው ልጅ ጋር መንግሥት ት/ቤት ያስተምሩ? ምርጥ ምርጡን ለኢህአዴግ ሹማምንት!!! ምን አልባት የመምህራን የኑሮ ችግርና ጉስቁልና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የእነሱን ልጆች ላይነካቸው ስለሚችል ይሆናል በሞራላችን ላይ የተረማመዱት፡፡

ውድ መምህራን ዛሬም ቢሆን ጥያቄችን አልተመለሰም፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር ለመምህራን ደመወዝ በአካፋ ዝቆ እንደጨመረ ነገር በብዙሃን መገናኛ አዋጅ ያስነገረበት ገንዘብ ኪሳችን ከሚገባ የእኛ ኑሮ ተገድቦ ለአባይ ግድብ ቢውል ይመረጣል፡፡ አፋችንን ለማስያዝ በማሰብ እጅግ በፈጠነ ውሳኔ የተወረወረችልንን 60 እና 70 ብር ከመጋቢት ወር ጀምሮ እንድንወስዳት መለፈፉ ከመቼውም በበለጠ የማስተማር ሞራላችንን ያደቀቀ ነው፡፡ እኛም ዜጋ መሆናችን እስኪረጋገጥ ትግላችን ይቀጥላል "አሉታ ኮንቱኑዋ!"

መምህር የለውጥ ሐዋርያ ነው!

## ዜና

# የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ ላይ የፈፀመው ጥቃት የትኩረት ማስቀየሻ ነው ተባለ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ ላይ የፈፀመው ጥቃት የትኩረት ማስቀየሻ ነው ተባለ፡፡

መጋቢት 5 ቀን 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት 18 ኪ.ሜ ወደ ኤርትራ ድንበር በመግባት ጥቃት መፈፀሙን ገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ቃል አቀባይ አቶ ሽመልስ ከማል ወታደራዊ ርምጃ የተወሰደባቸው ሦስት ቦታዎች ሲሆኑ የኤርትራ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት ተቃዋሚ አማፅያንን የሚያሰለጥንበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመግለጫው አያይዞም በጥር ወር በአፋር ጠረፋማ አካባቢ ለደረሰው የ5 ቱሪስቶች ሞትና የሁለት ጀርመናውያንና ሌሎች ኢትዮጵያውያን መታገትም ከዚሁ አካባቢ በሚነሱ ከመሆኑ አብራርቷል፡፡

ኤርትራ መንግሥት በበኩሉ ጥቃቱ በደረሰ በሁለት ቀናት ውስጥ ባወጣው መግለጫ "በወቅቱም ለማሳወቅ እንደሞከርነው ጉዳዩን ከሞቱትና ከታገቱት ቱሪስቶች ጋር ማገናኘቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቱን ለማሳመን ከመምከር አያልፍም" ብሏል፡፡ የኤርትራ መንግሥት አዲስ አበባ ከዚህ በፊትም ጥቃቶችን እንደ ፈፀመችብኝ ብገለፅም 70,000 ሰዎችን ከበላው የ1990-1992 ዓ.ም ጦርነት በኋላ ግን አዲስ አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቃት መፈፀሟን አምናለች፡፡

የኤርትራ መንግሥት ጉዳዩን እንደቁምነገር እንደማይገልፀው ቢያስታውቁም አቶ ሽመልስ በበኩላቸው "የኤርትራ መንግሥት ጥቃት ለመሰንዘር የሚችልበት አቋም የሌለው ሲሆን ያን ካደረገ ከፍተኛ ርምጃ ይወሰድበታል" ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በሌላ በኩል ሁኔታው ወደ ለየለት ጦርነት ይሸጋገር ይሆን የሚሉ አስተያየቶች የሚደመጡ ሲሆን ሪቻርድ ላፍ የተባሉ ፀሐፊ "ኢትዮጵያ የአስመራውን መንግሥት ለመገልበጥ የማትጠቀመው ዘዴ የለም፤ ነገር ግን ሙሉ ጦርነት የማይታሰብ ነው፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ግጭቶች ግን ሌላ ጊዜም መከሰቱን አምናለሁ፡፡ ሲሉ አስፍረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን አክራሪ እስላማዊዎችን በሶማሊየ እየረዳ የእጅ አዙር ጦርነት አካሂዷል በሚል የሚከሰው ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ኤርትራ ላይ ማዕቀብ እንደጣለባት ይታወሳል፡፡ ኤርትራ ጉዳዩን የፈጠራ ወሬ ነው ብትልም የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ጉረቤቶቿ ፈፅሞ የማያምኗት አገር ሲሉ ይተቿታል፡፡ በሌላ መልኩ ፒተር ጉድስፒድ የተባሉ ተንታኝ "የአፍሪካዋ ሰሜን ኮሪያ" የሚል ቅፅል ስም እንደሰጧት ተዘግቧል፡፡

ኒዮርክ ታይምስ የአቶ ሽመልስ ከማል ዘገባ ላይ ተመስርቶ ባወጣው ሪፖርት፣ኢትዮጵየ ፈጽምኩት ስለምትለው ጥቃት ምንም ዓይነት መረጃ እንደሌለ ያትታል፡፡

እንደሚታወቀው የኢሳያስ አገዛዝን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመጨረስ የመለስ አገዛዝ በኤርትራ ላይ ጠደቀት እንዲሰነዝር፣በተለይም እንደ አይጋ ፎረም ያሉ አክራሪ የአገዛዙ ደጋፊዎች ከፈተኛ ግፊተ ሲያደርጉ እንደነበር ይታወቃል፡፡

እንደዚያም ሆኖ ግን፣በርካታ ነባር የተግራይ ጀነራሎችን በማባረር፣በሕወሓት ውስጥ ያሉ ሊቀናቀኗቸው የሚችሉ የቀድሞ የሕወሓት አመራር አባላትን በጡረታ በመሸኘት፣ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ በማድረግ እና ነባር ቦዲጋርዶቻቸውን በመቀየር እራሳቸውን ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ ያደረጉት አቶ መለስ ዜናዊ፣የነ አይጋ ፎረምን ጠሪ በአደባባይ በማጣጣል ከሻዕቢያ ጋር ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ፣በማንኛውም ጊዜና ቦታ፣በማንም አደራዳሪነት ለመወያየት ዝግጁ እንደሆኑ በሚቆጣሩት ፓርላማ መግለጻቸው በስፋት ተዘግቧል፡፡ ሆኖም ይህ አሁን መከሰቱ የትኩረት ማስቀየሻ እንደሆነ የሚናገሩ አስተያየት ሰጪዎችም እንዳሉ ታውቋል፡፡ ሆኖም ይህ አሁን መከሰቱ የትኩረት ማስቀየሻ እንደሆነ የሚናገሩ አስተያየት ሰጪዎችችም በርካታ ናቸዉ፡፡

ይህ የአቶ መለስ ከሻዕቢያ ጋር ለመደራደር ያላቸው ፍላጎትና ውሳኔ፣ውስጥ ውስጡን በበርካታ የሕወሓት አባላትና ደጋፊዎች ዘንድ ማጉረምረምና ተቃውሞ ማስነሳቱን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ፡፡

ቃል አቀባዩ አቶ ሽመልስ ከማል "ኢትዮጰየ አደረሰች" የሚሉት ጥቃት ይህ ውስጥ ውስጡን በሕወሓቶች የተነሳውን ተቃውሞ ለማዳፈን እና አቶ መለስ በሻዕቢየ ላይ ጠንካራ እንደሆኑ ለማሳየት ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ የፈጠሪ ተረትና ውሸት እንጂ ምንም ዓይነት ጥቃት አቶ መለስ በኤርትራ ላይ እንዳላደረጉ የሚናገሩም አሉ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢህአዴግ አገዛዝ የሚቀጠለው ሳየንት በኳታር አደራዳሪነት በጀርመን አገር ኤርትራ መንግሥት ጋር ለድርድር እንደሚቀመጥ ሩባን ሳባ የተሰኘው የኤርትራውያን ድህረ ገጽ ዘገበ፡፡

አደራዳሪዎቹ ለውይይት መነሻ እንዲሆን ለሁለቱም አገሮች አምስት ነጥብ የያዘ ሰነድ አቅርበዋል፡፡ አምስቱ ነጥቦች

1. ኳታር የአሰብን ወደብ ለ20 ዓመታት እንድትከራይ፣ኢትዮጵያም ወደቡን እንድትጠቀም
2. በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ድንበር እንዲወሰን ኢትዮጵያ ቁርጠኝነት እንድታሳይ ከምትቆጣጠራቸው የኤርትራ ግዛቶች ለቃ አንድትወጣና ባድመን ለኤርትራ እንድታስረክብ
3. ሁለቱም አገሮች ማህበረሰባዊ ግንኙነቶችን እንዲጀምሩና እንዲያጠናክሩ
4. ሁለቱም አገሮች የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ግንኙቶችን እንዲጀምሩና እንዲያጠናክሩ
5. በባድመ ጦርነት ወቅት የተጎዱ ወገኖች ካሳ እንዲከፈላቸው

የሚሉት ናቸው፡፡

---

# ሙስና ! . . .

ከገፅ 3 የዞረ

የሚለከፈው ሕዝብ በደንብ ያውቃል። ከነአቶ ስብሀት ነጋ እንዲነግረው አይፈልግም!

እነ አቶ መለስ ዘናዊ፤ ስብሀት ነጋ፤ በረከት ስምንና መሰሎቻቸው ስለ-ሙስና መጮሀቸው በጎ ጎን ሊኖረው ይችላል። እንደዚህ ከሆነ ልንተባበራቸው ይገባናል (ከኔ ጀምሮ!) ሙስናን ያጠኑ ምሁራንና በአንዳንድ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩትንና ጥናት የሚያደርጉትን ጨምሮ - ለምሳሌ የዓለም ባንክ ተመራማሪዎች- በኢኮኖሚና የፖለቲካ ጠለፋን መሠረት ያደረገ ሙስና የአሸበሪነት ጠባይ እንዳለው፤ በዚህም የተነሳ ተሰባሪ እንደሆነ ጽፈዋል፤ ተገንዝበዋል።(በንግሊዝኛው Oligarchic corruption is unstable by its nature and violent as well የሚባለው ነው።) በኢትዮያ ላይ የተከሰተው የጠላፊ ሙስና የከፋና ለብዙ ዓመታት መቆያቱ የራሱ መግልጫዎች ቢኖሩትም፤ ሲበተን የሚያስከተላቸው መዘዞች ሕዝብን የሚያጫርስ፤ ሀብትንም የሚደመሥስ፤ አገርንም የሚያፈርስ ሊሆን ይችላል። እንግድህ እነ አቶ መለስ ዘናዊ፤ ስብሀት ነጋ፤ በረከት ስሞንና በተለይም ኢህአደግን ተጠግተው የከበሩ ግለሰቦችና ቡድኖች፤ ሙስናው በጣም ገምቶ መሆኑንና አደጋው ታይቷቸው፤አደጋው ደርሶ ሁሉንም ጠራርጎ፤ አገርንም አፍርሶ ከመሄዱ በፊት መላ ለመምታት ከሆነ፤ ሊበረታቱ ይገባቸዋል። በሙስና ላይ በሚደረገው ጦርነት ላይ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የሲቪክ ማህበራት፤ የረድኤት ድርጅቶች፤ በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊተባበራቸው ይገባል፤ እንደሚተባበራቸውም እርግጠኛ ነኝ። ምንም እንኳ አቶ መለስ አሁን ጠቅልለው የያዙት የፖለቲካ ሥልጣን የፈለጉትን እንዲፈጽሙ (እንዲሠሩ) ሊያደርጋቸው ቢችልም፤ እንደዚህ ያለውን የጠነባ ሙስና ለመታገል፤ ከፓርቲ አባሎቻቸው ያለመተባበር እምቢተኝነት (resistance) የሚጋጥማቸው መሆኑ ስለማይቀር ትብብሩን ከኢሕአዴግ አባላት ሳይሆን ከተቃዋሚ ድርጅቶች፤ ከሲቪክ ማህበራት፤ ከእርዳታ ለጋሾችና በተለይም ከኢትዮጵያ ሕዝብ መሆን አለበት። ይህ ትብብር እንዲገኝ በተለይ አቶ መለስ ዘናዊ በዩን መቅደድ ይችላሉ። ከነዚህም መካከል አንደኛው በኢትያጵያ ተንዘራፍቶ ያለው ሙስና ከፍተኛ ፖሊቲካዊ ሙስና (state capture) መሆኑን መገንዘብና ከላይ ሆነው መርዙን የሚረጭቱን እባቦች እራስ-እራሳቸውን ለማለት ቁርጠኛ ሆኖ መነሳትና መንገዱን በምሳሌነት ማሳየት ነው።[Recognizing the existence of large-scale and systemic state capture, that this state capture type of corruption is the root of widespread corruption, and that it is has undermined the country's potential transition communism to a market economy is paramount and a step in the right direction. Acknowledging that, in Ethiopia today, that it is the EPRDF's ethnic parties and their regional kingmakers who are appropriating state and public assets and who are systematically plundering the country's resources, who are expanding their political and financial power, influence and ability to employ their relatives and party cronies at the expense of the country, and who are promoting the personal and corporate interests of the political and economic elites would be a good beginning. Recognizing this fact helps us to be on the same page and allows us to collaborate in designing the methods of fighting the corruption scourge. ]

ሁለተኛው፤አቶ ስብሀት ነጋ በትክክል ያስቀመጡት; ማለትም፤"በኢትዮጵያ በተጨባጭ ያለው ሙስናን ለማጥፋ ትፍላጎት እንጂ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ብሎ ነገር የለም" ላሉት በቀርጠኝነት መፍትሔ መሻት ነው። ሦስተኛው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ፤ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ድርጅቱ የፖለቲካ ሥልጣን ካለው ፓርቲና ከሌሎቹም ሀይለኞች (powerful forces) ነፃ ማድርግና፤ ገለልተኛ በሆኑና ተዓማኒነት ባላቸው ግለሰቦች እንዲመራ ማድረግ ነው። ሁላችንም ተጠራርገን ወደ ቆሻሻ ከምንሄድ፤ በቁጭት፤ በብስጭትና በንዴት ከምንተላለቅ፤ አገርም ከመፍረሷ፤ ልንተባበር ይገባል። ትብብር ካለ ደግሞ ሁላችንም ተጠቃሚ እንሆናለን። በአንድና በዋናው በኩል የጥልፊያ ሙስናውን የምናቃልልበትና የሕዝብን ሀብት የምናስመልስባቸውን መንገዶች በጋራ መቀየስ እንችላለን። ለምሳሌ አንዳንዶቻችን፤ በምሥራቅ አውሮፓ ተፈጥሮ የነበረውን የማፊያ ጠባይ የነበረውን ኦሊጋርካዊ ሙስና እነዚያ ሀገሮችና የአውሮፓ ማህበር እንዴት ሊታደገው እንደቻለ፤ በራሽያ ደግሞ እነ ቭላዲር ፑትን የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎችንና ልምዶች፤ አጥንተንና አስሰን ማሳየት እንችላለን። በሌላው ጎን ደግሞ ከፀረ-ሙስናው ጦርነት በጣም ሊጠቀሙ የሚችሉት ሀብት የሰበሰቡት ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸው። ለምሳሌ፤ በንፁህ መልክ ሀብት የመሠረቱት ባለሀብቶች፤ ሀብታቸው በወላፈኑ እንዳይደመሰስባቸው፤ ያላግባብ የከበሩትም እንዲተርፋቸው መንገድን ይፈጥራል። ፈረንጆች ሁሉም አትራፊ (win-win situation) ይሆናል እደሚሉት ማለት ነው። እነዚህን ለማድረግ ኳሱን አስቀድሞ ማንከባለል ያለበት ኢሕአዴግ ነው።

---

# የዓለም ደቻሳ . . .

ከገፅ 9 የዞረ

ጉዳይ፣እኛ ምን እናድርግ?" የሚል አሳዛኝ መልስ ከዚህ በፊት በጽ/ቤቱ ይሰጣቸው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

አክለውም የፊሊፒንስ፣የግብፅ፣የሱዳንና ሲሪላንካ ዜጋ የሆኑ የቤት ሰራተኞች መንግሥቶቻቸው ከለላ በመስጠትና በመከታተል የዜጎቻቸውን ደህንነት እንደሚያስጠብቁ በመግለፅ በአንፃሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ከዚህ በፊት "ከአረብ ሀገር ቤርሜልና ሬሳ ነው የሚተርፈኝ" የሚል አሳዛኝ መልስ ተሰጠቶን ነበር ሲሉ ገልፀዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያውያን የቤት ሠራተኞች ስቃይ፣አስገድዶ መደፈርና እንግልት ሲበዛባቸው እንደሌሎች ዜጐች ለቆንስላ ጽ/ቤት ከመንገር ይልቅ ራሳቸውን እንደሚያጠፉና አንዳንዶቹ ከአሰሪዎቻቸው በመጥፋት በድብቅ ቤት ተከራይተው ያገኙትን ሥራ እንደሚሰሩ በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በፊት በሊባኖሱ ኢዝቦላና በእስራኤል መካከል ጦርነት ተከስቶ ደሃ የሚባሉ ሀገሮች መንግሥታት እንኳ ዜጐቻቸውን ተሯሩጠው ሲያስወጡ የኢትዮጵያ መንግሥት በቸልታ በመመልከቱ በዓለም ቀይመስቀል በኩል አመልክተው ወደ ሀገራቸው የገቡትን ቦሌ አየር ማረፊያ ሲደርሱ በኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ ነውና የመጣችሁት ይሄንን በቴሌቪዥን ግለፁ ተብለን እኛ ተታለን ሕዝብ እንድናታልል ተደርገናል፣ይሄንንም ለመተግበር ቃል ገብተው ቦሌ ሲደርሱ የጠፉም እንዳሉ በማስታወስ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

የዓለም ደቻሳን አሰቃቂ ሞት አስመልክቶ በተለየዩ ድህረገፆች በሊባኖስ መንግሥት ላይና ቤሩት በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ላይ የተለያዩ ትችቶች እየተሰነዘሩ ይገኛሉ፡፡ በተለይ ሐሙስ መጋቢት 6 ቀን 2004 ዓ.ም አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኙት የሊባኖስ ኤምባሲና የኢትዮጵያ ኤምባሲ ላይ በአካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና አንዳንድ የሌላ አፍሪካ ሀገራት ነዋሪዎች ተቃውሞአቸውን እንደገለፁ ተጠቁሟል፡፡

የዓለም ደቻሳ አሟሟትንና ቤሩት የሚገኘው ቆንስላ ጽ/ቤት ኃላፊው ሰጡት በተባለው አስተያየት ዙሪያ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃለ አቀባይ ሆኑትን አምባሳደር ዲና ሙፍቲን አነጋግረናቸዋል፡፡

አምባሳደር ዲና እንዳሉት ከሆነ የዓለም ደቻሳ አሰሪዎች አሚታል ብለው ቤሩት በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ይዘዋት መጥተው እንደነበር ገልፀውልናል፡፡ የቆንስላው ጽ/ቤት ጄነራል አሳምነው ደበሌ በበኩላቸው አሰሪዎቿን የማሳከም ኃላፊነት አለባችሁ ብለው እንደሸኛEቸው፣ ከዚያም ከግቢ ከወጡ በኋላ በዓለምና በአሰሪዎቿ መካከል አለመግባባት መፈጠሩን፣ሆስፒታል ተወስዳ እንደነበርና በመጨረሻም ራሷን እንዳጠፋች ይህንንም የሊባኖስ ፖሊስ ለቆንስላው ጄነራል እንደነገሯቸው አስታውሰዋል፡፡ በአሁን ወቅት በሥፍራው የሚገኘው ቆንስላ ጽ/ቤት ጉዳዩን ወደ ህግ እንደወሰደውና እየተከታተለው እንዳለ ከሚያውቁትና ከደረሳቸው ሪፖርት ውጭ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡ የቆንስላው ጽ/ቤት ጀነራል ለዴይሊስታር መገናኛ ብዙኃን ሰጡት የተባለውን አስተያየትም አምባሳደር ዲና አስተባብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ መካከለኛው ምስራቅ ባሉ አረብ ሀገራት በተለይ በሳዑዲ አረቢያ ከ45,000 በላይ ኢትዮጵያውያን በቤት ሰራተኝነት እንደሚሄዱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል፡፡

# የሙስና ነገር



አቶ አስገደ ገ/ሥላሴ

ሙስናን በሚመለከት፤ በአገራችን ህወሓት /ኢህአዴግ በረሃ እያለ በፍጥነት የጀመረና በአጭር እድሜው እንደ ስርአት ሆኖ የቆየ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሙስና በኢትዮጵያ ፍፁም ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል፡፡ የአገራችን ሃብት በጥቂት የመንግስት ሃላፊዎችና ከነሱ ትስስር ያላቸው ወገኖች እጅ ገብቷል፡፡

በቅርቡ አንድ የሚያስቅ ነገር ገጠመን፡፡ አቶ ስብሃት ነጋ በተሌቭዥን መስኮት ብቅ ብለው ሙስናን አስመልክተው መግለጫ ሲሰጡ ኢትዮጵያ ምንም እንኳ ሙስና ቢኖራት ከናይጀርያና ሌሎችም የተሸለች ናት ብለዋል፡፡

ሙስና ግን በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የህወሓት ኢህአዴግ መግለጫ ባህሪ እየሆነ የመጣና ኢህአዴግና ሙስና የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነዋል፡፡ ከላይ እስከታች ያሉ ሃላፊዎች በሙስና ተበላሽተው በእድሜያቸው አይተውት የማያውቁት ቅንጦትና ሃብት መሰብሰብ ችለዋል፡፡ አንድ አንድ ጊዜ ሙስናን ለመዋጋት ተብሎ የሚያዙና የሚታሰሩት ዋነኛው ምክንያታቸው ዝርፍያ ወይም ሙስና ሳይሆን በኢህአዴግ አይን በዚያ ዙሪያ ምስጢር የያዙ ወይም ንፁህ ሲሆኑ ነው፡፡ ትክክለኛ ሙሰኞች ሲያዙ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም፡፡ ምክንያቱም ሙሰኞች ስለማይጨካከኑ ህወሓት /ኢህአዴግ በአሁኑ ጊዜ በሙስና የተሰማሩትን ጨክኖ ልያጠፋ የማይችልበት ደረጃ ነው ያለው፡፡ ምክንያቱም ሙስናው የተሳሰረ ስለሆኑ ሙስናን ለመምታት ከሞከሩ ተያይዘው መግባታቸው ነው፡፡ ስለዚህ ሙስናን እንዋጋለን የሚለው ነገር የውሸትና ፍፁም ሊተገብር የማይቻል ነው፡፡

እግዲህ መላ መባል ካለበት!

ከሁሉም በላይ የህግ የበላይነት መኖር አለበት፤ ማለት በአገራችን ያሉ የፍትህና የፀጥታ አካላት ለገዥ ፓርቲም፣ ለተወዳዳሪ ፓርቲዎችም እኩል ማገልገል አለባቸው፡፡

ህዝባችን ምንም እንኳን ህገ መንግስቱ ጉድለቶች እንዳሉበት ቢታመንም ከህገ መንግስቱ ተጠቃሚ መሆን አለበት፤ እንደ ፍትህ ነፃነትና ሰብአዊ መብት የመሳሰሉት ሊረጋገጡለት ይገባል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በየጊዜው አዲስ አዋጆች በማወጅ ህብረተሰቡን ሊያማርሩ የሚችሉ ተግባራት መቆም አለባቸው፡፡

በነፃ ፕሬስ ላይ እየደረሰ ያለው አፈና በተለይ ጋዜጠኞች ላይ እየተደረገ ያለው እስርና መንገላታት ካልቆመ አደገኛ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡

መንግስት ፀረ አሸባሪነት ብሎ ያወጀው አዋጅ ለዋና አሸባሪዎች ሻዕቢያ፣ አልሻባብ፤ አልቃይዳ በግልጽ እንደ ማስቀመጥ የነዚያን ሽፋን በማድረግ ህጋዊና ሰላማዊ ፓርቲዎችን ማዋከብና ሽብር መፍጠር፣ ማሰር በአጠቃላይ ለፓርቲዎች ማፈኛ እየተጠቀመበት ስላለ ይህ አሰራር ባለመቆሙ የብዙሃን ፓርቲ መኖር አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ይህ ከሆነ የአሁኑን ትውልድ ወደ ሌላ የትግል አቅጣጫ ሊጋብዘው ይችላል፡፡

የህወሓት /ኢህአዴግ መንግስት ወደ ስልጣን የመጣው በትንሽ ደፈጣ ውግያ ብሶት ያወጣው ህዝብን በማሳለፍ ትልቅ ተዋጊ ሃይል በመፍጠር ደርግን የመሰለ ትልቅ ሃይል ደምስሶ በመቃብሩ ላይ ስልጣን የያዘ ነው፡፡ ውጊያ ደግሞ ሰውና ሃብት የሚበላ መሆኑን በሚገባ ያውቃል፡፡ ያ ውጊያ የፈጠረው ጠባሳ ሌላ እንተወውና በደፈጣ ውጊያና በደርግ ተሰልፈው በውጊያው አካላቸው የጐደሉና ጧሪ የሌላቸው አካል ጉዳተኞች በሚሊዮን የሚቆጠሩ እያየን ነው፡፡ በመሆኑም ኢህአዴግ እሚያደርገውን አፈና ወደ ቀደመው መንግሥት ሁኔታ እየመለሰን ነው፡፡

በኔ እምነት ህወሓት ኢህአዴግ በአሁኑ ጊዜ የተለየ የትግል አቅጣጫ ይዘው ለሚታገሉት የተለያየ ስም እየለጠፈ አሸባሪዎች፣፤ ትምክህተኞች፣ ጠባቦች፣ አንጃዎች፤ ወላዋይ ሃይሎች እያለ ይወነጅላል፣ ያናንቃል፡፡

ህገ መንግስት አክብረው የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከመወንጀል፣ ለማፍረስ ከመጣር፤ ከማሸበር ስክን ብሎ በመመልከት በሃሳብ ፍጭት፣ በሰላማዊ ውድድር፣ ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ በማቋቋም ነፃ ምርጫ ማካሄድ ነበር፡፡ ቂም በቀል ከመያዝ መታቀብ ከተሸነፉም አሜን ብሎ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ይህች አገር በኢህአዴግ ካልተመራች ትነጣጠላለች የሚል ፈሊጥ የሚያዋጣ ነገር አይደለም፡፡

ሌላዉ ህወሓት /ኢህአዴግና ሌሎች የ60ዎቹ ዓ.ም ፖለቲከኞች ይከተሉት የነበሩ የትግል ታክቲክና አቅጣጫ በመከተል ህወሓት /ኢህአዴግን ማስወገድ የሚቻለው በትጥቅ ትግል ነው የሚሉ ወገኞች የሚከተሉት የትግል አቅጣጫ (ምንም እንኳን) ትልቅ ስህተት ቢሆን ብሎም አገራችን ሊያደማና የሚያቆስል አደገኛ ቢሆንም÷

አንደኛ የኢህአዴግ መንግስትን በተለያየ መንገድ በመፎካከር በሰላማዊ መንገድ ህገ መንግስቱን በሚፈቅደውና በሰላማዊ መንገድ እንዲታገዙ ማድረግ እልክና ቂም በቀል በማስወገድ በተጨማሪ ኢህአዴግ ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲ በኔ ሳንባ ይተንፍሱ ማለቱን ማቆም አለበት፡፡

ሁለተኛ ትጥቅ አንስቶ የሚታገል ሁሉ አሸባሪ ነው ማለት ስህተት ነው፡፡ እንዲያ ከሆነ ደግሞ ህወሓትም በአሸባሪነት መከሰስ አለበት ማለት ነው፡፡ አሸባሪ የሆኑትን ደግሞ በሚገባ መምታት፡፡ ኢህአዴግ በህጋዊ መንገድ ብንገዳደረው ግን ለአገራችንም ለኢህአዴግ መንግስትም ጠቃሚ ነው፡፡

ሌላው የህወሓት /ኢህአዴግ መንግስት የአገራችንን የፍትህ አካላትና የደህንነት አካላት በሰላማዊ ትግል ለሚፎካከሩ ፓርቲዎች ሽብር መፍጠሪያና የክትትል መሣሪያ መደረጉን አቁሞ በመቀራረብና በመቻቻል ቢሰራ ለሁሉም ጠቃሚ ነው፡፡

ስለ አገራችን ሉአላዊነት ከምሁራኑ፣ ከትላልቅ ሰዎች፣ ከፓርቲዎችና ባለሃብቶች ጋር ተመካክሮ ቢሰራ የተሻለ ነው፡፡ ካለበለዚያ ቤት ዘግቶ ከኔ ሌላ አዋቂ የለም ማለቱ ጠቃሚ አይሆንም፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን ሰላማዊትና የበለፀገች አገር ልትሆን ከተፈለገ የአገራችን ሉአላዊነት፣ ድንበር፣ የባህር በራችን መከበር አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ የባህር በር አጥቶ በጕሮሮው ታንቆ ሊኖር አይችልም፡፡ የኢህአዴግ መንግስት ይህን አውቆት የህዝብ ጥያቄ መመለስ አለበት፡፡

ከሻዕብያ ጋር ያለው የግጭት አፈታት ህጋዊና ታሪካዊ አመጣጣችንን የማያፈርስ፣ ሉአላዊት ሃገራችንን በሚያከብር፣ ግልፅነት ባለው፣ ህዝባችን በሚያውቀው መልኩ መፈፀም አለበት፡፡ ከህዝብ እውቅና ውጭ የሚደረግ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በአጠቃላይ ህወሓት/ ኢህአዴግ በሻዕብያ ላይ ቁርጠኛ እርምጃ ካልወሰደ በኢትዮጵያ ህዝብና በተቃዋሚዎችም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ኢህአዴግ በሸዕብያ ላይ መጨከን አቅቶት ቢወላውልም የኢትዮጵያ ህዝብ አይወላውልም፡፡

ምርጫን በሚመለከት ባለፉት ሃገራዊና ክልላዊ የወረዳና ቀበሌ ምርጫዎች ፍትሃዊ እንዳልነበሩ፣ አለም አቀፍ መስፈርት እንደላሟሉ፣ በምርጫው ገዥው ፓርቲ እንዳጭበረበረ የአለም አቀፍ ታዛቢዎች ያራጋገጡት ነው፡፡ አሁን ወደፊትም በማጭበርበርና በመወንጀል ሊታለፍ ነው?

በኔ እምነት መሆን ያለበት

አሁን ያለውና በህወሓት /ኢህአዴግ ተመልምሎ የተዘረጋው የምርጫ ቦርድ መዋቅር ፈርሶ መንግስትና ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በዕምነት ያቋቋሙት ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ መፈጠር አለበት፡፡ ይህ የዴሞክራሲና የፍትህ ማስፈኛ ዋነኛው መንገድ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡

የኢህአዴግ መንግስት በቀረበው የምርጫ ሞዴሊትስ ፕሮፓዛል በአንድ አንድ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ፓርቲዎችና የኢህአዴግ አጋር ድርጅቶች ብቻ በመፅደቁ እንዲፈርስ ተደርጎ ኢህአዴግ፣ ሃቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶችና ሌሎችም ተደራድረው ባፀደቁት ህግ እንዲፈፀም፡፡ አሁን ያለው ገዥ ፓርቲ የሚፎክርበት የምርጫ ህግ ለነ መድረክ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሚደረጉ ድርድሮችም ግልጽነት ባለው መልኩ በብዘሃን መገናኛ እየታየ መሆን አለበት፡፡

በሚደረገው ምርጫ የመንግስት ባለስልጣናት (የገዥ ፓርቲ አባላት) ፖሊስ፣ መከላከያ፣ ደህንነት፣ የቀበሌ መሪዎች የመሣሰሉት ከጣልቃ ገብነት መታቀብ አለባቸው

ሁሉም ብዙሃን መገናኛ፣ ለገዥው ፓርቲም፣ ለተቃዋሚዎችም ፍትሃዊ የአየር ሰዓት ድልድል ማድረግ አለባቸው፡፡ ካአሁን በፊት የነበረው የውድድር ጊዜ ክርክር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ውድድር ይኑርም አይኑርም በሆነ ጊዜና ቦታ ተቃዋሚዎች ሚዲያ ሽፍን ማግኘት አለባቸው፡፡ ገዥው ፓርቲ የአገሪቱ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኤፍ ኤሞች (የፓርቲም ሬድዮ ጣብያ ሬዲዮ ፋና ድምፅ ወያኔ) ና ሌሎችም በሁሉም ቋንቋዎች፣ 24 ሰዓት ሙሉ ከምርጫ እስከ ምርጫ፣ ለ5 ዓመታት ለገዥ ፓርቲ እንደሚሰሩ ይታወቃል፡፡ ይህ መቆም ይገባዋል ለሁሉም ፍትሃዊ ክፍፍል ይደረግ፡፡

አሸባሪነትን በሚለከት

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

# ሰላማዊ ትግል እና ድርድር
# ክፍል 3፡ እንከን የለሽ ተደራዳሪ!



ግርማ ሞገስ
(girmamoges1@gmail.com)

በባለፈዉ ሳምንት እንከን የለሽ ተደራዳሪነት ስር ሶስት ወሳኝ ነጥቦችን አንስተን ቀሪዎቹን ሰባት ነጥቦች ለዛሬ በይደር መተዋችን ይታወሳል፤ እነሆ ቀሪዉ ክፍል፡፡

(4ኛ) ዝግጅት አራት፥ ይህ ዝግጅት በድርድር ላይ ለሚደረግ ሰጥቶ የመቀበል (Compromise) ስምምነት መስፍርት መቀመር (Setting Criteria for Offer and Counter-offer) ነው። ስለዚህ በእያንዳንዱ የድርድር ነጥብ ላይ ሌላው ወገን ወይንም ተቀናቃኞችን የሚለግሰንን ስምምነት (Offer) ፋይዳ/ዋጋ የምንመዝንበት መስፈርት የምናፈላልገው በዚህ ዝግጅት ነው። የኔ መስፈርቴ ምንድን ነው? የሌላውስ ወገን መስፈርት ምንድን ነው? የአለም ህዝብ የሚጠቀምባቸው መስፈርቶች አሉን? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተው መልስ ሊሰጥባቸው ይገባል። ይህ ዝግጅት ያላገኘነውን ድል የተቀዳጀን ወይንም ያልደረሰበን ሽንፈት የደረሰብን እንዳይመስለንም ይረዳናል። በድርድር ላይ እንዳንጭበረበር ይረዳናል።

(5ኛ) ዝግጅት አምስት፥ ይህ ዝግጅት ደግሞ በድርድር ላይ ከባላንጣ ተደራዳሪዎቻችን በኩል የሚመጡ የንዴት፣ የደስታ፣ የእሽታ፣ የመሰላቸት፣ የእንቢታ ወይንም ሌሎች ምልክቶችን (Signals, communication, and so on ) ላለመሳት የሚደረግ ዝግጅት ነው። ስለዚህ ከባላንጣችን በአንደበት፣ በአካል፣ በእንቅስቃሴ ወይንም በሌላ የሰው ልጅ ላይ ሊነበቡ በሚችሉ መንገዶች በሙሉ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ወይንም ምልክቶችን ላለመሳት እና በትክክል ተርጉመን ተገቢውን አዎንታዊ እርምጃ በተገቢው ሰዓት እና መንገድ ለመለገስ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

(6ኛ) ዝግጅት ስድስት፥ የዚህ ዝግጅት ተግባር እኛ ሌላውን ወገን ማመን ሳይኖርብን ሌላው ወገን (ተቀናቃኞችን) ግን እንዲያምነን ለማድረግ የሚደረግ ዝግጅት ነው። ይህ ዝግጅት ሳታምን ለመታመን ቻል (Be trustworthy without being trusting) የሚለውን የድርድር ጠቃሚ ሙያ ለማዳበር ይጠቅመናል። ስለዚህ ከሌላው ወገን (ከተቀናቃኝ) ጋር ልክ ያለው ግንኙነት (Relationship) የመመስርት እና ግንኙነትን በጥሩ ሁኔታ የማቆየት ችሎታ ሊኖረን ይገባል። በዚህ ረገድ የባላንጣ ፓርቲን ተደራዳሪ ተጠራጣሪ ከሚያደርግ፣ ከሚያስበረግግ እና ከሚያስቆጣ እርምጃ መቆጠብ እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ አነጋገር የሌላቸው የወረቀት መግለጫዎች ከማውጣት ተግባሮች በሙሉ ለመቆጠብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል ማለት ነው።

(7ኛ) ዝግጅት ሰባት፥ ይህ ዝግጅት ተቀናቃኝ ፓርቲን ወክሎ ለሚደራደርን ሰው ቃል መግባት ሊያስፈልግ እንደሚችል፣ የምንገባው ቃል ግን ከድርድር ካገኘነው ጠቀሜታ ጋር የተመጣጠነ መሆን እንዳለበት እና የገባነውን ቃል ሳናጓድል መፈጸም እንዳለብን ያስታውሰናል። ይኸን ማድረግ በሌላው ወገን መከበርን፣ አለመደፈርን፣ እና ቁም ነገረኛ ተደርጎ መወሰድን ያተርፋል።

(8ኛ) ዝግጅት ስምንት፥ የዚህ ዝግጅት ተግባር የምንደራደርበትን ጉዳይ በደንብ ከተረዳን በኋላ ያሉንን የድርድር አቅሞች፣ ድጋፎች፣ መረጃዎች፣ (ካርዶች) በትክክል እንድናውቅ ማድረግ ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ወደፊት የአሰብ ወደብ ይገባኛል ጥያቄን በተባበሩት መንግስታት ለድርድር ልታነሳ አስባለች እንበል። ኢትዮጵያ ይኼን አይነት አሳብ ካላት በዚህ ዝግጅት መሰረት ከድርድሩ በፊት በግልም ይሁን በቡድን ካስፈለገም ሙያተኛ ተደራዳሪዎችን (ወይንም ተመክሮ ያላቸውን) አሰባስቦ ካለአንዳች መታከት መነሳት እና መልስ ማግኘት ከሚገባቸው ጥያቄዎች ውስጥ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ይሆናሉ ማለት ነው፥ ጉዳያችን ቀደም ብሎ ይታወቃልን? ጉዳያችን ተቀባይነት አለውን? ህግ ይደግፈናልን? ፍትህስ (እጅግ ጠቃሚ ነው)? የታሪክስ ማስረጃ አለን? የህዝብ ድጋፍ አለን? የአለምስ ህዝብ ይደግፈናል? አስፈላጊውን የዲፕሎማሲ ትግል ለማድረግ አቅሙ አለን? የዲፕሎማሲ ተደራዳሪዎቻችን ችሎታቸው፣ ተወዳጅነታቸው፣ ታዋቂነታቸው፣ የንግግር ችሎታቸው፣ ተአማኒነት የማግኘት ችሎታቸው፣ ማራኪነታቸው ወ.ዘ.ተ. የተሟላ ነውን? በቀላሉ የህዝቡን ተአማኒነት ማግኘት እንችላለን? እንዲሁም በሌላ በኩል የሌላውን ወገን (ተቀናቃኝ) ወገን ሁኔታም አንስተን ተገቢ ጥያቄዎች በማንሳት እና መልስ በማቅረብ ድርድሩ ኢትዮጵያን በሚጠቅም አኳን እንዲያከትም ለማድረግ ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

(9ኛ) ዝግጅት ዘጠኝ፥ የዚህ ዝግጅት ተግባር የሌላውን ወገን (የተቀናቃኙን) ተደራዳሪዎች አስተሳሰብ እና ባህሪ በቅድሚያ እንድናውቅ ማድረግ ነው። በመሆኑም የሌላውን ወገን ተደራዳሪዎች አስተሳሰብ፣ ስልጠና፣ ባህሪ፣ ሙያ፣ ወ.ዘ.ተ. ድርድር ከመግባታችን ቀደም ብለን ለማወቅ የሚያስችል በቂ ስራ መስራት ተገቢ ነው። ለምሳሌ ያህል

# ኢመማ የኢትዮጵያን መምህራን ያዋረደ የደመወዝ ጭማሪ

ከመ/ር ቀለሙ ሁነኛው
kelemhun@yahoo.com

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በየዘመኑ ከሚነሱ ገዢዎች ጋር የሚሞዳሞድና እንደ እስስት የሚቃየር ማፈሪያ የሙያ ማህበር ነው:: የኃይለ ሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ ለመጣል በተደረገው ተጋድሎ የኢትዮጵያ መምህራን ሚና የጎላ እንደነበር የታሪክ ድርሣናት ህያው ምስክሮች ናቸው:: በደርግ አገዛዝ ዋዜማ ላይም ቢሆን ኢህአፓና መኢሶንን የመሣሰሉ ጠንካራ ፓርቲዎችን በመምራትና የህዝቡን ንቃተ ህሊና በማጎልበት ረገድ የመምህራን ሚና ጎልቶ ታይቷል:: በዘመነ ኃይለ ሥላሴ ለሞያው ከተሰጠው ከፍተኛ ክብር አንፃር የመምህራን ደመወዝ ከወረዳ አስተዳዳሪዎች ደመወዝ ጋር ተቀራራቢ እንደሆነ ማንም የሚመሰክረው ነው::

“የገበሬው አባት የወታደር አባት
የመሀንዲሱ አባት የዶክተሩ አባት
መምህር አንተ ባትኖር
መካን ነባር ህይወት . . .”

እየተባለ የተዘመረለት አኩሪ ሙያ ነበር መምህር ነት:: ይህን ታላቅና ክቡር ሞያ ደርግ ገደለው:: ኢህአዴግም በተራው ቀበረው:: ዛሬ የምናስተምረው ትውልድ ነገ መምህር ለመሆን ይመኝ እንደሁ ስንጠይቀው “ቲቸርዬ ምነው ምን በደልኩህ?” ሲል አሸማቃቂ ምላሽ ይሰጠናል:: ይህንን ውርደት ነው ያጎናፀፈን:: ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አንገትዬው የተበጫጨቀ ሸሚዝ፣ የሚለብስና የተንሻፈፈ ጫማ የሚጫማ የሲቪል ሠራተኛ ቢኖር መምህር ነው:: ወር ቆጥሮ ከሚያገኛት ደመወዝ ውጪ እንደ ሌላው የአገርና የህዝብ ሀብት ልዝረፍ እንኳን ቢል እጁ ላይ የሚኖረው ጠመኔ ነው፤ ዳስተር ነው:: መምህሩ የአባል ክፍያ አያውቅ:: በዓመት አንዴ እንኳን ስብሰባ ቢጠራ በኢህአዴግ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የተዘጋጀ አንባሻና ሚሪንዳ ይወረወርራትና ይሸኛል::

ኢህአዴግ በመምህራን ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመታገል ነፃ የሆነ ማህበር የለም:: ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ይመሩት የነበረውና ዛሬም ቢሆን አለም አቀፉ የመምህራን ማህበርና ILo (International Labor organization) ጭምር እውቅና የሰጡት ኢመማ ለአባላቱ ያለውን ወገንተኝነት የተመለከተው ኢህአዴግ ማህበሩን አፈረሰው:: መሪዎቹም አገር ጥለው ኮበለሉ:: የማህበሩ ገንዘብና ንብረት ኢህአዴግ በራሱ አምሳል ላዋቀረው የዛሬው ኢመማ በጠራራ ፀሐይ አስረከበ::

በኢህአዴግ ህገ መንግስት ድንጋይ መሠረት አንድ ሞያተኛ የሲቪክ ማህበራት አባል የመሆንም ሆነ ያለመሆን መብት አለው:: ማህበሩም የሚመሰርተው በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ እንደሆነ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ በተግባር የማይተረጎም ጉዳይ ነው:: አንድ መምህር ማህበሩን አልፈልግም ቢል የሚያጋጥሙት መሰናክሎች እስከ ሥራ መባረር ያደርሰዋል:: በምስጢር ጠረጴዛ ኪስ ውስጥ የተቀመጡ የተለያዩ መመሪያዎች በማህበሩ ጓዳ አሉ:: መምህሩ የማህበሩ አባል ካልሆነ ኢህአዴግ መስከረም በጠባ ቁጥር ስብሰባ እየጠራ የሚደሰኩርለትን የሞያ ፍቃድ (የማስተማር ፍቃድ) እና የሞያ ብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ማግኘት አይቻልም:: ይሄ ደግሞ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ቦንብ ነው:: መምህሩ በማህበሩ ላይ ቢያምፅ ኢህአዴግ በነጋታው የሞያ ፍቃድ በመስጠት ብዙሃኑን ከጨዋታ ውጭ ያደርጋቸዋል::

ዛሬ እያንዳንዱ መምህር የሞያ ማህበሩ አባል መሆኑ የሚታወቀው በየወሩ በሚከፍላት የ4 ብር መዋጮ ብቻ ነው:: ከዚህ በዘለለ በማህበሩ መዋጮ ብቻ ነው:: በማህበሩ እንቅስቃሴም ሆነ በትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ በማህበሩ መድረክ የሚደረግ ውይይት የለም:: የትምህርት ፖሊሲውን ድክመት መተቸት አይቻልም:: በየደረጃው በሚዘጋጁ የመማሪያ መፅሐፍት ላይ የሞያው ባለቤት የሆነው መምህሩ የሚሰጣቸው ግብረ መልሶች (feed back) ተቀባይነት የላቸውም:: የትምህርት ጥራቱ ከዓመት እጅግ ዘግናኝ በሆነ ፍጥነት ሲያሽቆለቁል እየታየ ለመምህሩ አስተያየት የዝሆን ጆሮ ይባላል:: በየደረጃው በራሳቸው ጊዜ የተመረጡ የማህበሩ አመራሮችም ደፋ ቀና የሚሉት ለራሳቸው ጥቅም ነው:: ለኢህአዴግ ታማኝ በሆኑ ቁጥር ነፃ የት/ት እድል ይሰጣቸዋል፤ በተለያዩ ቦታዎች ይሾማሉ:: ማህበሩ ከተመሠረተበት አላማ አንፃር የመምህሩን መብት ለማስከበርና የት/ትን ጥራት ከማስጠበቅ አንፃር አይደለም ውርውር የሚሉት:: ግባቸው የኢህአዴግን እድሜ ከማራዘም አንፃር መትጋት ብቻ ነው::

የኢትዮጵያ መምህራን በኢህአዴግ አገዛዝ የሚደርስባቸው ጫና እየበረታ ሲመጣ ፅኑ አቋም ያላቸው የአመራር አካላት በድሬዳዋው የጥቅምት 2004 ዓ.ም ጉባኤ ላይ ብቅብዬ በተለይም ከአማራ ክልል የመጡ የማህበሩ መሪዎች የትግራይና የኦሮሚያ ክልል አመራሮችን በማስከተል ለመምህራን ያላቸውን ወገናዊነት ማሳየታቸውን በዚሁ ጋዜጣ ላይ ማስነበቤ ይታወሳል:: ጉባኤውም በአቋም መግለጫው ተራቁጥር ሦስት ላይ የመምህራን የደመወዝ ስኬልና የእርከን ማሻሻያ እንዲደረግና የወር ደመወዙም የወቅቱን የኑሮ ውድነት ከግንዛቤ ያላስገባ በመሆኑ መንግስት በአፋጣኝ ማስተካካያ እንዲያደርግና እስከ ጥር 30/2004 ዓ.ም ምላሽ እንዲሰጥ ባስተላለፈው መሠረት የአገሪቱ መምህራን ውጤቱን በጉጉት ይጠባበቁት ነበር::

የኢህአዴግ አመራሮችም የመምህራንን ጥያቄ ለማድበስበስ ብዙ ጥረዋል:: የድርጅት አባል የሆኑ መምህራንን ለብቻ በመነጠል ትግሉን ለማኮላሸት የተደረገው ጥረት ሙሉ ለሙሉ ባለመሳካቱና በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የሥራ ማቆም አድማዎች በማየላቸው በኢቴቪ የቴአትር መድረክ ላይ በሸፍጥ መተወን የሚችለው ኢህአዴግ አስገራሚ ትዕይንት አሳየን፤ አስደመጠን:: መንግስት ለሙያው ልዩ ትኩረት ከሌላው የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛ የተለየ የደመወዝ ስኬልና እርከን ማሻሻያ ማድረጉን ለፈፈ:: ውድ ኢትዮጵያውያን የመንግሥትን የሸፍጥ አሰራር አጠናችሁ እውነተኛውን ፍርድ ስጡ:: ያን ያህል ነጋሪት የተጎሰመለትና የሁለት ሚ/ር መስሪያ ቤት ሚኒስትር ዴኤታዎች ያቀነቀኑት የደመወዝ ጭማሪ ዜማ ለዲፕሎማ ምሩቅ የ61.00 ብር ለመጀመሪያ ዲግሪ የ73.00 ብር ጭማሪ ነው:: ይህችም ጭማሪ ከዋናው ደመወዝ ጋር ስትደመር ለሥራ ግብር፣ ለጡረታ አበል ወዘተ ተቆራርጣ እስከ 50 ብር ትደርሳለች:: ይህ ማለት ደግሞ አንድ ሊትር ዘይት እንኳን የማይገዛ ጭማሪ ነው:: ከሁሉም በላይ የሚገርመው አንድ መምህር ጡረታ እስኪወጣ የማይደርስበትን የደረጃ እድገት መመሪያ በማውጣት ከ5 እስከ 7 ሺህ ብር የሚደርስን ጣሪያ መናገር ምን የሚሉት ቀልድ ነው:: ይሄ ማለት ደግሞ 50 ብር ጨምሮ የቤት ኪራይና የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችን በመምህሩ ላይ ማስወደድ? ማለት ነው:: በዚህ ድርጊት የሚጎዳው መምህሩ ብቻ ነውን?

እጅግ በጣም የሚያሳዝነውና መምህሩንና ሞያውን ለተጨማሪ ውርደት የአረገው የኢመማ ፕሬዝዳንት የሆነው አቶ ዮሐንስ ባንቲ ለኤሌክትሮኒክስና ለህትመት ሚዲያዎች የሰጠው ምላሽ ነው:: ጭማሪው አበረታችና መምህሩን ለሥራ የሚያነሳሳ መሆኑን መግለፁ እውን ይህ ሰው የሞያ ማህበሩ ፕሬዝዳንት ወይስ የኢህአዴግ ሊቀመንበር? የሚል ጥያቄን የሚጭር ነው::

ከሦስት አመት በፊት በባለሞያ የተጠናው የደመወዝ ስኬልና የእርከን ማሻሻያ ግቡ 61 እና 73 ብር ለማስጨመር መሆኑ እጅግ አሳዛኝ ነው:: አቶ ዮሐንስ ጭማሪው (ማሻሻያው) የመምህሩን ጥያቄ የሚመልስ ስላይደለ እንደገና መጤን አለበት:: ለማለት ጉልበት ቢያጥረው እንኳን ለምን ዝምታን አልመረጠም? ምንስ አስወተወተው? ለምንስ የወከለውን መ/ር ድምፅ እስኪሰማ መልስ ከመስጠት አልታቀበም? ውድ ኢትዮጵያውያን በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ህዝብ ነጋሪት የተጎሰመለት የመምህራን የደመወዝ ጭማሪ ከላይ እንደገለፅኩት አንድ ሊትር ዘይት እንኳን የማትገዛ መሆኑን ከግንዛቤ አስገብታችሁ እባካችሁ በየጓራችሁ ቤታችሁን በተከራዩ መምህራን ላይ ኪራይ ጨምራችሁ ለስቃይ አትዳርጓቸው:: ከእናተው ጋር እየኖሩ የናንተኑ ልጆች እውቀት የሚያስጨብጡ የእውቀት አባቶች ናቸውና:: ጠግበው መብላት ባይችሉ እንኳን ቤት ገመና ከታች ነውና ሲርባቸው በጊዜ ገብተው ኩርምት ብለው

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# ኢህአዴግ ለመምህራን . . .

ከገፅ 14 የዞረ

ገንዘብ ምክንያት ጠቅላላ የገንዘብ አቅርቦት በዓመት በሃምሣ በመቶ እንደሚያድግ ገልፆ ነበር:: ይህንንም ስለተናገረና የመንግሥትን ገመና በማጋለጡ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ወርፈውታል::

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ብቻ ሳይሆን ከንግድ ባንኮችም ቢሆን አዋጭነታቸው ላልተረጋገጡ የቢዝነስና የልማት ፕሮጀክቶች የሚሰጡ ብድሮች የዋጋ ንረትን በማባባስ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: ይህን በተመለከተ ዋናው ተጠያቂ የመንግሥት ንብረት የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው:: አንዳንድ ሰዎች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን “የሙስና ባንክ” እያሉ መጥራት ጀምረዋል:: “የመንግሥትና የግል ሌቦች” ትላልቅ ሕንፃዎች የገነቡት “ከበላይ አካል” በሚሰጥላቸው ቀጭን ትዕዛዝ መሠረት ከዚህ ባንክ በሚወስዷቸው ብድሮች ነው:: እነዚህ ግለሰቦች “ሌቦች” በመሆናቸው ሕንፃዎችን የሠሩት በግንባራቸው ወዝ ካፈሩት ገንዘብ ከፊሉን ለረጅም ጊዜ ቆጥበው ሳይሆን በአንድ ጀምበር በተፈቀደላቸው የባንክ ብድር በመሆኑ ለግንባታው የሚወጣው ወጪ በዋጋ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል::

በዚህ የመንግሥት የገንዘብ ፖሊሲ በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዱት እንደ መምህራን ዝቅተኛና ቋሚ ደመወዝና ገቢ ያላቸው ዜጎች ናቸው:: ሥርዓቱ የሙስና ሥርዓት እንደመሆኑ ከፍተኛ ደመወዝና ገቢ የሚያገኙት ሰዎች በችሎታቸውና በምርታማነታቸው አይደለም፤ ለእነሱ መንግሥት ያስቀመጠላቸው መስፈርት አባልነት፣ታማኝነት እና ደጋፊነት ነው:: በዚህም ምክንያት ደመወዝ እና ገቢ ከመርታማነት ተነጥለዋል:: ምንም ዓይነት ተጨባጭ ምርት ወይም አገልግሎት ለማያመርቱ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ወታደራዊ መኮንኖች የፖሊስና የደህንነት ኃላፊዎች በሚሊዮን ለሚቆጠሩ የኢህአዴግ አባላት ሰላዮች፣ ጠርናፊዎች፣ካድሬዎች፣ አማካሪዎችና ደጋፊዎች ሕወሓት/ኢህአዴግ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ገንዘብ እየታተመ ከፍተኛ ገንዘብ ይሰጣቸዋል:: በሀገራችን ዋናው የዋጋ ጥረት መንስዔ ይህ ነው:: ገንዘብ በምርት ካልተደገፈ ውጤቱ የዋጋ ንረት መሆኑን ለማወቅ ኢኮኖሚክስ መማር አያስፈልግም::

በመሆኑም በሀገራችን የዋጋ ንረት ሊወገድ የሚችለው ሥርዓቱ ሲወገድ ብቻ ነው:: ለዚህም ነው ሥራአጦች የፋብሪካ ሠራተኞች መምህራን ሌሎች ተራ የመንግሥት ሠራተኞች ተራ ወታደሮች፣የፖሊስ አባላት፣ተማሪዎች፣የቤት እመቤቶች፣ወጣት ሴቶችና በአጠቃላይም ወጣቱ ትውልድ ሕብረታቸውንና አንድነታቸውን አጠናክረው ለሰላማዊ ትግል ቆርጠው መነሳት ያለባቸው በተለይ መምህራን የኢኮኖሚ መብታቸውን ለማስከበርየጀመሩትን መጠነ ሰፊ ትግል በተጠናከረ መልክ መቀጠል ይጠበቅባቸዋል:: ለመምህራን ተደረገ የተባለው የደመወዝ ጭማሪ እንደ ቀልድ የሚቆጠር ይመስለኛል:: ሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ በቆየባቸው በአለፉት ሃያ አንድ ዓመታት የገበያ ዋጋ በሃያ እጥፍ ገደማ የጨመረ ሲሆን ደመወዝ ግን ቢበዛ በአምስት እጥፍ ነው እንደጨመረ የሚገመተው ይህ የሚያሳየው የዋጋ ንረት የሥርዓቱ ውስጣዊ ባሕርይ መሆኑን ነው:: ይህም ማለት ሕወሓት/ኢህአዴግ የሚያደርገው ኢምንት የደመወዝ ጭማሪ ለሃያ አንድ ዓመታት ያደረሰብንን የኑሮ ደረጃ ማሽቆልቆል ጨርሶ ሊያካክስ አይችልም:: ብቸኛው መፍትሔ በሰላማዊ ትግል ሥርዓቱን ማስወገድ ነው:: ሕወሓት/ኢህአዴግ ፍርፋሪ በመወርወር እየተነሳ ያለውን ሰላማዊና ሕዝባዊ ማዕበል ማቀዝቀዝ አይችልም::

የሚከተሉትን ሶስት ወገኖች እንመልከት፥ (1) ከጦር መኮንኖች ጋር የምንደራደር ከሆነ አኩሪ ታሪክ፣ ማሸነፍ፣ የተፈተነ ስለመሆን፣ ዝግጁ መሆን፣ መውሰን፣ መከበር፣ ስነስርዓት፣ ለአደራና ለኃላፍነት ብቁነት፣ ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉት ቃላቶችን በድርድር ንግግራችን ውስጥ ብንጠቀም ይበልጥ ለጆሮዋቸው ስለሚጥሙዋቸው ለበለጠ መቀራረብ ይጠቅማሉ። (2) የተፈጥሮ ሳይንትስቶችን በሚመለከት፥ ለምሳሌ ውይይቱ ስለውሃ ከሆነ ወሃን ምን ውሃ አደረገው? ከሚለው ጥያቄ እንደሚነሱ እና እነዚህ ወገኖች ትልቅ የውሃ ጅረት ሲያዩ የሚታያቸው ሞሊኪውሎች (Molecules) እንደሆኑ ቀደም ብለን ብንገነዘብ ይጠቅመናል። (3) ድርድሩ ለምሳሌ ከመሐንዲሶች (ኢንጂነሮች) ጋር ከሆነ ደግሞ መሐንዲሶች አንድ ነገር መስራት አለመስራቱ ላይ እንደሚያተኩሩ፣ ካልሰራ እንዲሰራ ምን መደረግ አለበት በሚለው ላይ ውይይቱ ቢያተኩር እንደሚያስደስታቸው፣ ከሰራ ደግሞ እንዴት የተሻለ እንዲሰራ ማድረግ ይቻላል የሚል ወይይት እንደሚጥማቸው እንዲሁም ትልቅ የውሃ ጅረት ሲያዩ ፈጥኖ የሚታያቸው እንደ ተፈጥሮ ሳይንትስቶቹ ሞሊኪውሎች (Molecules) ሳይሆኑ ኢነርጂ (Energy) እንደሆነ ቀደም ብሎ ማወቅ መቀራረብን ለመፍጠር ይረዳል።

(10ኛ) ዝግጅት አስር፥ የዚህ ዝግጅት ተግባር በድርድሩ ውስጥ የሚፈጠር (1) አለመግባባትን ወደ መግባባት እና (2) እንቢታን ወደ እሺታ ለማሸጋገር እንድንችል ምን ማድረግ እንዳለብን በቅድሚያ እንድናውቅ ማድረግ ነው። ይህ ዝግጅት ሌላው ወገን (ተቀናቃኝ) ምን ብሰጠው (Offer) ከድርድሩ ይወጣል ወይንም አይወጣም የሚለውን በትክክል መተንበይ ወይንም መገመት እንድንችል ይረዳናል። መተንበይ እንድንችል ደግሞ ሌላው ወገን ከስምምነት ምን ያገኛል? ምንስ ያጣል? ካለመስማማትስ ምን ያገኛል? ምንስ ያጣል? ለሚሉት ጥያቄዎች የሚገኙትን መልሶች በማጤን ነው።

ሰዎች (እቃ መግዛትን ጨምሮ) እንቢ የሚሉባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም የሚከተሉት የብዙዎቹ የጋር ምክንያቶች ናቸው። (1) አንደኛው ምክንያት መስማማት የሚያመጣውን በትክክል መገንዘብ ካለመቻልና ከመፍራት ነው። መፍትሄው የፍራቻውን ምክንያት በትክክል መረዳታ እና ከፍራቻ ወደ ምቾት የሚያሸጋግሩ ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ ነው። (2) ሁለተኛው ምክንያት በስስምነቱ እና ስለስምምነቱ እንደምታ እርግጠኛ አለመሆን ነው። መፍትሄው ማብራራት (ማሳወቅ) ነው። (3) ሶስተኛው ምክንያት እንካ የተባለው የመስማሚያ ድጎማ ፋይዳው በቂ አይደለም በሚል ነው። መፍትሄ እርግጥም ፋይዳው ዝቅተኛ ከሆነ ክፍያውን ከፍ በማድረግ ፋይዳውን ከፍ ማድረግ ነው። ፋይዳው ዝቅተኛ ካልሆ ደግሞ አለመሆኑን በማስረጃ አስደግፎ አሳማኝ በሆነ መንገድ ማብራራት ነው። (4) አራተኛው ምክንያት እንቢ ማለት ቀላል በመሆኑም ነው። እሺ ማለት በራስ ላይ አዲስ አሳብ እና አዲስ ስራ ስለሚያመጣ አዲስ ስራ እና አብሮት የሚመጣውን አሳብ ለማስወገድ ከመፈለግም ነው። ይህ ከነበሩበት መንቀሳቀስን ያለመሻት ዝንባሌ (Initial Inertia) የሚባለው ነው። መፍትሄው እሺታ የሚያመጣውን ጠቀሜታ ማስረዳት ነው። እንቢታ ምን ምንን እንደሚነፍግ ቀስ በቀስ ለማስረዳት መሞከር ነው።

ስለዚህ ከፍ ብለን በመረመርናቸው የድርድር መዘጋጃ ነጥቦች ላይ በሙሉ ከድርድሩ በፊት በግልም ይሁን በቡድን ካስፈለገም ሙያተኛ ተደራዳሪዎችን (ወይንም ተመክሮ ያላቸውን) አሰባስቦ ካለአንዳች መታከት ዝግጅት ማድረግ ይጠቅማል። እከን የለሽ ተደራዳሪ እንድንሆን በር ይከፍታል። አሜን!

---

------------- ፍጻሜ ድርድር

# የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ራሳችሁን ከተዘረጋው ወጥመድ ነፃ አውጡ

በለጠ ጎሹ

ወጣቶች የምላችሁ በግምት ከ15-35 ዕድሜ ክልል ውስጥ ያላችሁትን ነው፡፡ እኔ ከዚያ የዕድሜ ክልል ከወጣሁ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ግን ስለ አለፍኩበት ለእናንተ ወንድሞቼ፣ እህቶቼና ልጆቼ ለምትሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ብዙም ሳይሆን፣የማካፍላችሁ ተሞክሮና ልምድ አለኝ ብዬ አምናለሁ፡፡

ብዙዎቻችሁ ተማሪዎች ናችሁ፤ሥራ አጥ የሆናችሁትም ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ጥቂቶቻችሁ በግል ሥራና በመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥራችሁ የቀንም ሆነ የወር ገቢ የምታገኙ ናችሁ፡፡ ጐዳና ተዳዳሪዎችም አላችሁ፡፡ በሴተኛ አዳሪነትም ኑሮአቸውን የሚገፉ ሞልተዋል፡፡

በአጠቃላይ፣በአዲስ አበባ ከተማ የወጣቶች ጠቅላላ ቁጠር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ኢህአዴግ የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት ከ3.5 ሚሊዮን አይበለጥም ይላል፤ በእኔ ግምት ግን ከ 6 ሚሊዮን አያንስም፡፡ ከዚያ ውስጥ የናንተ የወጣቶች ብዛት ከጠቅላላው ቢያንስ ሃምሣ በመቶ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ይህ ማለት የእናንተ ብዛት ቢየንስ ሦስት ሚሊዮን /3 ሚሊዮን/ ገደማ ነው ማለት ነው፡፡ እንግዲህ፣እናንተ በደንብ ባትገነዘቡትም፣ለአዲስ አበባ ሕብረተሰብ የእናንተ ወሳኝነት ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

ለዚህም ነው፣ ሕወሓት ኢህአዴግ መንግሥት በእናንተ ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርጐ እየተንቀሳቀሰ ያለው፡፡ ግን ይህን የሚያደርገው እናንተን ለመጥቀም ሳይሆን ሊጠቀምባችሁ ነው፡፡ ትኩስ ኃይል፣ብሩህ አእምሮ እና የፈጠራ ችሎታ እናንተ ዘንድ እንዳለ ሕወሓት ኢህአዴግ አሳምሮ ያውቃል፡፡ እናም፣በመጀመሪያ ያነጣጠረው ጥራት ያለው ትምህርት እንዳታገኙ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ይህ ራሱ የፈጠራው የትምህርት ጥራት ችግር እየተባባሰ መምጣቱን ራሱ በሚቆጣጠረው ሚዲያ ለይስሙላ ያህል እያስተጋባው ነው፡፡ አዛኝ ቅቤ አንጓች የሷል ይህ ነው፡፡ ምክንያቱ ግልፅ ነው፡፡ ወጣቶች ጥራት ያለው ትምህርት ካገኙ እንደ ጥላሁን ግዛው፣እንደ ብርሃነ መስቀል ረዳ፣እንደ ዮሐንስ ስብሐቱ፣እንደ ገብሩ ገብረወልድ፣እንደ መስፍን ካሱ፣እንደ ገበየሁ ፈሪሣ ወዘተ ሁሉንም ነገር መጠየቅ ይጀምራሉ፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ ይህን ነው እንደ ጦር የሚፈራው፡፡

ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ፈንታ በወጣቶች ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ በሆነው የፍቅርና የወሲብ ስሜት ላይ በማተኮር እናንተ ወጣቶችን ከትክክለኛው የእውነት ፍለጋ ሃዲድ ገፍትሮ አስወጥቷችኋል፡፡ በዚህም መሠረት ምርጥ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮችን ከሥራ አባሮ በየካምፓሱ የፍቅርና የወሲብ ፊልሞችን ያሳያል፡፡ በመሠረቱ ዕውቀትና ፍቅር ተፃራሪ አይደሉም፤ እንዲያውም አውነተኛ ፍቅር የሚመነጨው ከጥልቅ ዕውቀት ነው፡፡ ወሲብ የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ፈንጠዝያ ነው፡፡ (sex is a celebration of love)፡፡ ሌላ ነገር አይደለም፡፡ ገዥው ፓርቲ ወሲብን የሚጠቀምበት የእናንተን አእምሮ ለማላሸቅ ነው፡፡ የላሸቀ አእምሮ ደግሞ አይጠይቅም፤አይመራመርም፡፡ መጠየቅ አትችልም፤መመራመር አትችልም ሲባልም፣ሰብዓዊ መብቴ ነው ብሎ አይቃወምም፡፡

የፕሌቶን፣የአሪስቶትልን፣የአርኪሚዲስን፣የኮፐርኒክስን፣የአዳም ስሚዝን፣ የዘራያዕቆብን፣ የያሬድን፣ የማርክስን፣ የቮልቴርን፣የአንስታይንን፣የስቲፈንግ ሆውኪንግን፣ወዘተ ሕያው ስምና ሥራ እየጠቀሳችሁ እንዳትመራመሩ፣ እንዳትጠይቁ፣ እንዳትወያዩ፣ በጥራዝ ነጠቅነት በየጊዜው የሚቀፈቅፋቸውን "ፍልስፍናዎች" እንደ እንቆቆ ሊግታችሁ እየሞከረ ነው፡፡ ራሱ እንኳን ትርጉማቸውን በደንብ የማያውቃቸውን ጊዜ ያለፈባቸውን የርዕዮት መግለጫ ንድፈሃሣቦች በግድ እየጫነባችሁ ነው፡፡ እስኪ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ ብሎ ነገር ምንድን ነው?" በማርክሳዊ ርዕዮት ይህ ጥልቀት ያለው ፍልስፍና ሊሆን ይችላል፤ ግን "ነጭ ካፒታሊዝም" ነው የምከተለው ለሚለው ግን ይህ ቃል ፈፅሞ ምንም ትርጉም የለውም፡፡ ለካፒታሊስት ሥርዓት ተስማሚው የርዕዮት ንድፈሃሣብ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ሳይሆን "ዴሞክራሲያዊ አብዮት" ነው፡፡ ማለትም በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ አረብ ሀገሮች የተካሄደው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዓይነት ነው፡፡ ሌሎች ሕወሓት/ኢህአዴግ ራሱ በደንብ የማያውቃቸው ግን በየቀኑ እንደ በቀቀን የሚደግማቸው ቃላትና የርዕዮት መግለጫዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ ለምሳሌም፣ "ልማታዊ መንግሥት፣ኪራይ ሰብሳቢነት፣ነፍጠኝነት፣ትምክህተኝነት፣ብሔርተኝነት ወዘተ" በየቀኑ የምንሰማቸው አደናጋሪ ቃላትና ሐረጐች ናቸው፡፡ አሁን እኔ እንደምጠይቀው፣ እንዳትጠይቁ፣እንዳትመራመሩ ደግሞ አካዳሚያዊ ነፃነታችሁን ገፏችኋል፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶች ሆይ ሕወሓት/ኢህአዴግ ከአጠመደላችሁ ወጥመድ ራሳችሁን ነፃ ለማውጣት ታገሉ፡፡ በጐሰኝነት እንዴት እንደበከላችሁ ደግሞ ትንሽ ላጫውታችሁ፡፡ ሕወሓት ሁሉንም ብሔረሰቦች አቅፎ ያታግል የነበረውን "ኢሕአፓ"ን የ"አማራ ቡችላ" ነው በማለት ሕወሓትን አምኖ በትግራይ አካባቢ ይንቀሳቀስ የነበረውን ይህን የፖለቲካ ድርጅት በተለይ አሲምባ በሚባለው አካባቢ፣ሕወሓት የነበረውን የትጥቅ የበላይነት በመጠቀም ከእንቅስቃሴ ውጪ ማድረጉ በታሪክ መጻሕፍት ተመዝግቦአል፡፡ እንደሚታወቀው ከኢህአፓ ወሳኝ መሪዎች መካከል ብዙዎቹ የትግሬ ብሔረሰብ አባላት የነበሩ ናቸው፡፡ እነ ብርሃነ መስቀል ረዳን፣እነ ዘሩ ክሾንን ወዘተ መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ሕወሓት የጭፍን ጐሰኞች ቡድን እንደነበረውና አሁንም ከዚሁ ጠባብነት እንዳልተላቀቀ ነው፡፡ ከሻዕቢያ ጋር በመሆንም የደርግን ሕብረብሔራዊ ሠራዊት "ያሸነፈው" ይኼው የጭፍን ጐሰኞች ስብስብ ነው፡፡

የደርግ ሠራዊት የተሸነፈው በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ወታደራዊ አመራር ድክመት እንጂ፣የቆመላት ኢትዮጵያዊነት ከጐሰኝነት ያነሰ ዓላማ ሆኖ አይደለም፡፡ ሕወሓት ግን ወታደራዊ ድሉን ብሔርተኝነት /ጐሰኝነት/ በኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀዳጀው ድል ነው ብሎ ነው የሚያምነው፡፡ ይህ በጣም የተሳሳተ ግንዛቤ ነው፡፡ የደርግ መንግሥት ለሕዝብ የሚጠቅሙ እንደ መሬት አዋጅና የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ዓይነት ጥቂት የማይባሉ ርምጃዎች የወሰደ ቢሆንም በሌላ ገፅታው ፀረ ዴሞክራሲ ስለነበርና የኢኮኖሚ ፖሊሲውና አመራሩ ለዕድገት አመቺ ስላልነበር፣በብዙኋኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጣልቶ እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው ሐቅ ነው፡፡ ስለዚህ ሕወሓት በወታደራዊ ፍልሚያው ደርግን "ሊያሸንፍ" የቻለው ከወታደራዊ አመራሩ ድክመት በተጨማሪ ደርግ በአብዛኛው ሕዝብ ተጠልቶ ስለነበር ነው፡፡

ሕወሓት ግን ይህን አመለካከት አይቀበልም፡፡ እሱ የሚያምነው "በጐሳ የተደራጀ ሠራዊት ያሸንፋል" በሚለው መፈክር ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ ሥልጣን ይዞም እንኳን ከዚህ አስተሳሰቡ አሁንም አልተላቀቀም፡፡ በፖለቲካው "ኢህአዴግ" የሚባል ሕብረብሔራዊ ጭምብል እንደፈጠረው ሁሉ በሠራዊት አደረጃጀቱም "የብሔር ተዋፅዖ" በሚል ሽፋን "ሕብረብሔራዊ ሠራዊት" መሥርቼአለሁ እያለ ይዋሻል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የሰራዊቱ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች በሙሉ በራሱ ብሔር አባላት የተያዙ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ቦታዎችና የጀኔራሎቹን ቁጥር ጠጋ ብሎ በተመለከተ ይኼም ብቻ አይደለም፤ በደህንነት እና በፖሊሲ ሠራዊት ውስጥ ያሉ ወሳኝ ቦታዎች በሙሉ የተያዙት በራሱ ብሔረሰብ አባላት ነው፡፡ ፖለቲካውን ደግሞ ማን እንደሚያሽከረክረው ሁላችንም በደንብ የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡

ሕወሓት የጐሣ የበላይነቱን በወታደራዊ ኃይል ከጨበጠ በኋላ በፖለቲካውና በኢኮኖሚውም መስክ

ወደ ገፅ 16 ዞሯል

# ኢህአዴግ ለመምህራን ያደረገው የደመወዝ ጭማሪ ሠላማዊ ትግሉን አያቀዘቅዘውም

ጎይቶም ሸዊት

የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ከመጋቢት 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን የደመወዝ ጭማሪ ማድረጉን ገልጿል፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ፣የተደረገው ጭማሪ ከ61 ብር እስከ 73 ብር ገደማ ብቻ ነው /ሰንደቅ፣መጋቢት 5፣2004/፡፡ መንግሥት ይህንንም ለማድረግ የተገደደው ትርፍ ገንዘብኖሮት ሳይሆን፣ወደ ሦስት መቶ ሃምሣ ሺ (350,000) የሚገመቱት መምህራን የሥራ ማቆም አድማ ሊመቱ ይችላሉ በሚል ሥጋት ነው፡፡ በዚህ ላይ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ከፍተኛ ጫና አለ፡፡ እንደሚታወቀው በአወሊያ ት/ቤት የተጀመረው የሙስሊሙ ሕብረተሰብ የመብት ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ ወደ ግዙፍ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እየተቀየረ ነው፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ ሕዝቡን ሳያማክር በሱማሊያ በድጋሚ እያደረገ ያለው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትም አልጋ በአልጋ እንዳልሆነለት ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን እየዘገቡ ነው፡፡ በኢኮኖሚው መስክም ያሉት መጠነ ሰፊ ችግሮች እንደቀጠሉ ናቸው፡፡

በዚህ ሁሉ ውጥረት መካከል በሚቀጥለው ዓመት መግቢያ ላይ ይደረጋል የተባለው የአዲስ አበባ ምርጫ እየደረሰ ነው፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ መላ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር እንደሚችሉ ገብቶታል፡፡ በመሆኑም እንደተለመደው ኃይል እና መደለያ ያቀናጀ የምርጫ ዘመቻ ጀምሮአል፡፡ በአንድ በኩል ታዋቂ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን እየደበደበ እያሠራ እያሰቃየና እየገደለ በሌላ በኩል የተለያዩ መደለያዎችን እየሰጠ ነው፡፡ከየቀበሌው ሥራ አጦችን እያፈሰ በሙያ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ እያጐረ ነው፡፡ (ለምሳሌ፣እንደ ኮብል እስቶን ላሉ ጥቃትን ሥራዎች)፡፡ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲንና" የ"ልማታዊ መንግሥትን" ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው እያለ፣በየወረዳው ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማካሄድ፣በውሎ አበል መልክ ለተቸገሩና ለተራቡ ወጣቶች የኪስ ገንዘብ እያደለ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ገንዘብ የሚያወጣው ከሕዝብ ከተሰበሰበ የመንግሥት በጀት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዴሞክራሲ ግንባታ ተብሎ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከተመደበው አሥር ሚሊዮን ብር (10 ሚሊዮን ብር) ሰባት ሚሊዮን ብር (7 ሚሊዮን ብር) ለራሱ ወስዶ፣የቀረውን ከሰባ (70) በላይ ለሆኑት የራሱ ተለጣፊ የፖለቲካ ድርጅቶች አከፋፍሏል፡፡ በጣም የሚያስገርመው በተጭበረበረው የ2002 ምርጫ እንኳ ከኢህአዴግ ቀጥሎ ሁለተኛ ለወጣው መድረክ የተሰጠው ገንዘብ ከአራት ሺ ብር በታች መሆኑ ነው፡፡ አራት ሺ ብር የአንድ ቀን ሕዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ እንኳን አይበቃም፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን መድረክን በአደባባይ ለመሳደብና ለማውረድ የተቃጣ የምፅዋዕት ድርጊት እንደመሆኑ መድረክ ገንዘቡን ለምርጫ ቦርድ ተመላሽ አድርጓል፡፡

አሁን ለመምህራን የተደረገውም የደመወዝ ጭማሪ ከስድብ የሚቆጠር ይመስለኛል፡፡ የዋጋ ንረት በዓመት በአማካይ ከ35 በመቶ በላይ በሚያድግበት ሀገር፣ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ከአምስት በመቶ (5 በመቶ) ያልበለጠ የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ ምን ትርጉም ይወጣል? ይህንን በምሳሌ ማስረዳቱ ነገሩን ይበልጥ ግልፅ ያደርገዋል፡፡ ለምሳሌ የአንድ መምህር የወር ደመወዝ አንድ ሺ ብር (1000) ብር ነው እንበል፡፡ ደመወዙን በሙሉ አንድ ኩንታል ጤፍ ለመግዛት ያውለዋል ብለን እናስብ፡፡ የአንድ ኩንታል ጤፍ አንድ ሺ ብር ቢሆንና ዋጋው በ350 ብር ቢጨምር ከጭማሪው በኋላ የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ 1350 ብር ይሆናል፡፡ የመምህሩ ደመወዝ የጨመረው ግን በአምስት በመቶ ብቻ በመሆኑ፣ጭማሪውን አካትቶ ደመወዙ ቢጨመርም በፊት ይገዛ የነበረውን አንድ ኩንታል ጤፍ እንኳን መግዛት አይችልም፡፡ አሁን ሕወሓት/ኢህአዴግ ለመምህራን አደረግሁ የሚለው የደመወዝ ጭማሪ ይህን የመሰለ ነው፡፡

መምህራን ለሕወሓት/ኢህአዴግ እንዲህ በቀላሉ የሚታለሉ አይመስለኝም፡፡ ብዙ ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታ ያላቸው ዜጐች ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው የሕወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣኖችና ካድሬዎች ከደመወዛቸው በተጨማሪ መሬት በነፃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሁለትና ሦስት ቪላዎች ያከራያሉ፤ከአንድም ሁለት መኪናዎች ከነዳጅ ወጪው ይመደብላቸዋል፤ ሲታመሙ ውጭ ሀገር ሄደው በመንግሥት ወጪ ይታከማሉ፤ወዘተ፡፡ የሕወሓት/ኢህአዴግ ቅጥረኛ "መምህራን" ደግሞ ደመወዝ የሚከፈላቸው በልዩ ስኬል ነው፡፡ ለምሳሌ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው ኢኮኖሚስቶች በወር ከሰላሣ ሺ ብር (30,000 ብር) በላይ እየተከፈላቸው የሚሰሩ አሉ፡፡ እነዚህ "ምሁራን" "አዲስ የወጣው የሊዝ አዋጅ ሰፊውን ሕዝብ ይጠቅማል በሀገራችን የደረሰው የዋጋ ንረት ከውጭ ሀገር የተዛመተ ነው እንጂ በሀገር ውስጥ ከልክ ያለፈ የገንዘብ ሕትመት ያመጣው ችግር አይደለም፤ ድርቅ ቢኖርም ረሀብ የለም፤በኢትዮጵያ ድህነት እየቀነሰ ነው፤ኢኮኖሚው በዓመት አሥራ አንድ በመቶ በላይ አድጐአል፤ ገበሬዎች ሚሊየነር እየሆኑ ነው፤ በአዲስ አበባ የንፁሕ ውኃ አቅርቦት ሽፋን ከሰማኒያ በመቶ በላይ ደርሷል፤ወዘተ" እያሉ የተራቀቀ የሂሣብ ቀመር ጭምር እየተጠቀሙ ሽምጥጥ አድርገው ይዋሻሉ፡፡

ሕወሓት/ኢህአዴግ ከዘመነ ኃ/ሥላሴ ጀምሮ በወጥነት ያገለግል የነበረውን የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል በመሻር የመንግሥት የደመወዝ በጀቱን /አሁን በዓመት ከ 20 ቢሊዮን ብር በላይ ነው/ ሠራተኞቹን በጥቅም ከፋፍሎ ለመግዛት እየተጠቀመበት ነው፡፡ እንደ ሀገር ውስጥ ገቢ ያሉ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚገለገሉበት የደመወዝ ስኬል ለመምህራን ከተመደበው የደመወዝ ስኬል ቢያንስ በአምስት እጥፍ ይበልጣል፡፡ ለምሳሌ የገቢዎች ጉሙሩክ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ መላኩ ፈንታ የወር ደመወዛቸው ብቻ አስራ ሰባት ሺ አምስት መቶ (17,500) ነው፡፡ አቶ መላኩ ይህን ውለታ ለመክፈል ሲሉ ደሃውን ሕዝብ ከአቅሙ በላይ ቀረጥና ግብር እየጫኑ ፍዳውን እያሳዩት ነው፡፡ ለመከላከያ ለደህንነት እና ለፖሊስ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችና ኃላፊዎች የሚሰጡት ጥቅማጥቅሞች እጅግ ከፍተኛ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ሁለትና ሦስት ቢላዎች እያከራዩ በወር ቢያንስ ከመቶ ሃያ ሺ ብር በላይ የሚያገኙ አሉ፡፡ እዚህ ላይ አንድ ፈገግ የሚያሰኝ ገጠመኝ ላጫውታችሁ፡፡ አንድ የሕወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣን በሚመራው የመንግሠት መ/ቤት ያሉ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ሲጠይቁት፣ "ደመወዝ? የምን ደመወዝ?" ብሎ መለሰላቸው ይባላል፡፡ ሰውዬው ከሚያከራያቸው ቪላዎች በወር መቶ አሥር ሺ ብር ስለሚያገኝ፣በባንክ ሂሣቡ የሚገባለትን የወር ደመወዝ ጨርሶ ረስቶታል፡፡

በእኔ ግምት ከሁሉም የመንግሥት ሠራተኞች ዝቅተኛ የደመወዝ ስኬል ያላቸው መምህራን ናቸው፡፡ ለምሳሌ አሁን ተሻሻለ በተባለው የደመወዝ ስኬል አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ጀማሪ መምህር የሚያገኘው ደመወዝ 1600 ብር ያህል ብቻ ነው፡፡ ይህ ያልተጣራ ደመወዝ (gross salary) እንደመሆኑ የሥራ ግብር እና የጡረታ አበል ሲቀነስለት ከ1200 ብር አይበልጥም፡፡ ይህን የሚያገኝ መምህር እንዴት ሊኖር ነው? ባለ ሁለት መኝታ ቤት ኮንዶሚኒየም ለመከራየት ቢያንስ በወር 1500 ብር ያስፈልጋል፡፡ ለመሀል ከተማ ቅርብ በሆነ አካባቢ አራት በአራት (4x4) ሜትር የሆነች አንዲት ክፍል የጭቃ መኖሪያ ቤት ለመከራየት ደግሞ እስከ 600 ብር ያስፈልጋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የመጨረሻውን እርካሽ ምግብ ለመመገብ፣በቀን ቢያንስ አርባ ብር /በቀን ሦስት ጊዜ ለመብላት/ ይጠይቃል፡፡በዚህ ስሌት መሠረት፣የመምህራን ደመወዝ ለምግብ ብቻ እንኳን የሚበቃ አይሆንም፡፡

ሕወሓት/ኢህአዴግ በሀገራችን የመንግሥት ሠራተኞችን የደመወዝ ስኬል ምስቅልቅሉን ያወጣው ሕዝቡን ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸው ነው፡፡ የደመወዝን የመግዛት ኃይል እንዲያሽቆለቁል ያደረገው ደግሞ የዘረጋውን የሙስና ሥርዓት ወጪ ለመሸፈን ከሕዝብ በታክስና ቀረጥ መልክ የሚሰበሰበው ገንዘብ ስለማይበቃው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እያዘዘ በገፍ የሚያሳትመው ገንዘብ ከምርት አቅርቦት በእጅጉ ስለበለጠ ነው፡፡ በአንድ ወቅት የዓለም ባንክ ተወካይ በአብዛኛው መንግሥት በገፍ በሚያሳትመው

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# የአቶ መለስ እዉነተኛ የሥልጣን መሠረት ማን ነዉ?



ያዕቆብ ልኬ

በለጠ ጎሹ ወ/ሚካኤል የተባሉ ሰዉ "ሠላማዊ ትግል እና የአቶ መለስ የሥልጣን መሠረቶች" በሚል ርዕስ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 31 ማክሰኞ የካቲት 20 ቀን 2004 ዓ.ም. ባወጣዉ እትም ላይ "የአቶ መለስ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሽፋኖች" ሰፊ መሆናቸዉን ካስረዱ በኃላ የሚከተለዉን ብለዋል፡-

" ... ‹የአቶ መለስ› እዉነተኞቹ የሥልጣን መሠረቶች ... በአብዛኛዉ ከአንድ ብሔር የተወጣጡ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዥ መኮንኖችና ኃላፊዎች እንዲሁም የአሜሪካ እና የሌሎች ምዕራባዉያን መንግሥታት ዕርዳታና ድጋፍ ናቸዉ፡፡" ብለዋል፡፡

ጽሑፉ ሁለት ሀሳቦች የያዘ ሲሆን በእነሱ ላይ የራሴን አስተያየት ከመስጠቴ በፊት መጀመሪያ በአቶ መለስ አምስት የማደናገሪያ ቃላት ላይ ስምምነት እንዲኖረን እተረጉማቸዋለሁ፡፡ ከዚያም በሁለተኛዉ የጽሑፌ ክፍል የአቶ መለስን እዉነተኛ የፖለቲካ ሥልጣን መሠረት አመለክትና በመጨረሻ አጠቃልላለሁ፡፡

የአቶ መለስ ማደናገሪያ አምስት ቃላት

ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ፕሬዝደንት፣ ሕዝብ እና ሕዝቦች የሚሉ ቃሎች አቶ መለስ እና ፓርቲያቸዉ የኢትዮጵያን 82 ሚሊዮን ሕዝብ ለከፋፍለህ ግዛ ሥርዓታቸዉ እንዲመች፣ ከመደበኛዉ የዓለም-አቀፍ ትርጉም ዉጭ፣ እንደፈለጉት ተርጉመዉ የሚጠቀሙባቸዉ ቃላት ናቸዉ፡፡ ይህ ሕዝብ ግን በታሪክ ሂደት በብዙ ሽህ ዘመናት አንድነት የመሠረተ፣ በክፉና በደጉ አብሮ የኖረ፣ በቀላሉ የማይደናገር፣ ግን ባሕሉ ሆኖበት፣ እስቲ 'ይደር' በማለት ሁኔታዎችን በአስተዉሎት እና በቻይነት፣ የተሻለ ሀሳብ ይመጣል ብሎ፣ የሚጠብቅ ሕዝብ ነዉ፡፡

"ብሔር" ማለት ሀገር ነዉ፡፡ ሀገር ደግሞ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ብሔረሰቦች፣ በአንድ በታወቀ ድንበር እና መንግሥታዊ ሥርዓት ዉስጥ ተጠቃልለዉ፣ በዘርና በሀይማኖት ሳይከፋፈሉ፣ በጋብቻ፣ በንግድ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ኑሮ እና በባህል ተሳስረዉ፣ የሥራ ቋንቋ ጨምሮ፣ በአንድ የሕግ ጥላ ሥር በመከባበር፣ በመደማመጥ እና በመቻቻል አብሮ፣ በአንድነት የሚኖር ሕዝብ ነዉ፡፡

ከዚህ ከብሔር እና ከሀገር ትርጉም አንፃር ከ82 ብሔረሰቦቻችን ዉስጥ አንዱም የብሔርን ወይንም የሀገርን መለኪያ ለብቻዉ የሚያሟላ የለም፡፡ መመዘኛዉን የሚያሟላ ኢትዮጵያ ሀገራችን ብቻ ነች፡፡

ብሔረሰብ፣ ከብሔር የሚለየዉ፣ የታወቀ አንድ የጋራ ቋንቋ እና ብዙ ጎሳዎች ያለዉ አንድ ሕዝብ ሲሆን፣ በመንግሥትነት እና በሀገርነት ግን አይታወቅም፡፡ ብሔር የሚባለዉ ግን፣ አንድ ብሔረሰብ ወይም ከዚያ በላይ እና ብዙ ጉሳዎች በአንድ በታወቀ መንግሥት ሥር ተጠቃልለዉ የሚኖሩ፣ የአንድ ሀገር ሕዝብ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት 82 ብሔረሰቦቻችን እንጂ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች አይባሉም፡፡ ስለዚህ ጸሐፊዉ በጽሑፋቸዉ "ከአንድ ብሔር" ያሉትን "ከአንድ ብሔረሰብ" በማለት እንዲያስተካክሉ በአክብሮት እጠይቃቸዋለሁ፡፡

እንደ ብሔር እና ብሔረሰብ ሁሉ ሕወሓት ለከፋፍለህ ግዛዉ ዓላማዉ እንዲጠቅመዉ በፌዴራል ኢትዮጵያ መንግሥት የታቀፉትን እያንዳንዱን የዘጠኝ ክልሎች አስተዳዳሪዎች ፕሬዝደንቶች ብሎ ሰይሞአቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ አንድ ፕሬዝደንት ሳይሆን 10 ፕሬዝደንቶች እንዲኖራት ተደርጋለች፡፡

በዚህ አንፃር የሌሎች ሀገሮች ልምድ መመልከት የሕወሓትን ስዉር ዓላማ የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ ለምሳሌ አሜሪካንን እንዉሰድ፡፡ ሕንድን ወይም ብራዚልን ወይም ሌሎች ሀገሮች መዉሰድ ይቻላል፡፡ ዉጤቱ ተመሳሳይ ነዉ፡፡

አሜሪካ ከፌዴራል ዋና ከተማ ሌላ 50 የፌዴራል ክልሎች አሉዋት፡፡ ሆኖም አንድ ፕሬዝደንት እና 51 አስተዳዳሪዎች እንጂ 51 ፕሬዝደንቶች የሉዋትም፡፡ የእያንዳንዱ ክልል መሪ አስተዳዳሪ ወይም Governor ተብሎ ይጠራል፡፡ ፕሬዝደንት አይባልም፡፡ ታዲያ ሕወሓት ለምንድን ነዉ የእኛዎቹን የፌዴራል ክልሎች መሪዎች (አስተዳዳሪዎች) ከማለት ፕሬዝደንቶች ማለት የመረጠዉ? በሚከተሉት ምክንያቶች ማሰብ ይቻላል፡፡

አንደኛዉ፣ ሀገራችንን በብሔረሰብ በመከፋፈሉ፣ ብሔረሰቦች እኩል ናቸዉ የሚለዉን፣ በተግባር ሳይሆን እንደለመደዉ በቃላት፣ ለመሸንገል የእያንዳንዱን ክልል መሪዎች ፕሬዝደንት በማለት እኩልነታቸዉን ለማሳየት አስቦ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ ሌላ ግን የኢትዮጵያ ፕሬዝደንት የዘጠኙም "ፕሬዝደንቶች" የበላይ በመሆኑ ከእርሱ ጋር እኩል ናቸዉ ለማለት ፈልጎ እንዳልሆነ ወይም "አስተዳዳሪ" የሚለዉ ቃል የፊዉዳል ቅሪት ነዉ በማለት ከመጠቀም ተቆጥቦ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡

ሌላኛው ምክንያቱ መሪዎቹን በማሞካሸት እነሱን ለስዉር ዓላማዉ ተገዥ ለማድረግ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ማንም የክልል መሪ በዚህ ስም እንደማይሸነገል ማሰብ ይቻላል፡፡

የሕወሓት 82 ብሔረሰቦቻችንን ሌላዉ የመከፋፈያ ዘዴ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ" በማለት ፋንታ "የኢትዮጵያ ሕዝቦች" ማለት ነዉ፡፡ በአንድ ሀገር ዉስጥ ብዙ ብሔረሰቦች ቢኖሩም፣ ማንም ማህበረሰብ ሕዝብ ሊባል እንደሚችል ሁሉ፣ እያንዳንዱ ብሔረሰብም ሕዝብ መባሉ አነጋጋሪ ባይሆንም፣ አንድነትን ከልዩነት አጉልቶ ለማሳየት ሲባል(ለሕዝቦቹ ጠቃሚዉ እሱ ነዉና!) የአንድ ሀገር ሕዝብ እንጂ የአንድ ሀገር ሕዝቦች አይባልም፡፡ የማንኛዉም የዓለም ሀገር ልምድ የሚያረጋግጠዉ ይህንኑ ነዉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ግንኙነት በጣም እየጠነከረ ከመጡት ሀገሮች እንጀምር፤ ቻይና እና ሕንድ፡፡

በዊኪፔዲያ መረጃ መሠረት ቻይና 56 የሚሆኑ ብሔረሰቦች አሉዋት፡፡ ሕንድ ከ1652 በላይ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች አሏት፡፡ ሁለቱም ሀገሮች የቻይና ሕዝብ፣ የሕንድ ሕዝብ፣ እየተባሉ እንጂ የቻይና ሕዝቦች፣ የሕንድ ሕዝቦች፣ ተብለዉ አይጠሩም፡፡ የምዕራቡን ዓለም እንመለከት፡፡

አሜሪካ፣ ከዓለም ዙሪያ የተሰባሰቡ፣ የብዙ ብሔረሰቦች ጥርቅም ነች፡፡ ሆኖም የአሜሪካ ሕዝብ እንጂ የአሜሪካ ሕዝቦች ተብላ አትታወቅም፡፡ ታላቋ ብሪታኒያን እንዲሁ ማየት ይቻላል፡፡

በመላዉ ዓለም ያሉ ሀገሮች እያንዳንዳቸዉ ብዙ ብሔረሰቦች ቢኖራቸዉም፣ ራሳቸዉን እንደ አንድ ሕዝብ በመቁጠር ሕዝብ ሲሉ፣ የእኛዉ የአቶ መለስ ፓርቲ እና መንግሥት፣ ሕወሓት-ኢህአዴግ፣ ለምንድን ነዉ የኢትዮጵያን ሕዝብ "የኢትዮጵያ ሕዝቦች" የሚለዉ? ከላይ እንዳልኩት ባለማወቅ ሳይሆን ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸዉ በማቀድ ነዉ፡፡

ወደ ገፅ 7 ዞሯል

# የጠመንጃ ፓለቲካ የት ያደርሰን ይሆን?

(በአሻግሬ መሸሻ )

አምባገነናዊ መንግስትን ወይንም ኢ-ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን አስወግዶ በምትኩ ለሀገርና ለሕዝብ ደህንነት የሚቆም ስርዓትን ለመታደግ ሰላማዊ ትግል ወደ መፍትሔ የሚያመራ መስመር ነው፡፡

ይህ ማለት ህዝባዊ ጥቅምና ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሕዝቡን አታግሎ በዲሞክራሲያዊ የምርጫ ስርዓት በሕዝብ ፍላጎትና ፈቃደኝነት የማይፈልገውን ስርዓት አስወግዶ በምትኩ ህዝባዊ ስርዓትን ማስፈን ነው፡፡ የነበረው ስርዓት ለሰላማዊና ለዲሞክራሲያዊ ትግል ቀና ምላሽ እንዲሰጥ በሕዝብ ድምፅ ቀጥቶ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡

ከሰላማዊ ትግል እና ከትጥቅ ትግል ማማረጥ በስልጣን ላይ ባለው ስርዓትና ባህሪ የሚወሰን ቢሆንም በየትኛውም መመዘኛ ግን ከትጥቅ ትግል ይልቅ ህዝባዊ መሠረት ያለው ሰላማዊ ትግል ምንያህል ተፈላጊና አዎንታዊ እንደሆነ በተለይም የዘመናት የጦርነት ታሪክን ላስተናገደች ሀገር ለምርጫ የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው እኛም የሠላማዊ ትግል አምባሳደሮች ጦርነትንና ጦረኛ መሆንን አጽንኦት ሰጥተን የምንቃወመው፡፡ ይህን እውነታ መሠረት በማድረግ ዛሬ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስናስተውል ግራ መጋባትና ምስቅልቅል ያለ ሆኗል፡፡ በተለይም የተቃዋሚዎች ጠንካራ ሆኖ አለመገኘት በህዝባችን ላይ ዛሬም እንደትላንቱ ሠብዓዊ መብት እንዲረገጥ፤ ሰዎች ያለበቂ ምክንያት ከስራ ገበታቸው እንዲፈናቀሉ፤ ከነቤተሰቦቻቸው በርሃብና ርዛት እንዲቀጡ፤ በኑሮ ውድነት ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ይገፋሉ፤ ያለፍ/ቤት ትዕዛዝ በአገዛዙ ሹመኞች የቃል ትዕዛዝ ብቻ በታጣቂዎች ወይም በአገዛዙ ካድሬዎች እየታፈኑ በእየእስር ቤቱ ይታጎራሉ፤ በሽብር ስም ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን እያነቁ እስር ቤት ማጎር የተለመደ ሆኗል፡፡

ለምሳሌ፡-የመድረክ አመራሮችና የመኢአድ አባሎች ያለበቂ ምክንያት በየቦታው አሁንም ይታሰራሉ፡፡

ሌላው ተዋቂው የፖለቲካ ተንታኝና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ጨምሮ ሌሎች ጋዜጠኞችም የእስራቱ ሠለባ ሆነዋል፡፡ ከዚህም ውጭ ያሉትን ተዋቂ ጋዜጠኞችን መንግስት አሁንም የማስፈራራትና የአመለካከትና ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብትን ተነፍገዋል፡፡ እንዲሁምጋዜጠኞችን ደህንነቶች እያደረሱባቸው ያለውን ወከባ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህን ካልኩ ዘንደ ትንሽ ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች ልጥቀስ፡-

በሕገ - መንግስቱ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ "ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሠለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል" ይላል ፡፡ ይህንን ድንጋጌ የሰጠን ኢህአዴግ ሳይሆን ሕገ-መንግስቱ ነው፡፡ በተጨማሪም በሕገ -መንግስቱ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንዲህ ይላል፡-

"ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው፡፡ ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት ፤ በስነ-ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ ፤ የመቀበልና፤ የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል" ይላል፡፡ ይህንን መርህ ግን ገዥዎቻችን ሙሉ በሙሉ ጥሰውታል፡፡

ለምሳሌ ፡- መረጃ የመቀበልና የማሰራጨት የሚለውን እንመልከት፡-

በአሁኑ ሰዓት እንኳን ቀጥተኛ ሽብር ይቅርና ከቤተሰብ አባል አንዱ ሆስፒታል ገብቶ ቀዶ ጥገና ቢያካሂድና ለወዳጅ ዘመድ "ኦፕሬሽኑ ተሳክቷል" ብለን ለወንድሞቻችን ለእህቶቻችን/ በስልክ ብንናገር ቀጥታ የሚያስወነጅል ሆኗል፡፡ የአውራአምባ ታይምስ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬን እና የፍትሕ ጋዜጣ አምደኛ መ/ርት ርዕዮት አለሙን ምን ብለው እንደፈረዱባቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት ውጭ ያሉ ቤተሰቦቻችን በስልክ እንደፈለግን ማውራት የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ በኢንተርኔት ስለሀገር ማውራት የማይታሰብ ነው፡፡ ለዚህም ነው የመድረክ አባላት "ሕገ-መንግስታዊ መብታችን ይከበር" እያሉ በተገኘው አጋጣሚ ሲጮሁና እውነቱን ሲያጋልጡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፓርላማውን ወንበር ያለአግባብ በቡጢ እየደበደቡ ለማስፈራራት የሚሞክሩት፡፡ ታዲያ ሕገ - መንግስቱን ራሳቸው እየጣሱ ዜጎች እንዴት ማክበር ይችላሉ?

ዛሬም ካለፉት ስርዓት በባሰ መልኩ ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን አልተከበሩም፡፡ የመሰብሰብ ፤ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብታችን፤ በነፃነት የመዘዋወር መብታችን ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት አላገኙም፡፡ በሐገሪቱ በሁሉም አቅጣጫ ማለት ይቻላል፤ በፖለቲካ አመለካከት ብቻ መከሰስ፤ ከተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲወጡ የማድረግ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡ ይህም ችግር በዛሬዎቹ ገዢዎቻችን የመጡ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ተገንዝቧል፤ አውቋልም፡፡ ይህን ሁሉ ችግር አስወግዶ ትክክለኛውን የማያዳግም የሕዝብ የበላይነት ለማምጣት ዛሬም እንደትላንቱ ከባድና መራራ ትግል ያስፈልጋል፡፡ ግን ምን ዓይነት ትግል? ሠላማዊ ወይምስ የትጥቅ ትግል? ምላሽ የሚያሻው ጥያቄ ነው፡፡

የትጥቅ ትግሉን ውጤት አይተነዋል፡፡ የአንድ ትውልድ ወጣቶችን የጨረሰ ጦርነት ተካሂዶ ደም እንደጅረት ፈሶ ፤ አጥንቶ እንደ እንጨት ተለቅሞ የተገኘው ውጤት በዘር፤ በቋንቋና በጎሳ እየተለያዩ ኢትዮጵያዊነት ስሜትና አንድነት እንዲጠፋና ወንድም ወንድሙን እህት እህቷን አባት ልጁን ፤ ልጅ አባቱን ፤ እንዳያምንና እርስ በርስ የሚያስተናንቅ ሥርዓት ነው የተፈጠረው፡፡ በርግጥም ምንም ቢሆን በጠመንጃ ኃይል ስልጣን ላይ የወጣ መንግስት ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህም ነው የዛሬዎቹ ገዢዎቻችን ስልጣንን የሙጥኝ ብለው ሕዝብና ሀገር እየጎዱ ትውልድ እየገደሉ ያሉት፡፡

በየትኛውም መመዘኛ የትጥቅ ትግል ከሠላማዊ ትግል ሊመረጥ የሚችልበት ጐን የለውም፡፡ በዚህ የምናምን ከሆነ የመረጥነውን ሠላማዊ ትግል ለማካሄድ የወቅቱ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ያህል አመቺ ነው? ይህም አንገብጋቢና ምላሽ ማግኘት ያለበት የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

ሠላማዊ ትግል ለማካሄድ የግድ የመሰብሰብ የመሰለፍ ፤ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ ነፃነት ያስፈልጋል ማለት አይደለም፡፡ እነዚህን ነፃነቶች በተሟላ መልኩ ለማግኘት ራሱ ሠላማዊ ትግል ማለት በደፈናው ለስላሳና ምቹ የማይጎረብጥ የትግል ስልት ነው ማለት ሳይሆን በተቀናጀ መልኩ ጫካ ተገብቶ ከሚካሄድ ከትጥቅ ትግል በመለስ ማናቸውንም መስዋዕት የሚጠይቅ የትግል ስልት ነው፡፡

ለዚህም ነው "ጦርነትን አንሻም፤ እምነታችን ሰላማዊ ትግልን ማካሄድ ነው" ብለን የምናምን ኃይሎች የሕዝብ ድጋፍን በመተማመን ሠላማዊ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማቋቋም ዲሞክራሲያዊ መብቶች አለመከበራቸው በማሰማታችን የሚታፈኑ የሚታሰሩ፤ ከዚህም በከፋ መልኩ በግፍ ቶርች የሚደረጉ መኖራቸው እውነት ነው፡፡ ለዚህም የመድረክ አባላትና የመኢአድ አባላትም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህም መንግስት ለሰላማዊ ትግል መጠናከር ቀና አመለካከት ፈጽሞ የሌለው መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆን የአድነት ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት አቶ አንዱዓለም አራጌ፤ ስለ ህዝባቸውና ሀገራቸው ደህንነት ሲታገሉ "ሽብርተኛ" ተብለው መታሠራቸውም አልበቃ ብሎ በእሥር ላይ እንዳሉ ተስፋ በቆረጠ ነፍስ ገዳይ የሚያሰደበድቧቸው፡፡

በሠላማዊ ትግል እያመን ትግል እንታገላለን እያልን ነገር ግን ሠላማዊ ፖለቲካ መሪዎቻችንና አባሎቻችን እንደሌባና ወንበዴ ያለበቂ ምክንያት ዘብጥያ ሲወረወሩ ፤ ክላሽና ቦምቦ ሳይሆን ብዕርና ወረቀት የተከማቸበትን ቤትና ቢሮአቸውን በአምባገነኖች ሲታመስና ትልቅ እንግልት ሲደርስባቸውና ከዚህም አልፎ በህግ ከለላ ስር ሆነው እየተደበደቡ እያየንና እየሰማን እጃችንን አጣጥፈን በመቀመጥ ተስፋ የምንቆርጥ አይደለንም፡፡ የበለጠ እንድንቆርጥና ሰላማዊ ትግሉን የምር እንድንይዘው እየተፈጠረ ያለው ሁኔታ የግድ ይለናል፡፡ ሠላማዊ መሪዎቻችንን አሣስራን እጆቻችንን አጣጥፈን የምንቀመጥ የዋሆች አደለንም፡፡ የሕዝብና የሀገር ጠላቶች የዛሬው ጥረታቸው እኛ የቀመስነውን ጦርነት እናንተም ቅመሱት ማለት ይመስላል፡፡ ሠላማዊ ትግሉም ተጨናግፎ ሕዝቡን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እየመሩት ያሉት፤ የዛሬዎቹ ገዢዎቻችን ናቸው፡፡ ይህ የመረጡልን መንገድ የእነሱ እንጂ የእኛ ፍላጎት ባለመሆኑ ማንኛውም እውነተኛ ዜጋ ለሠላም የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ በመክፈል ሀገርንና ሕዝብን ከጥፋት መታደግ ነገ ሳይሆን ዛሬ ምላሽ ማግኘት ያለበት የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

## ለመላው ኢትዮጵያውያን ወጣቶች
## <<ወጣቶችና ወቅታዊ የሀገራችን ፖለቲካ>>

**በሚል ርዕስ የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራርና ኢኮኖሚስት ከሆኑት ወንድወሰን ፀጋዬ ጋር እሁድ መጋቢት 16 ቀን 2004 ዓ.ም. በአንድነት ፓርቲ ዋናው ፅ/ቤት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ውይይት ስለሚደረግ ሁላችሁም ተጋብዛችኃል፡፡ አድራሻ፡- ቀበና ከኦሮሚያ ደን ልማት ህንፃ ገባ ብሎ አንድነት ፓርቲ ዋናው ፅ/ቤት አዳራሽ**

**አዘጋጅ**
**የአንድነት ፓርቲ የድርጅት ጉዳይ ወጣቶች ኮሚቴ**


# የቦረና እና ጉጂ ዞን ነዋሪዎች እንዲፈናቀሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው

በኢትዮጵያ በስተደቡብ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ቦረና እና ጉጂ ዞን ቀበሌዎች ያሉ ነዋሪዎች ከቦታቸው እንዲፈናቀሉ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው ገለፁ፡፡

እንደነዋሪዎቹና ታማኝ ምንጮቻችን ገለፃ ከሆነ ነዋሪዎቹ እንዲፈናቀሉ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው አካባቢው በወርቅ ማዕድን የበለፀገ ስለሆነ የሼህ መሐመድ ሁሴን አሊ አላሙዲ ንብረት ለሆነው ለሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኩባንያ ቦታውን ለመስጠት እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ በተለይ በጉጂ ዞን ሻኪሶ ወረዳ በሚገኘው ሬጂ ቀበሌ ነዋሪዎች ከሚኖሩበትና ከሚተዳደሩበት ማሳ ሙሉ ለሙሉ ያለምንም ካሳ እንዲነሱ መደረጋቸውን እሳቸውም ከነቤተሰቦቻቸው ችግር ላይ መውደቃቸው ተጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ዞን በሳቦሩ ወረዳ ቡሪካሮና ቡሪኤጀርሳ ቀበሌ ያሉ ነዋሪዎችም ከሚኖሩበት አካባቢ እንዲነሱ መደረጉን ምንጮቻችን ጠቁሟል፡፡

በቦረና ዞን መልካሶዳ ወረዳ በሚገኘው ሀሎመዴዳ ቀበሌ ደግሞ ኤዲቻ፣ ሎቶሪ፣ አኮቴ፣ ኦዳ፣ ሀንቃሬ፣ ዳዳቡዱ፣ አካባቢ ነዋሪዎች እንዲነሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል ሲሉ ነዋሪዎቹ ተናግረዋል፡፡ ከአሬሮ ወረዳ ቢቢሌ ቀበሌ ደግሞ ዋዩ ቦዳ በሚባል አካባቢ ያሉ ነዋሪዎችም ያለምንም ካሳና ቅድመ ዝግጅት በአስቸኳይ ከቦታቸው እንዲነሱ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በፊትም መንግሥት ለሚድሮክ ኩባንያ የነዋሪዎችን ማሳ ሲሰጥ አካባቢውን እንደሚያለማና ነዋሪዎቹን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ቃል በመግባት እንደሆነና በተግባር ግን እንዳልተፈፀመ ነዋሪዎቹ ያላቸውን ቅሬታ ገልፀዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአካባቢው ነዋሪ በከፍተኛ ሁኔታ ለመጠጥ ውሃ ችግር እንደተጋለጠና በማዕድን ማውጫው አካባቢ ለከፍተኛ የውሃ ወለድ በሽታ እየተጠቁ እንደሆነ እንዲሁም ህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠው ዜጐች ንብረት የማፍራትና ከቦታችን ያለመፈናቀል መብቶቻችን እየተጣሰ ነው ሲሉ ነዋሪዎች ያላቸውን ቅሬታ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡ ነዋሪዎቹ እንዲፈናቀሉ የኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳደርም ነዋሪን በማስገደድና በማስፈራራት ትልቁን ሚና እየተጫወተ እንደሆነ የዜና ምንጮቻችን አስታውቀዋል፡፡

# በሰሜን ጐንደር የፍትህ ሥርዓቱ አደጋ ላይ ነው ተባለ

በሰሜን ጐንደር የፍትህ ሥርዓቱ ጥያቄ ውስጥ እንደገባና ከነፃ ዳኝነት ይልቅ ህብረተሰቡን ተቃዋሚ ነው በሚል በማያውቁት ጉዳይ የወንጀል ክስ እየተመሰረተባቸው ፍ/ቤቶች የፖለቲካ ሥራ እያካሄዱ ነው ሲሉ ነዋሪዎች የተሰማቸውን ቅሬታ ገለፁ፡፡ በህጋዊ መንገድ በተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን የአካባቢው አመራሮች ብልሹ አሰራሮቻቸውን ለመሸፈን ሲሉ የወንጀል ክስ እየመሰረቱ ነዋሪዎችን በማስፈራራትና በማሰር እያሰቃዩአቸው እንደሚገኙ ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ ነዋሪዎቹ ክስ ከተመሰረተባቸው በኋላ በቀጠሮ ብቻ እንዲጉላሉ እንደሚደረግም ተጠቁሟል፡፡ በዚህም ምክንያት የፍትህ ሥርዓቱ አደጋ ላይ ወድቋል ሲሉ ነዋሪዎቹ ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በሰሜን ጐንደር ዞን የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ብርሃኑ ወልዴ የከተማ ቤት ከነቦታው በመግዛታቸው "ሙስና ፈፅመሃል" ተብለው ታስረውና ክስ ተመስርቶባቸው በ10 ሺህ ብር ዋስ ተለቀው ውሳኔ እንሰጣለን በሚል የሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለ12ኛ ጊዜ መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም መቀጠራቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀውልናል፡፡

አቶ ብርሃኑ ወልዴ ከአቶ መንግስቴ አስረስ ጋር በመሆን ከአቶ ሙልጌታ መኳንንት በህጋዊ መንገድ የከተማ ቤት ቦታ በ2000 ዓ.ም ቢገዙም በ2003 ዓ.ም የከተማው መሐንዲስ ሰይድ ገበያው በ5 የሙስና ወንጀል ክስ እንደተመሰረተባቸው አስታውሰዋል፡፡ ነገር ግን አቃቤ ህግ የእሳቸው ስም እና ክስ አብሮ መካተቱ በስህተት እንደሆነ በመሐንዲሱ ላይ ክስ የመሰረተው አቃቤ ህግ እንደነገሯቸው አስታውሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ መሐንዲሱ በ45 ሺህ ብር በዋስ ከተለቀቁ በኋላ አብዛኛው በዋስ ያስያዙት ብር እንደተመለሰላቸው በማስታወስ ወንጀሉን ፈፅመዋል የተባሉትና የተከሰሱት ውሳኔ አግኝተው በነፃ መሰናበታቸውንና የእሳቸው ክስ ግን ለውሳኔ እየተባለ በሰሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ለ12ኛ ጊዜ በመቅጠር ብዙ እየተንገላቱ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ይህ የተፈፀመበትንም ምክንያት አቶ ብርሃኑ ሲያስታውሱ በ2002 ዓ.ም በነበረው ምርጫ ወቅት በሰሜን ጐንደር ዞን መድረክን እያስተዋወቁ ሳለ ከዞኑ የኢህአዴግ አመራሮች "ቅስቀሳውን ብታቆም ይሻልሃል አለበለዚያ ከምርጫ በኋላ እንደምናስርህ እወቅ" የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋቸው እንደነበር አውስተዋል፡፡ ከዚያም በ2003 ዓ.ም ያስጠነቀቋቸው የዞኑ አመራሮች መተግበራቸውን እንደሚያሳይ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ብርሃኑ ጉዳያቸው ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ እንደሆነ፤ ፍ/ቤትም አውቀውም ፋይላቸውን በማዘዋወር ዳኛ ተቀይሯል እንደሚሉ፣ ከመደበኛ ችሎት ውጭ በቢሮ የሚታይበት ጊዜም እንዳለ፣ በችሎት ወቅትም ሰዎች እንዳይከታተሉ እንደሚያስወጧቸው በተደጋጋሚ እንደሚነገራቸው አስታውሰዋል፡፡ አሁንም ቢሆን በሰሜን ጐንደር ያለው የፍትህ ስርዓት አደጋ ላይ መውደቁንና ህዝቡንም እያማረረ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎችም በዞኑ ባለው የመልካም አስተዳደር እጦት አቤቱታና ቅሬታ ስናሰማ የማናውቀው ስም እየተሰጠን ስለምንከሰስና ስለምንታሰር ባሉት የመንግስት አመራሮች እምነት የለንም ብለዋል፡፡ በመግስትና በህዝብ ንብረት ላይም ጥፋት ሲፈፀም አይቶ ለሚመለከተው አካል መጠቆም እንደወንጀል እየተቆጠረ አያገባችሁም እየተባልን ስለሆነ ከዚህ በኋላ ከመንግስት ጋር አብሮ መስራት አስቸጋሪ ሆኗል ሲሉ በተለይም ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

# ቤንቺ ማጂ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ መሆኗ ተገለፀ

- ተፈናቃዮች በምግብ እጥረትና የጤና አገልግሎት አጥተዋል ተባለ
- የመምህራን ደሞዝ ጭማሪ ቅሬታ ፈጥሯል
- የሱርማና የደዚ ጐሳዎች ግጭት እልባት አላገኘም
- በቡና አምራቾች ላይ ካድሬው ችግር ፈጥሯል ተባለ

በደቡብ ክልላዊ መንግሥት ቤንቺ ማጂ ዞን በተለያዩ ችግሮች እየታመሰች መሆኑን የዜና ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "በጉራፈርዳ ወረዳ በሹፒ ቀበሌ የተፈናቀሉት በደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ሽፈራው ሽጉጤና በአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ አያሌው ጐበዜ ስምምነት እነደገና ወደ ሥፍራቸው እንዲገቡ መላካቸው ቢታወስም ቦታቸው ላይ እንዳይሰፍሩ በመከልከላቸው ማጂ ዞን ፖሊስ መምሪያ ሜዳ ላይ ሠፍረው በረሃብና በጤና አገልግሎት እጦት ችግር በመማቀቅ ላይ ናቸው፡፡ ቀይ መስቀልና እርዳታ ሰጪዎች እንዳያገኙዋቸው ታፍነው ይገኛሉ" ብለዋል፡፡ ምንጮቻችን እንደሚሉት 264 አባወራዎች በችግር ውስጥ ስለሚገኙ የሚመለከተው የመንግስት አካል አስቸኳይ መፍትሔ ሊፈልግላቸው ይገባል በማለት ጥሪያቸውን ያቀርባሉ፡፡

ሌላው በቤንቺ ማጂ መነጋገሪያ የሆነው የመምህራን ደሞዝ ጭማሪ ጉዳይ ነው በማለት ምንጮች ያብራራሉ፡፡ ከ73-130 ብር ጭማሪ ያመጣው የደሞዝ ጭማሪ "መንግስት በመምህሩ ላይ ያለውን ጥላቻና ንቀት የገለፀበት ነው" ሲሉ ይገልጹታል፡፡ መምህራኑ መብታቸውን ለማስከበር እንደሚፈልጉ በመነጋገር ላይ ናቸው" ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በዚሁ ዞን "በሱርማና በዲዚ ጐሳዎች ግጭት እስከአሁን ዕልባት ባለማግኘቱ በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እየደረሰ ነው" ይላሉ በዚሁ ሳቢያ ከ1000 በላይ መኖሪያ ቤት የወደመ ስለሆነ ከፍተኛ እርዳታ ያስፈልጋል ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

በቤንቺ ማጂ ዞን ውስጥ 11 ወረዳዎች አስሩ ቡና አብቃዮች ቢሆኑም እሸት ቡና እንዳይሸጥ በካድሬዎች በመከልከሉ አድርቆ ለገበያ ቢያቀርብም ለከፍተኛ ኪሳራ መዳረጋቸውን ይገልጻሉ፡፡ ፍቃድ ያለው ነጋዴ ሲመጣ ገብሬውን አንዱን ኪሎ በ28 ብር እንዲሸጥ ቢያስገድዱም ቡናው እስከ 50 ብር ተሸጧል፡፡ ካድሬዎች እያንዳንዱ ጉዳይ እኛ ካልወሰንን እያሉ በህዝብ ላይ ምሬትን እየፈጠሩ ናቸው፡፡ በማለት አሁን በዞኑ ያለውን ችግር ያብራራሉ፡፡ የቤንቺ ማጂ ዞን መስተዳድርና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዋና የሥራ ሂደት በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡

# የኢትዮጵያ ወጣቶች . . .

ከገፅ 14 የዞረ

ተመሳሳይ የበላይነት መያዙን ሊክድ አይችልም፡፡ በሀገር ውስጥ ጅምላ ንግድ፣በወጪና በገቢ ንግድ (export/import)፣በኢንዱስትሪ በሰፋፊ እርሻዎች በሕንፃ ግንባታ ወዘተ የበላይነቱን የጨበጠ ለመሆኑ መላ የአዲስ አበባ ወጣቶች በሚገባ ያውቁታል፡፡ በ1997 ምርጫ እናንተ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆን ብላችሁ በአንድ ድምፅ ከአዲስ አበባ የሥልጣን ማማ ልታመርዱት በተነሳችሁ ጊዜ፣ሕወሓት ለብሔር አባላቱ ምን እያለ ነበር የሰበከውና ያነሳሳው? "አማራና ጉራጌ ኢንተርሃሞይ መሥርተው ሊያጠፏችሁ ነውና ተነሱ" እያለ ነበር የሚቀሰቅሰው፡፡ ምን ያለበት ዝላይ አይችልም እንዲሉ በመጨረሻም፣የዴሞክራሲ መንገድ እንደማያዋጣው ባወቀ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከራሱ ብሔር በተውጣጡ "አጋዚያን" ሕፃናትና አዛውንት ሳይመርጥ፣በጅምላ አስጨፈጨፈን፡፡ሰኔ 1 1997 እና ጥቅም 2 ቀን 1998፡፡

በሌላ በኩል፣መቼም ወጣቶች የአፍላነት ባሕርያቸው ስለሚያጠቃቸው በቀላሉ ይደለላሉ ብሎ እናንተን ወጣቶችን እየሰበሰበ በውሎ አባል መልክ ሰላሣና ሃምሣ ብር ያድላችኋል፡፡ የእሱ ዓላማ፣ በሚያድላችሁ ገንዘብ ጫት ቅማችሁ፣ድራፍት ቢራ ተጐንጭታችሁ፣ከማንም ጋር ተዳርታችሁ እሱ የሚሠራውን መሠሪ ሥራ ሁሉ ርግፍ አድርጋችሁ እንድትረሱለት ነው፡፡ ይህን ካደረጋችሁ ሙሉ በሙሉ ወያኔ/ኢህአዴግ ካጠመደላችሁ ወጥመድ ውስጥ ገብታችኋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ወጥመድ ለማምለጥ ቅንጅት ይላችሁ እንደነበር፣ገንዘቡ የራሳችሁ ነው፡፡ ተቀብላችሁ ረጠከመሪር ድምፃችሁን ግን ለእነዚያ የወያኔ ካድሬዎች እንዳትሰጡ፡፡

እንደዚሁም እናንተ ወጣቶች ሀገር ለቃችሁ ስትሰደዱ ወያኔ/ኢህአዴግ በእጅጉ ነው የሚደሰተው፡፡በቅርቡ በአብዛኛው የወያኔ/ኢህአዴግ ደጋፊ የሆኑ ወደ 150 የሚጠጉ የአስኮብላይ /ባሪያ ፈንጋይ ይሏቸዋል/ ድርጅቶች፣እዚህ ባለው የሳውዲ ኤምባሲ ውስጥ ባደረጉት ውይይት፣ ሳዑዲ አረቢያ ከኢትዮጵያ በቀን አንድ ሺ አምስት መቶ ኮብላዮችን /ሠራተኞችን/ ለመቀበል ዝግጁ መሆኗን አስታውቃለች፡፡ ሽንት ቤት ጠራጊ ወዘተ ለማድረግና እንዲሁም በመድሃኒት እያደነዘዙ "ኩላሊት ለመሥረቅ" በአጭሩ የእናንተ ወጣቶች ከሀገር መሰደድ ሕወሓት/ኢህአዴግ የውጥረት ማስተንፈሻ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለሕወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ውጥረት እንደ ማስተንፈሻ ሆነው የሚያገለግሉት የወጣቶች ሀገር ለቆ መሰደድ ከውጭ የሚላክ ሐዋላ ወያኔ/ኢህአዴግ ራሱ ለወጣቶች የሚሰጣቸው ልዩ ልዩ መደለያዎች በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት /ኢሬቴድ/ የሚካሄደው የሐሰት ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ እና ሕወሓት/ኢህአዴግ የሚያራግባቸው የጐሣ ልዩነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ውጤታማ ባልሆኑባቸው አጋጣሚዎች ደግሞ፣ ሕወሓት/ኢህአዴግ እየተሳደበ፣እየደበደበ፣ሰቆቃ እየፈፀመ፣እያሰረና እየገደለ መላ የኢትዮጵያ ወጣቶችን ያስፈራራል፤ ያሸማቅቃል፤ ያፍናል፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ከእነዚህ ሁሉ ወጥመዶች ራሳችሁን ነፃ ማድረግ የምትችሉበት ዘዴ አንድ እና አንድ ብቻ ነው፡፡ በሕብረት እና በአንድነት በጨቋኙና አፋኙ የሕወሓት/ኢህአዴግ ሥርዓት ላይ ያላሰለሰ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ ብቻ ነው፡፡ "እኔ ተቀጥሬ ደመወዝ አገኛለሁ"፤ "የእኔ ቤት አልፈረሰም፤ ዘመዶቼ ሐዋላ ይልኩልኛል፤ የእኔ ሱቅ አልፈረሰም፤ልጆቼን ላሳድግ"፤ወዘተ በሚሉ ሰንካላና ራስ ወዳድ ምክንያቶች ራሳችሁን ከሠላማዊ ትግሉ ካገለላችሁ፣ መከራችሁና ስቃያችሁ ይቀጥላል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሁላችሁንም የሚያስተባብሩ በርካታ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ተከስተዋል፡፡ የዋጋ ንረቱ ያመጣው የኑሮውድነት ሁላችንንም እየጠበሰን ነው፡፡ ከሁሉም የባሰው ደግሞ ሕወሓት/ኢህአዴግ አፅመ ርስታችንን ለመንጠቅ ያወጣው የሊዝ አዋጅ ነው፡፡ ከዚህ የባሰ ምን ይመጣባችኋል? ምን ይመጣብናል? በሥራ ማቆም አድማ አዲስ አበባን ጭር እናድርጋት ሊያም ሚያዝያ 30 1997 እንድገመው፡፡ ከእንግዲህ "የመንግሥት እና የግል ሌቦችን" አንፈራም የሌቦች አለቆችንም አንፈራም፡፡ የአዲስ አበባ ወጣቶች ሆይ አዲስ አበባን ከተቆጣጠራችሁ መላ ኢትዮጵያን ትቆጣጠራላችሁ፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ በጠመንጃ የተቆጣጠራትን አዲስ አበባ እናንተ በዴሞክራሲ መንግድ በድምፃችሁ ተቆጣጠሯት፡፡

ሠላማዊ ትግል ያሸንፋል፡፡